*"ብሉይ ኪዳን ሐሜት "የሌላውን መልካም ስም (ዝና) ማጥፋት መሆኑን ያሳያል። ዮሴፍ በልጅነቱ ስለ ወንድሞቹ ክፉነት ለአባቱ አወራ። "...ወንድሞቹ የሚፈጽሙትንም በደል እያመጣ ለአባቱ ይነግር ነበር" (ዘፍ. 37፥2)። ዮሴፍ የሚያወራው እውነትነት ያለው ቢሆንም፥ መጥፎ ሪፖርት ነበር። ይኸው ቃል በዘኍልቁ ላይ ተጠቅሷል። ከኢያሱና ከካሌብ ጋር የከነአንን ምድር እንዲሰልሉ የተላኩት አሥሩ ሰላዮች፥ "...በእስራኤላውያን መካከል አሳሳች ወሬ አሰራጩ...." ይላል (ዘኍልቁ 13፥32) ስለ ተስፋይቱ ምድር ሰላዮቹ ያሰራጩት ወሬ መልካምነት የሌለው ወሬ ነበር። በአዲስ ኪዳን ደግሞ "ሐሜት" የሚለው ቃል በሁለት ዓይነት መልክ ተገልጿል። አንደኛው፥ "መናገር" ማለት ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ "ተቃራኒ" ማለት ነው። ስለዚህ "ሐሜት" ማለት በሌላው ላይ ተቃራኒ የሆነ ነገር መናገር ማለት ነው። ሐሜት ማለት የሚወራው ነገር እውነትም ቢሆንም ባይሆንም፥ የሌላውን ሰው ስምና ዝና ለማጥፋት ወይም ለማበላሸት የሚወራ ወሬ ነው።"*

የተወራው ወሬ እውነትነትም ቢኖረው፥ ወሬውን በአደባባይ ለሁሉም መናገር አለብን ማለት አይደለም። ብዙ ጊዜ ለራሳችን ነጻነት ለመስጠት፥ ወይም የሚሰማን ሰው እንዳይታዘበን፥ *"ይህን የማወራልህ፥ ተብሎ ያለቀ ወሬ ስለሆነ ነው። እንዴት አንተ ወይም አንቺ አልሰማሽም..."* በማለት ነው። በወሬ ትንሽ ቅመም ጨምረን ከማውራታችን በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ንግግራችን ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት የሚመክረንን እንመልከት። *"ክቶ ከአፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ፥ ነገር ግን ለሚሰሙት ጸጋን የሚሰጥና ለማነጽ የሚጠቅም፥ ለሰዎችም አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ"* ይላል (ኤፌ. 4፥29)። ሐሜትን ከማውራትም ሆነ፥ ከመስማት ራስን መጠበቅ እንዴት ይቻላል? ሐሜት የሚያመጣውን ጉዳት የተረዱ ሁለት ክርስቲያን ባልና ሚስት፥ ለራት ሰዎችን ሲጋብዙ፥ ተጋባዦች በግልጽ ማየት እንዲችሉ፥ ግድግዳቸው ላይ በትልቁ *"በመካከላችን ያልተገኘ ሰው ስሙና ታሪኩ በቤታችን አይጠራም"*



የሚል ጽሁፍ ጽፈው ይለጥፋሉ። ይሄም ለጋባዦችም ሆነ ለተጋባዦች በጣም ጥሩ ማስጠንቀቂያ ይሆንላቸዋል። እንዴት ግሩም አሳብ ነው! ራሳችንን ከሐሜት ለመጠበቅ ይህን የመሰለ ጥንቃቄ እናድርግ ይሆን?

ብዙ ጊዜ ሳናስብ በችኮላ በመናገራችን ምክንያት፥ ራሳችንን ችግር ውስጥ እንጥላለን። ከመናገራችን በፊት፥ በማሰብ ፈንታ፥ ከተናገርን በኋላ፥ ስለ ተናገርነው ነገር የማሰብ ጸባይ አለን። አማርኛ ተናጋሪ የሆንን ሁሉ የምናስበው በአማርኛ ነው። በእንግሊዝኛ ለመናገር ስንፈልግ፥ በአዕምሯችን የምናስበውን ወደ እንግሊዝኛ እየተረጎምን እናቀርበዋለን። ሳናስብ ዝም ብለን የመጣልንን ለመናገር ብንሞክር፥ እንግሊዝኛውን ስብርብሩን ነው የምናወጣው። በዚሁ ዓይነት በጥንቃቄ ሳናስብ የመጣልንን ሁሉ የምንናገር ከሆንን፥ በራሳችንም ሆነ በሌሎች ሰዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሳችን የታወቀ ነው። ብዙ ጊዜ "ለምን እንዲህ ብዬ ተናገርኩ?" ብለን እንጸጸታለን። የእግዚአብሔር ቃል *"ሳያስብ በችኮላ ከሚናገር ሰው ይልቅ አዕምሮ የጎደለው ሰነፍ የተሻለ ተስፋ አለው"* ይላል (ምሳሌ 29፥20)። "እከሌ ሠረቀ" የሚል ወሬ ብንሰማ፥ እውነት መሆኑን ሳናረጋግጥ፥ "ሠረቀ" የተባለው ሰው የሚሰጠውን ምክንያትና አስተያየት ሳንሰማ "ሠረቀ" ብቻ ሳይሆን፥ ለጆሮ እንዲጣፍጥ ጨማምረን "ባንክ ሰብሮ ሠረቀ" ብለን እናወራለን። ለምሳሌ ባልና ሚስት ተጋጭተው፥ ከሁለቱ አንደኛው ምክር ለመጠየቅም ሆነ የሚያዝንለት ሰው ለማግኘት፥ የትዳር ጓደኛው ያደረሰበትን በደል ወደ አንድ ሰው ዘንድ ሄዶ ችግሩን ይገልጻል። ሰሚው በአንድ ወገን ያለውን ታሪክ ብቻ ሰምቶ ቢፈርድ፥ ስለ ሌላው ሰው ያለው አስተያየት መጥፎ ቢሆን፥ እንዲሁም አንድ አቅጣጫ የያዘውን ወሬ ለሌላው ቢያስተላልፍ፥ ትልቅ ስህተት ይሠራል። በዚህ ዓይነት የተጋጩትን ባልና ሚስት ከመጥቀም ይልቅ የበለጠ ሊያራርቃቸው ይችላል። እንዲሁም፥ የራሱንም የግል መንፈሳዊ ሕይወት ያበላሻል። ያዕቆብ *"ወንድሞቼ ሆይ! እርስ በርሳችሁ አትተማሙ፥ ሰውን የሚያማ ወይም በሰው ላይ የሚፈርድ ሕግን ያማል"* ይላል (ያዕ. 4፥11)። ስለዚህ "ተበደልኩ" የሚለውን ሰው ብቻ ሰምተን ከመፍረድ ወይም

ለምሳሌ፥ መሰለች የጸሎት ጥያቄውን ያቀረበችው ከላይ በገለጽነው ምክንያት አይደለም ብለን እንመን። "ለመሆኑ ትዳራቸው ላይ ችግር እንዳለባቸው በምን አወቀች? ማን ነገራት?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። አንድ ቀን ሳሙኤልና ትሁት ሆስፒታል ሰው ጠይቀው ሲወጡ፥ በአንድ ምክንያት የጋለ ክርክር ሲያደርጉ ስላየቻቸው፥ "ችግር ሳይኖርባቸው አይቀርም" የሚል የራሷን ግምት ወስዳ ይሆናል። አባባሏ "ሳይሆን አይቀርም" በሚል ከሆነ ትልቅ ስህተት ነው። ባልና ሚስት በውይይታቸው ሁልጊዜ የሚስማሙ፥ ምንም የማይጨቃጨቁ አድርጎ መገመት፥ የጋብቻን እውነተኛ ተፈጥሮና ባሕሪ አለመረዳት ይሆናል። "ሳይሆን አይቀርም" በሚል ግምት ብቻ ስለ ሌሎች ክርስቲያኖች ማውራት፥ የምናወራው ከልብ በመቆርቆር እንኳን ቢሆን ትልቅ ስህተት ነው።

በሌላ በኩል መሰለች እንዳለችው ሳሙኤልና ትሁት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የቀዘቀዙና በጋብቻቸውም ላይ ችግር ይኑርባቸው ብለን እንውሰድ። ይህንን ይዞታቸውን መሰለች እንዴት ማወቅ ቻለች? ችግራቸውን ራሳቸው እስኪያስተካክሉት ድረስ ማንም ሰው እንዲያውቅባቸው አይፈልጉም ይሆናል። ይህ የግል ጉዳያቸው እንጂ በአደባባይ የሚወጣ የሕዝብ ጉዳይ አይደለም። ምናልባት በመንፈሳዊ ሕይወቷ ብርቱ ስለመሰለቻቸው መሰለች በጸሎት እንድትረዳቸው ይህንንም በሚስጥር እንድትይዘው አስጠንቅቀው ነግረዋት ይሆናል። ይሁን እንጂ፥ ከፈቃዳቸው ውጪ በመሰለች አማካኝነት የግል ችግራቸው፥ የጓዳቸውና የቤታቸው ሁኔታ በአደባባይ በጸሎት ስም መታወጁ ትክክል አይደለም። ይህ ዜና ለብዙዎች በመድረሱ ሳሙኤልና ትሁት ማወቃቸው አይቀርም። ሳሙኤልና ትሁት በጸሎቱ ከሚያገኙት ዕርዳታ ይልቅ፥ አሉባልታው ይበልጥ ይጎዳቸዋል። በዚህ ምክንያት ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመቅረብ ይልቅ እየሸሹ ይሄዳሉ።

## 4.2. <u>*አሉባልታ ጎጂነቱን ባለማወቅ ነው*</u>

ክርስቲያኖች የሌላውን ሰው ድካም (ውድቀት) ለማውራት የሚፈልጉበት ምክንያት ምን ይሆን? ይሄ ችግር ዓለም አቀፍ



ይመስላል። በጀርመን አገር በ1920 (እ.ኤ.አ.) ክርስቲያኖች በጋራ የሚኖሩበት የአማኞች ሕብረት ተቋቁሞ ነበር። የሀሜትና የአሉባልታ ምላስ ሕብረታቸውን እንደሚያጎድፈው አስቀድመው ስላወቁ በዚህ ሕብረት ውስጥ ከነበራቸው ልዩ ልዩ የመተዳደሪያ ደንብና ሕግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የነበረው፥ "ማንኛውም አማኝ በሌላው አማኝ ላይ የፍርድ ቃል (የመኮነን) ቃል እንዳይናገር የሚል ነበር። ክርስቶስም በተራራው ስብከቱ ላይ ይህንኑ አስተምሯል። *"በእናንተ ላይ እንዳይፈረድባችሁ በማንም ላይ አትፍረዱ፥ ምክንያቱም በሌሎች ላይ በምትፈርዱበት ዐይነት በእናንተም ላይ ይፈረድባችኋል። እንዲሁም በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል"* ይላል (የማቴ. 7፥1-2)። ክርስቶስ ሊያስተላልፍ የሞከረው ትምህርት፥ ሌላው ላይ መፍረድ፥ መንቀፍና መተቸት ክርስቲያናዊ ተግባር አለመሆኑን ነው። ግብዝ በራሱ ዓይን ላይ የተጋደመውን ግንድ በማንሳት ፈንታ በሌላው ዓይን ላይ ያለውን ትንሽ ስንጥር ለማንሳት ይሞክራል። ይሁን እንጂ፥ በመካከላችን ያሉትን ሀሰተኛ ነብያትና አስተማሪዎችን ለይተን ማወቅና በእነርሱ ላይ መፍረድ የለብንም ማለት አይደለም። እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአግባቡና በሥርዓት የማይራመዱ መታረም፥ መቀጣት፥ አስፈላጊ ከሆነም ከአገልግሎት መገለል የለባቸውም ማለት አይደለም።

የደከመውን በመደገፍ ፈንታ ማጋለጥ፥ ለፍርድ ማቅረብ ጥንትም ቢሆን በሃይማኖት ሰዎች አካባቢ የተለመደ ባህሪ ነበር። በክርስቶስ ዘመን አንዲት ሴት ስታመነዝር አግኝተው ክርስቶስ እንዲፈርድባት እያዳፉ ይዘዋት መጡ። ክርስቶስም ኃጢአተኛዋ እርሷ ብቻ ሳትሆን እነርሱም እንደሆኑ በሚገባቸው መንገድ ለማሳየት *"ከእናንተ መካከል ኃጢአት የሌለበት በመጀመሪያ ድንጋይ ይወርውርባት"* ሲል ነጻነት ሰጣቸው (የዮሐ. 8፥7)። በክርስቶስ ፊት መዋሸት እንደማይችሉ ስለተገነዘቡ፥ ክሳቸውንና የተከሰሰችውን ሴት ከክርስቶስ እግር ሥር ጥለው ጠፉ። ኢየሱስ ግን በመፍረድ ፈንታ፥ "ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ" በማለት ካስጠነቀቃት በኋላ በነጻ አሰናበታት። የሀሜትና የአሉባልታ ምላስ ሹል በመሆኑ በጣም ይጎዳል። አሉባልታ ጎጂ መሆኑን እያወቁ፥ አሉ

ባልታ ሲያወሩ ሕሊናቸውን የማይቆረቁራቸው ለምን ይሆን? "ኃጢአት ሲደጋገም እንደ ጽድቅ ይቆጠራል" የሚል አባባል እንዳለ እናውቃለን። አሉባልታንና ሀሜትን ብዙ ጊዜ በሕይወታቸው የተለማመዱ ህሊናቸው ደንዝዞ ኃጢአትነቱ ስለማይሰማቸው ነው። ብዙዎች ፍቅራቸውንና ሕብረታቸውን የሚያዳብሩት አሉባልታ በማውራት ነው። ተገናኝተው ሌላውን እየቆራረጡ፣ እያሳነሱ ሲያወሩ ሞቅ ይላቸዋል። ሁለት አሉባልታ የሚወዱ ሰዎች በሌላ ነገር እርስ በርሳቸው ባይጣጣሙ፣ በሀሜት ወሬያቸው ግን በጣም ይግባባሉ። ስለሆነም፣ ሲገናኙ ሁልጊዜ ማውራት የሚፈልጉት እነርሱን ስለሚመለከታቸው ጉዳይ ሳይሆን፣ ስለሚያሙት ሰው ነው።

የአሉባልታና የሀሜትን ጎጂነትና አደገኛነት አስጠንቅቀው የሚናገሩና የሚጽፉ፣ በክርስትና እምነት ውስጥ ያሉ ብቻ ሳይሆኑ ዓለማውያንም ጭምር ናቸው። የአሉባልታንና የሀሜትን ባህሪና እንዲሁም የሚያስከትለውን ጉዳት ከተረዱት ፈላስፋዎችና አዋቂዎች መካከል፣

*(1) ሸሪዳን-- "አሉባልታ አውሪዎች 'ምን እያደረጋችሁ ነው?' ተብለው ሲጠየቁ የሚሰጡት መልስ፣ 'ውሸት እየሸቃቀጥን ነው' የሚል ነው አለ።*

*(2) ፓስካል-- አሉባልታን ሲገልጽ "የአሉባልታ ትክክለኛ ትርጉም፣ ሁለትና ሁለት አምስት ነው ብሎ ማውራት ነው" አለ።*

*(3) ፕሳቱስ-- "አሉባልታ አውሪዎችና አሉባልታ ተቀባዮች (አድማጮች) ሁለቱም በስቅላት መቀጣት አለባቸው። አውሪውን ምላሱን ይዞ ማንጠልጠል፣ ሰሚን ደግሞ ጆሮውን ይዞ ማንጠልጠል ነው" አለ።*

*(4) ሶቲል የተባለው ምሁር ደግሞ የአሉባልታን አደገኛነት ሲገልጽ፣ "አሉባልታ አውሪዎች የሚያጠፉት ጥፋት እሳትና ሰይፍ ከሚያጠፉት ይበልጥ ፈጣንና አደገኛ ነው" አለ።*



## 4.3. <u>በጥላቻ ምክንያት</u>

አሉባልታና ሀሜት ይጎዳል እንጂ ማንንም አይጠቅምም። ሀሜተኛው ሀሜት በሚያወራበት ሰው ላይ የጥላቻ እንጂ የፍቅር መንፈስ እንዳለበት አያንጸባርቅም። በሌላው ላይ አሉባልታ ማውራት ያንን ሰው ድምጽ በሌለው መሣሪያ እንደ መግደል መሆኑን ብንረዳ ብዙዎቻችን ራሳችንን እየነጨን ንስሀ እንገባ ነበር። አንድ ጊዜ በውሻው በጣም የተናደደ፣ በራሱ እጅ ተኩሶ መግደል ያልፈለገ አንድ ሰው ውሻውን፣ *"ሂድ ከፊቴ ጥፋ፣ እኔ በእጄ ተኩሼ አልገድልህም። መጥፎ ስም ብቻ እሰጥሃለሁ"* በማለት ውሻውን ገበያ መካከል ውስዶ ከለቀቀው በኋላ፣ *"ዕብድ ውሻ... ዕብድ ውሻ!..."* በማለት ጮኸ። የዚህን ሰው ጩኸት የሰማ ሰው ሁሉ፣ ሰውየው የተናገረው ነገር እውነት መሆኑንና አለመሆኑን የሚያጣራበት መንገድ ስለሌለው፣ ራሱን ለማዳን ሁሉም ሸሽቶ ለማምለጥ መሯሯጥ ጀመረ። ይሄ ዕብድ ውሻ ሌላውን ሰው ከመንከሱ በፊት ሁኔታው ያሳሰበው አንድ ሌላ ሰው ሽጉጡን አውጥቶ ያንን ውሻ ተኩሶ ገደለው። የውሻው ባለቤት እንዳወጀው፣ ያ ውሻ ያበደ ውሻ አልነበረም። ይሁን እንጂ፣ "ዕብድ ውሻ" የሚል ስም ስለተሰጠው፣ እንዳበደ በመቆጠሩ ተገደለ። ልክ እንደዚሁ ሀሜትና አሉባልታ በሌላው ላይ ማስወራት፣ እኛ ተኩሰን ባንገድለውም፣ ለገዳይ አሳልፈን እንደመስጠት የሚቆጠር መሆኑን መዘንጋት የለብንም። በአሉባልታና በሀሜት ተመተው የቆሰሉ፣ የደሙና የተጎዱ ስንቶች ይሆኑ? ቤታቸው ብቻ ይቁጠራቸው።

አሉባልታና ሐሜት በእግዚአብሔር ዘንድ ያስጠይቃል። *"በእውነት እላችኋለሁ ሰዎች በሚናገሩት ምንም ጥቅም በሌለው ከንቱ ቃል ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል። ምክንያቱም ከቃልህም የተነሳ ይፈረድልሃል፤ ከቃልህም የተነሳ ይፈረድብሃል"* ይላል (የማቴ. 12፥36-37)። በሌሎች ላይ እንደ ፈረድነው በእኛም ላይ አንድ ቀን ይፈረድብናል። የሚፈረድብንም በጠባያችንና በአኗኗራችን ይዞታ ሳይሆን፣ በምላሳችን በሌሎች ላይ ባደረስነው ጉዳት መጠን ነው። በእኛ አሉባልታና ሀሜት ምክንያት ሌላው የነበረውን መልካም ስም ቢያጣ፣ ከሥራው ቢባረር፣ ከሌላው ሰው ጋር አንድነቱና ግንኙነቱ እንዲሻክርና እንዲበላሽ ብናደርግ፣

በቤተሰብ መካከል ብጥብጥና ጠብ እንዲፈጠር ምክንያት ብንሆን፥ ለዚያ ሁሉ አንድ ቀን በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂዎች እንሆናለን።

አንድ አዋቂ ሰው የአሉባልታንና የሀሜትን ምክንያት ሲገልጽ፥ *"ጊዜ ለመግደል (ጊዜ ለማሳለፍ) ሲሉ ብቻ አንዳንድ ሰዎች የሰው ስም ይገድላሉ (ያጠፋሉ)"* አለ።

- ➡ *"ታፈሰችን ዛሬ ተብለጭልጫ ጸጉር ሠሪ ቤት አየኋት። ክርስትናውን ችላ ሳትለው አትቀርም..."*
- ➡ *"ኧረ እኔም ከንፈሯን ቀለም ተቀብታ፥ ቅንድቧን ላጭታ አየኋት..."*
- ➡ *"ጸሎት ቤት ካየኋት ብዙ ጊዜ ነው። ጌታን ሳትተው አትቀርም..."*
- ➡ *"ኧረ ከእጮኛዋም ጋር ሳትለያይ አትቀርም። አብረው ሆነው አይቻቸው አላውቅም..."*
- ➡ *"እሰቲ እባካችሁን እንጸልይላት!..."* ይባላል።

ነቀፌታ መልኩን ለውጦና ተሸፋፍኖ የሚቀርበው በአሉባልታና በሀሜት መልክ ነው። ሀሜት አውሪው ሰው ብዙ ጊዜ ስለ ሌላው ሰው ተቆርቋሪ መስሎ ይቀርባል። ብዙ ጉዳት ያመጣል ብለው ስለማያስቡ፥ ሥራ ሲፈቱ ብዙዎች ሀሜትን እንደ ጊዜ ማሳለፊያ ይጠቀሙበታል። ይሁን እንጂ እየቆየ ሲሄድ ያመረቅዝና ወደ ካንሰርነት ይለወጣል። አሉባልታና ሀሜት የሚያዘወትር ሰው፥ ምንም ያህል ጎጂና አጥፊ መሆኑን ቢረዳም፥ በወሬው ልዩ ደስታ ስለሚያገኝበት ራሱን ከዚያ ልማድ ማላቀቅ ያቅተዋል። "ነቀፌታና" አሉባልታ (ሐሜት) የሚለያዩበት በአንድ ነገር ብቻ ነው። ይኸውም፥ ብዙ ጊዜ ነቀፋ የሚያደርገው ተነቃፊው ሰው ባለበት ሲሆን፥ ሀሜትና አሉባልታ የሚወራው ሁልጊዜ ከባለጉዳዩ በስተኋላ ወይም በድብቅ ነው። ምንም ያህል ተቆርቋሪ በመምሰል ይወራ እንጂ፥ አሉባልታና ሀሜት ሰውየው በሌለበት ስምና ዝናውን ዘልዝሎና ቆራርጦ መግደል ነው። ከላይ በምሳሌ እንደተመለከትነው "ለእከሌ እንጸልይለት" በማለት ሀሜትና አሉባልታ ጸሎት መልክ ማቅረብ ሥጋዊነት እንጂ መንፈሳዊነት አይደለም።



## 5. <u>አሉባልታ መለያው ምንድነው?</u>

ሀሜት ጎጂነቱን፥ መለያየቱንና እንደ እሳት ማቃጠሉን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"ክፉ ሰዎች ሌሎችን የሚጎዱበትን መንገድ ያስባሉ፥ ንግግራቸውም እንደ እሳት የሚያቃጥል ነው። ክፉ ሰዎች ሀሜት ያሰራጫሉ፥ ሁከትን በማነሳሳት በፍቅር የተሳሰሩትን ወዳጆች ይለያያሉ"* ይላል (ምሳሌ 16፥27-28)። ሀሜትና አሉባልታ ምን ያህል በሰው ሕይወት አደገኛና መርዛምነት እንዳለው ለማስረዳት አንድ ሰው ይህን ታሪክ በምሳሌ ተናገረ። አንድ ሰው ውሻ ነክሶት ዕርዳታ ለማግኘት ወደ ሀኪም ዘንድ ሄደ። ሀኪሙ በጥንቃቄ ከመረመረው በኋላ ራሱን እየነቀነቀ *"ወንድሜ! በመጥፎ ውሻ ተነክሰሃል። በሕይወት ለመቆየት ያለህ ጊዜ በጣም ጥቂት ቀናት ብቻ ነው፥ አዝናለሁ ምንም ልረዳህ አልችልም"* አለው። ሰውየውም ጥቂት ካሰበ በኋላ ወረቀትና እርሳስ እንዲሰጡት ጠይቆ ለብዙ ደቂቃ ያህል እያሰበ መጻፍ ጀመረ። መጻፉን ጨርሶ ሊነሳ ሲል፥ ኑዛዜውን የጻፈ ስለመሰለው ሀኪሙ *"ይህን ያህል ጊዜ የፈጀብህ ኑዛዜህ በጣም ረጅም ቢሆን ነው"* አለው። ሰውየውም ሲመልስ *"ኑዛዜ አይደለም። ከዚህ ስወጣ የምነክሳቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር እያወጣሁ ነበር"* አለው። በዚህ ዓይነት፥ ሀሜትና አሉባልታ የሌላውን ስምና ዝና መግደያ መርዝ መሆኑን ስንቶቻችን ተገንዝበነው ይሆን?

በብሉይ ኪዳን "አሉባልታ" የሚለውን ቃል ይጠቀሙበት የነበረው በጠቅላላው መጥፎ ሪፖርት ሲሰጥ ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ "አሉባልታ" ማለት የሌላውን ሰው ጥሩ ስም መግፈፍ ወይም ዝናውን ማጉደፍ ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን ደግሞ "አሉባልታ" ማለት በሌላው መፍረድ ወይም የተቃውሞ ድምጽ ማሰማት ማለት ነው። የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሀፊ *"ወንድሞቼ ሆይ! እርስ በርሳችሁ አትተማሙ፥ ሰውን የሚያማ ወይም በሰው ላይ የሚፈርድ ሕግን ያማል፥ በሕግም ላይ የፈርዳል"* ይላል (ዕብ. 4፥11)። ስለ ሌላው የሚወራው ወሬ ሁሉ አሉባልታ ወይም ሀሜት ነው ማለት አይደለም። ታዲያ መለያው ምንድነው?

(1) ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው፥ ወይም ወሬው የሚወራበት

እያለ አንዱ ሌላውን መጠቆም ይጀምራል። አሉባልታው የፈለቀበትን ምንጭ ለማውጣት መሞከር በገዛ እጅ ሌላ ችግር በራስ ላይ መጨመር ይሆናል። ስለዚህ አሉባልታን ለማስቆም፣ ወሬውን ችላ ማለት አንዱ ጥሩ መንገድ ነው።

(3) በአሉባልታና በሀሜት ነፋስ የነፈሰውን ወሬ ለማረም ወይም ሀሰተኛነቱን ለመግለጽ መሞከር፣ ያልሰሙ ሰዎችን እንዲሰሙ ማድረግ ነው። አሉባልታ እንደ ማንኛውም ኃጢአት ዕድል ከሰጠነው ፈጥኖ ያድጋል። ብዙ ጊዜ ትክክል ያልሆነ ወሬ ስለ እኛ ሰምተዋል በማለት ያንን ለማስተካከል በሞከርን ቁጥር አሉባልታው እየጨመረና እያደገ ይሄዳል። ያልሰሙትም እንዲሰሙት ይሆናል። ሌላው ጉዳይ ስለ እኛ ትክክል ያልሆነ ወሬ ሰምተዋል በማለት ራሳችንን ለመግለጽ ስንሞክር ብዙዎች ስለ ጉዳዩ ፍጹም አለማወቃቸውን እንረዳለን። ቢሰሙ እንኳን ይህን ያህል ለአሉባልታው ሥፍራ ሰጥተውት እንዳልነበረ እንገነዘባለን። እኛ ወሬውን ለማስተባበል ስንሮጥና ስንታገል ሲያዩ፣ ይበልጥ አሉባልታው እውነትነት ይኖረው ይሆናል ብለው እንዲያስቡና እንዲጠራጠሩ ያደርጋቸዋል። ስለ እኛ የተወራውን አሉባልታ በገዛ እጃችን እንዳናስፋፋው እንጠንቀቅ። ብዙ ጊዜ አሉባልታን ችላ ብለን ስንተወው በገዛ እጁ እየጠፋ ይመጣል። "ጊዜ ይለየዋል" በማለት በእርጋታና በጸጥታ ለመተው ስንሞክር፣ ሳናስበው አሉባልታው ሞቶና ተቀብሮ እናገኘዋለን።

(4) ሌሎች አሉባልታ ሲያወሩብን፣ አጸፋውን ለመመለስ እኛም ስለ እነርሱ ማውራት ስንጀምር፣ ይበልጥ እሳቱ ይስፋፋና ወደ ሌሎችም እንዲደርስና እንዲጎዱ ይሆናል። አንዳንድ ተንኮለኛ ሰው "እንዲህ ነህ ብሎ የነገረኝ እከሌ ነው" በማለት ንጹህን ሰው አሳልፎ የሚሰጥበትም ጊዜ እንዳለ ማወቅ ይረዳናል። እኛም ይህን ሰምተን ሳናረጋግጥ ያን ሰው ብንጠላውና ስለ እርሱ ክፉ ነገር መናገር ብንጀምር ትልቅ ስህተት ላይ እንወድቃለን። ስለዚህ አሉባልታን ለማጥፋት ሌላ አሉባልታ ማውራት ይጎዳል እንጂ እየጠቅምም።

(5) አሉባልታና መጥፎ ወሬ ሲወራብን ልባችን ማዘኑና ቅር መሰኘቱ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ፣ በዚህ ልባችን መራራ ሥር ካበቀለና በጥላቻ ከተሞላን የምንጎዳው እኛው ራሳችን ነን። በአሉባልታና በሀሜት ተሰንካክሎና ተፈንካክቶ የሚወድቅ ቢኖር፣ መራራነት ያጠቃው ሰው ብቻ ነው። በአሉባልታው መረበሽ፣ ራሳችንን ከአሉባልታ አውሪዎች ጋር እኩል ማድረግ ወይም እንደነርሱ ማነስ ነው። በአሉባልታ ወሬ መረበሽ እውነቱን እያወቅን ራሳችንን እንደ መጠራጠር ይቆጠራል።

(6) በአሉባልታ ወሬ ተደናግጠን ስለ ራሳችን ያለን ግምትና አስተያየት ዝቅተኛ እንዳይሆን አስፈላጊውን ጥንቃቄ እና ድርግ። ማንነታችንን ሊወስነው የሚችለው አሉባልታና ሀሜት መሆን አይገባውም። ስለ ራሳችን አሉባልታ በሰማን ቁጥር ራሳችንን መደበቅና ማሸሹ አሉባልታውን አይቀንሰውም። ሸሽተን ከተደበቅን፣ ሰዎች የተነገረው አሉባልታ እውነት መስሏቸው እንዲፈርዱብን ዕድል ይሰጣቸዋል።

(7) ደግነታችንን የማይመኙ ሰዎች ጎጂ የሆነ አሉባልታ ሲያስወሩብን ልባችንን ሰፋ አድርገን በንቃት እንቁም። ሊጎዳን የሚፈልግ ጠላት እንደሚታገለን ልብ እንበል። በቀላሉ እንዳይጎዳን ራሳችንን እናጠናክር። ነቀፌታው የተሻለ ሰው ያድርገን እንጂ እንዲጎዳን አንፍቀድለት።

(8) አንዳንድ ሰዎች የአሉባልታ ወሬ ሲያስወሩብን ስንሰማ፣ ይህን ያህል ከፍተኛ ዋጋ አንስጠው። ለእነርሱም አጸፋውን ለመመለስ አንታገል። ክፉ ቃል ስለ እነርሱ ከአፋችን አይውጣ። ስጋትና ጭንቀት ወደ ውስጣችን እንዲገባ የልባችንን በር እንክፈት። ኃይላችንን፣ ቆጥበን ለእግዚአብሔር ክብር እናውለው እንጂ ከእነርሱ ጋር "ለእንካ ሰላምታ" መጠቀሚያ አናባክነው። በጎ የሆነ ነገር ብቻ እንጂ ክፉ ነገር ስሜታችንን አይቀስቅሰው።

(9) የአሉባታ ወሬ ለሚያወሩብን ሰዎች እንጸልይላቸው። በተፈጥሯችን ሰዎች የሚጎዳንን ሉባልታ ሲያስወሩብን ያስቆጣናል፣ እራሳችንን እንድንከላከል ወይም አስፈላጊውን መልስ እንድንሰጥ ያደርገናል። ይሁን እንጂ ትክክለኛ አይደለም። በተዋጋነው ቁጥር የበለጠ መጥፎ እየሆነ ይሄዳል።

ይታያል። ብዙ ጊዜ ችግራችን እግዚአብሔር ትልቅ የሚለውን ኃጢአት፥ እኛ አቃለን እንደ ትንሽ ኃጢአት ስለምንመለከተው ነው።

አሉባልታ የሚጠነሰሰው በአዕምሮ ውስጥ ነው። የሚወለደው በኃጢአተኛው ተፈጥሯችን ውስጥ ሆኖ በእኛ እምቢ ባይነት፥ ቅናትና ምቀኝነት እያደገ ይሄዳል። አድጎ አድጎ አንድ ቀን በግልጽ እስኪፈነዳ ድረስ፥ ራሱን ሰውሮ ይቆያል። ይህን ባህሪ ለማሸነፍ ትልቅ ዲሲፕሊን ወይም ውሳኔ ማድረግን ይጠይቃል። ውሳኔውም ኃጢአት የሆነውን "እምቢ" ትክክል የሆነውን "እሺ!" ማለት የቻልን እንደሆን ነው። ስለዚህ አዕምሯችን ሀሜትንና አሉባልታን እንዳያፈልቅ እራሳችንን እናለማምድ።



# ምዕራፍ ፮

# ተሳዳቢ ምላስ

*"ከቶ ከአፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ፥ ነገር ግን ለሚሰሙት ጸጋን የሚሰጥና ለማነጽ የሚጠቅም፥ ለሰዎችም አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ።"*
*(ኤፌሶን 4፥29)*

ከሰዎች አንደበት የሚወጣው ቃል በራስም ሆነ በሌላው ሰው ሕይወት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ እንደሆነ ባለፉት ምዕራፎች በሰፊው ተመልክተናል። ለዚህ ነው ያዕቆብ "ምላስም እሳት ናት፥ ምላስ በአካል ክፍሎቻችን መካከል የምትገኝ ክፉ ዓለም ናት፥ ሥጋችንንም ሁሉ ታቆሽሻለች" ያለው (ያዕ. 3፥6)። እንደገና የተወለዱ ክርስቲያኖች ሁሉ፥ ረጅም ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመቆየታቸው ብቻ፥ ያደጉ ወይም የበሰሉ ናቸው ማለት አይደለም። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ቢታይባትም፥ ከአባላቱ መካከል አብዛኛዎቹ ሥጋ ማኘክ ሲገባቸው ገና ወተት በመጋት ላይ ያሉ ሕጻናት እንደ ነበሩ ሐዋርያው ጳውሎስ መጀመሪያ በጻፈላቸው መልዕክቱ ላይ ገልጾታል። ለዚህ ነው ሥጋዊ

ከዕንቅልፏ ባና ተነሳች። ለስለስ ባለ ድምጽ "ምነው? ምን ሆንክ?" ብላ ጠየቀችው። በዚህ ወቅት ክፉ ምላሱን ወደ እርሷ ያዞርና በእርሷ ላይ አነጣጥሮ መተኮስ ይጀምራል። "ምን እንድልሽ ትፈልጊያለሽ? ዝም ብለሽ እንደ ግንድ ቀኑን ሙሉ ተጋደሚ! አንቺማ ምን አለብሽ ተኝተሽ ትበያለሽ! ደም መጣጭ (ፓራሳይት) ነሽ!" ብሎ ይሰድባታል። ጸባዩን ብታውቅም፥ "ምነው እኔ ምን አደረግሁህ? ለምን ትሰድበኛለህ?" ብላ ጠየቀችው። በዚህን ጊዜ ወሰን የለህ ድምጹን ከፍ አድርጎ እየጮኸ "አባክሽን ተይኝ! እንግዲህ በጥዋት ተነሳሽ በምላስሽ ልትለበልቢኝ! አንቺ እቤት ውስጥ ትለበልቢኛለሽ፥ የሥራ አለቃዬም አሥር ደቂቃ አረፈድክ ብሎ ይለበልበኛል፥ አሁንስ የት አባቴ ልድረስ?" ብሎ ያለአግባብ መበሳጨት ጀመረ። ጆሮ የሚበጥስ የስድብ መዓት በሚስቱ ላይ አውርዶ ተቻኩሎ ከቤቱ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ወጣ። በዚህ ወቅት ወሰን የለህ ክርስቲያን መሆኑን አስታውሶ፥ "ይህን ዓይነት ክፉ ወይም፥ የስድብ ቃል ከአፌ መውጣት አልነበረበትም፥ በጣም አዝናለሁ" ብሎ አልተጸጸተም። ክርስቲያኖች በሌሉበት አካባቢ፥ ክፉ ቃልን መናገር ወይም መሳደብን ተለማምዶታል።

መኪናው ውስጥ ገብቶ ሞተሩን ሲያስነሳ፥ "ሚስቴ ምን አደረገችኝና ነው ይህን ዓይነት የስድብ መዓት ያወረድኩባት? እርሷንም እግዚአብሔርን በደልኩ" በማለት የአዕምሮ ጸጸት ፈጽሞ አልተሰማውም። ትራፊክ ፖሊስ የለም ብሎ በሚያስብበት አካባቢ ከተወሰነው ፍጥነት በላይ መንዳት ጀመረ። እንደ እርሱ የቸኮለ ሰው የትራፊክ ሕግ ሳይጠብቅ ድንገት ከፊቱ ጥልቅ አለበት። ሊገጨው ትንሽ ነበር የቀረው። ወሰን የለህ በዚህን ጊዜ በጣም ተናደደ። ሰውየውም ባይሰማ፥ የመኪናውን መስታወት ዝቅ አድርጎ እጁን እያወራጨ "ደደብ! የማይረባ! ቆሻሻ! አህያ!" እያለ በሰውየው ላይ የስድብ መዓት አወረደበት። የሚያስደንቀው ነገር ግን መኪናው ኋላ ላይ "ኢየሱስ ያድናል" የሚል ጽሁፍ ለጥፎ፥ "ክርስቲያን ነኝ እወቁልኝ" የሚል ይመስላል። መኪናው ላይ የለጠፈውን ጽሁፍ ያነበበ፥ ወሰን የለህ የተሳደበውን ስድብ የሰማ ሌላ ሰው ቀድሞት እያለፈ፥ "ታዘብኩህ" የሚል ይመስላል አንገቱን ነቅንቆበት ሄደ። ወሰን የለህ የሰውየውን ሁኔታ አይቶ ወደ ራሱ በመመለስ ፈንታ፥ ይሄም ሰው የበለጠ ያበሳጨውና በእርሱም ላይ የስድብ መዓት ያወርድበታል።



ዚህ ዓይነት እየተበሳጨ መሥሪያ ቤቱ ይደርሳል። ሥራ የገባው አንድ ሰዓት አሳልፎ ነበር።

ልክ ቢሮው እንደገባ ከሥራ ባልደረባዎቹ አንዱ፥ አለቃችን "ወሰን የለህ ሲመጣ በቀጥታ እኔ ቢሮ እንዲመጣ' ንገሩት ብሏልና ሂድና አነጋግረው" አለው። ወሰን የለህ እየተንጫነጨ አለቃው ቢሮ ገባ። አለቃውም "ስንት ሰዓት እንደሆነ ለማወቅ ለመሆኑ ሰዓትህን አይተሃል? ዛሬ ደግሞ ምክንያትህ ምን ይሆን?" ብሎ ጠየቀው። ምን ዓይነት መልስ እንደሚሰጥ አስቀድሞ ስለተዘጋጀበት ተዝናንቶ ምክንያቱን መናገር ጀመረ። "ሚስቴ እኩለ ሌሊት ላይ ድንገት ታማ ሆስፒታል ይዣት ሄጄ ነበር። ሌሊቱን ሙሉ ዕንቅልፍ አልተኛሁም። አሁንም እርሷን ባዶ ቤት ጥዬ ነው ወደ ሥራ የመጣሁት" አለው። የወሰን የለህ አለቃም የቀረበለትን ምክንያት ስላልተጠራጠረ ምንም ዓይነት ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠው አሰናበተው። ወሰን የለህም የህሊና ክስ ሊያስጨንቀው ሲገባ፥ እንዲያውም ስለብልጠቱ ራሱን እያደነቀ ወደ ምድብ ሥራው ሄደ። በዚህ ዓይነት ሳምንቱ አልቆ ዕሁድ ደረሰ። ወሰን የለህና ሚስቱ ቤተ ክርስቲያን ሄዱ። በዕለቱ መልዕክት የሚያቀርበው ወሰን የለህ ስለ ነበረ መድረኩ ላይ ወጥቶ እንደ መልአክ ይሰብክ ነበር። "ሚስቴ ግብዝ ብላ በትዝብት ዓይን ታየኛለች" ብሎ አላፈረም። ሁለት ዓይነት መልክ ይዞ መኖርን ስለተለማመደ፥ ሕሊናው ደንዝዟል። እነዚያን ክፉ ቃላት በሚስቱ ላይ በወረወረበት ምላሱ፥ ቅዱስ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል መስበክ ጀመረ። "በአንድ ራስ ሁለት ምላስ" የያዘውን ባሏን ሲሰብክ ቁጭ ብላ ስታዳምጥ ሚስቱ ምን ይሰማት ይሆን? ሐዋርያው ያዕቆብ፥ "ከአንድ አፍ ምስጋናና እርግማን ይወጣሉ፥ ወንድሞቼ ሆይ! ይህ ሊሆን አይገባም። ከአንድ ምንጭ ጣፋጭ ውሃና መራራ ውሃ ሊወጣ ይችላልን? ወንድሞቼ ሆይ! የበለስ ዛፍ የወይራ ፍሬ ሊያፈራ ይችላልን? ወይስ የወይን ተክል የበለስ ፍሬ ሊያፈራ ይችላልን? እንዲሁም ከመራራ ውሃ ጣፋጭ ውሃ ሊገኝ ይችላልን?" (ያዕ. 3፥10-12) ሲል የተናገረው እንደ ወሰን የለህን ዓይነቶችን ነው።

በወደቀው ዓለም ውስጥ እስከ ኖረ ድረስ፥ ሰው ሊያበሳጩት ከሚችሉ ነገሮች ማምለጥ አይችልም። ነገር ግን የሚያስቆጣውን ነገር የሚያስተናግድበትን መንገድ መምረጥ ይችላል። ግማሹ ታግሶ

መበት ምክንያት የተለየ ነው። በመስቀል ላይ ሲሰቅሉት፣ በምስማር ሲጠረቅቁት፣ ሲሰድቡት፣ በጥፊ ሲመቱት፣ ምራቃቸውን ሲተፉበት፣ የሾህ አክሊል ሲደፉበት፣ የለበሰውን ገፍፈው በመውሰድ በልብሱ ቁማር ሲጫወቱበት፣ ጦር ወርውረው ጎኑን ሲወጉት አልተሳደበም። በመሳደብ ፈንታ *"የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው"* ብሎ ነው የጸለየው።

እነርሱ የሚሳደቡት፥ ከአፋቸው እንደ ጦር የሚወጋ ቃል የሚ ወረውሩት ስለ ጽድቅ ሲሉ ሳይሆን፥ *"ለምን አልቀደምኩም፥ ለምን የእኔ ፍላጎት አልተሟላም፥ ለምን የተመኘሁትን አላገኘሁም"* ብለው እንደሆነ ግልጽ ነው። ታሪኩ ተረት ይሁን እውነተኛ የተፈጸመ እንደ ሆነ አላውቅም። አንድ ጊዜ አንድ ሰው አንዱን "ሰደበኝ" ብሎ ከሶ ፍርድ ቤት አቀረበው። ሰዳቢው "አልሰደብኩትም" ብሎ ተከራከረ። ዳኛው ተሰደብኩ ያለውን ሰው "ለመሆኑ ምን ብሎ ሰደ በህ?" ብለው ጠየቁት። *"ምንአባክ! ብሎ ሰደበኝ"* ሲል መለሰላቸው። ዳኛውም *"ይሄማ ስድብ አይደለም"* በማለት ተከሳሹን በነጻ ለቀቁት። ከሳሽ የዳኛውን ፍርድ ከሰማ በኋላ በጣም ተናዶ *"ምንአባክ ማለት ስድብ ካልሆነማ፥ ክቡርነቶ! እርሶም ምናባትዎን!"* ብሏቸው ፍርድ ቤቱን ለቆ ወጣ ይባላል።

ዓለማውያን ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያኖችም የስድብ ቃል ከአፋ ቸው ሲወጣ ይሰማል። መጠኑ ይለያይ እንጂ፥ ሳናውቀው ከሁላች ንም አፍ አልፎ አልፎ ክፉ ቃል ይወጣል። በአፍ ከመተላለፍ ነጻ ብንሆንም፥ አልፎ አልፎ ከሰዎች አፍ በሚወጣ ክፉ ቃል፥ ተጎድ ተን ስለምናውቅ፥ በክፉ ምላስ፥ አጥንት ሰብሮ በሚገባ ስድብ ስሜ ታቸው የተጎዳ፥ የቆሰሉና የደሙ ሰዎች ጉዳታቸው ይገባናል። ተሳ ዳቢው በመሳደቡ ጉዳት ስላልደረሰበት ይርሳው እንጂ፥ የተሰደበው ሰው ግን በቀላሉ አይረሳውም። የሚያሳዝነው፥ የተጎዳው ሰው "ተጎ ዳኹ" ብሎ ስሜቱን ሲገልጹ፥ *"አዝናለሁ! ይህን የተናገርኩት ሳላውቅ ነው። ይቅርታ"* በማለት ፈንታ *"እንዴት በዚህ ዓይነት በቀላሉ ትጎ ዳለህ"* ብለው የሚከራከሩ ሰዎች መኖራቸው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የሚያስደንቀው፥ ተሳዳቢዎቹ የሰደቧቸውን ሰዎች "ስድብህ ጎዳኝ ብለው ቅር ይለዋል፥ ያዝናል" ብለው መጎዳታቸው የማይገልጹ መሆናቸው ነው።



ሁላችንም አልፎ አልፎ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ራሳችንን መቆጣጠር የምንቸገርበት ጊዜ ሊኖር ይችላል። መሀንዲስ፥ ሀኪም፥ ነርስ፥ አስተማሪ ወዘተ. ለመሆን ብዙ ዓመት ትምህርት ቤት ገብቶ መማርን ይጠይቃል። ትምህርት ቤት ሳይገቡና ሳይማሩ ከላይ በዘረዘርናቸው የሥራ ሙያዎች ላይ መሰለፍ አይቻልም። ወላጅ መሆን ከባድ ኃላፊነትና ትልቅ እውቀትና ጥበብ የሚያስፈልገው ቢሆንም፥ ወላጅ ከመሆኑ በፊት ትምህርት ቤት ገብቶ የተማረ ማንም የለም። ስለሆነም፥ ልምምድ የሌላቸው አንዳንድ አዳዲስ ወላጆች ልጆቻቸውን በማሳደግ ሥራ ላይ ተሰልፈው ብዙ ስህተቶ ችን በልጆቻቸው ላይ ይፈጽማሉ። በተለይ እናት (ጥሩ እናት ከሆ ነች) ስለ ልጆቿ ከጥዋት እስከ ማታ ድረስ እንደምትደክም የታወቀ ነው። ለእናት ቀኑ ረጅም፥ ሌሊቱ አጭር ነው። ቀኑን ሙሉ ታግላ መሸት ሲል ያላት ትዕግሥትና ኃይል ስለሚያልቅ በቀላሉ ትበሳጫ ለች። ጥቂት ሲነጫነጩ፥ ምንም ያህል ብትወዳቸውም ብድግ አድ ርጋ ከግድግዳ ጋር ማጋጨት የሚቃጣት ጊዜ እንደሚኖር ግልጽ ነው። በጣም ከመድከሟ የተነሳ አስፈላጊ የሆነ እንኳን ጥያቄ ልጆቿ ቢጠይቋት "ኡ! ኡ!" ብላ መጮኽ የሚቃጣት ጊዜ አለ። በአፏ የመጣላትን ስድብ፥ ይጎዳል፥ አይጎዳም ብላ ሳታስብ ክፉ ቃል ትወረውርባቸዋለች። ክርስቲያን ከሆነች፥ ክርስትያንነቷ የሚ ፈተነው በዚህ ዓይነት ጊዜ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነው "ትዕግሥት" ይታይባታል? ወይስ የስድብ መዓት ከአፏ ይወጣል? አንዳንድ ሰዎች በንዴት ገንፍለው የመጣላቸውን የስድብ ቃል በሰው ላይ ሲወረውሩ፥ ራሳቸውን ለመከላከል፥ አላጠፋሁም ለማ ለት፥ እንዲሁም ከህሊና ክስ ለመዳን *"የሚሰማኝን፥ የልቤን፥ እውነ ቱን መናገሬ፥ ግልጽ መሆኔ ነው"* ይላሉ። እውነቱን መናገር፥ ግልጽ መሆን፥ የሚሰማቸውን ስሜት መግለጽ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በፍቅር፥ በርህራሄና እንዲሁም ራስን በመቆጣጠር መሆን እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

ጸብ ጫሪነት ከሕይወታችን ክፍል አንደኛው መሆን የለበትም። ጸብ ጫሪነት ከቁጣ መንፈስ የመነጨ ሲሆን፥ *"እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን፥ የእኔ ፍላጎት ከሌሎች ሁሉ ቅድሚያ ይሰጠው፥ ወይም የእኔ ብቻ ፍላጎት ይሟላ"* ባይነት ነው። እውነተኛ ክርስቲያኖች

በት ጫካ ውስጥ አይደለም። ደውለህ በሰዓቱ አልደርስም ለምን አት
ለኝም? ጥዋት ከእንቅልፌ ከተነሳሁበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ጊዜም
አላረፍኩም። ውስጥ እግሬ ተቃጠለ። ምን አለ አንተማ ውጭ
ትውላለህ። እኔማ እንደ ሌሎች ሴቶች ባሎች መስለኸኝ ነው። አንተ
ወግና ማዕረግ የምትፈልግ ሰው አይደለህም። እስቲ እከሌን እየው፥
በሰዓት ገብቶ በሰዓት የሚወጣ፥ ሚስቱን የሚያከብር፥ ለሚስቱ
የሚሽቆጠቆጥ ሰው ነው። አንተ ብቻ ነህ በእኔ ላይ የምትጫወተው...
ግድ የለም ጥፋቱ ያንተ አይደለም... ጥፋቱ የእኔ ነው... ንቄ ብተ
ውህ ኖሮ ትሸር ነበር..." በማለት አፏ ላይ የመጣላትን ሁሉ ወረወ
ረችበት።

ከሌሎች ወንዶች ጋር እያወዳደረች የምትፈልገውን ዓይነት
ስድብ አውርዳ ስትጨርስ፥ "ጨረስሽ?" ብሎ ጠየቃት። እርሷም
"ምን ልትል ነው? አንተ እንደሆንክ ምክንያት አታጣ!" አለችው።
እርሱም "በጣም አዝናለሁ! ቀኑን ሙሉ የደከምሽበት ነገር በዚህ
ሁኔታ ማለቁ ያሳዝናል። ይህን ሁሉ የስድብ መአት ሳታወርጅብኝ
ምክንያቴ ምን እንደሆነ ብትጠይቂኝ ኖሮ ጥሩ ነበር። መጽሐፍ
ቅዱስ 'ሰው በልቡ የተረፈውን በአፉ ይናገራል ስለሚል፥' ሁኔታው
የልብሽን አቋም ያሳያል። ይህን ሁሉ ምግብ ያዘጋጀሽው ወደሽ
ኝና አክብረሽኝ ነው? ወይስ 'ይህን ሰራሁ ብለሽ ራስሽን ደስ
እንዲልሽ ነው? ወደሽኝ ቢሆን ኖሮ፥ የተዘጋጀው ለእኔ ከሆነ፥
'እወደሃለሁ የምትይውን ሰው እንዴት ከፍ ዝቅ አድርገሽ ትሰድቢ
ዋለሽ? እንዴት ከሌሎች ወንዶች ጋር እያወዳደርሽ፥ እያጥላላሽና
እያሳነስሽ ትናገሪዋለሽ? አጥጋቢ ምክንያት ባይኖረኝ እንኳን በሰዓቱ
ለእራት ባለመምጣቴ ምክንያት ብቻ ይህን ያህል ከፍ ዝቅ አድር
ገሽ ልትሰድቢኝ ይገባል ወይ? መጽሐፍ ቅዱስ 'ሚስቶች ሆይ!
ባሎቻችሁን አክብሩ' ይላል እንጂ፥ 'ሚስቶች ሆይ! እራት አዘጋጅ
ታችሁ ስትጠብቋቸው በሰዓቱ ያልመጡ እንደሆን ስደቧቸው' ነው
ያለው? ለመሆኑ ክፉ ቃል፥ ስድብ ኃጢአት አይደለም? ክርስትናሽ
እዚህ ላይ የት ነው ያለው?" ሲል ጠየቃት። ንግግሩን አቋርጣ
"ስብከትህን እዚያው ለራስህ አድርገውና፥ ምክንያትህን ንገረኝ"
አለችው። "ምክንያቴ ይሄ ነው። ከሥራ ወጥቼ ወደ ቤት ስመጣ፥
የትራፊክ መብራት ቀዩ አልፎ አረንጓዴው ሲበራ ገና መሄድ

ስጀምር አንድ ትንሽ ልጅ ከየት እንደመጣ ሳላውቅ በርሮ በመ
ኪናዬ ተመቶ ወደቀ። አንቡላንስ ተጠርቶ ልጁ በአስቸኳይ ወደ
ሆስፒታል ተወሰደ። ፖሊስ መንጃ ፈቃዴን፥ የመኪናዋን የባለቤት
ነት ካርድና የኢንሹራንስ ወረቀት ተቀብሎ፥ መኪናዋ የእኔ መሆ
ኗን፥ ወንጀል ያለብኝ መሆን አለመሆኔን ሲመረምር ቆየን። ፖሊሱ
እንደጨረሰ፥ የተገጨው ልጅ በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማየትና
ለመጠየቅ ሆስፒታል ሄድኩ። ሁሉን እንደ ጨረስኩ ወደ ቤት
መጣሁ። በአደጋ ምክንያት ደነገጥኩ። አሁን ደግሞ ጨካኝ በሆ
ነች ሚስት ምላስ ተገረፍኩ። ምክንያቴ ገባሽ?" በማለት መልስ
ሰጣት። "ጥፋተኛ ነኝ! አዝናለሁ" በማለትና ሁኔታውን በማስተካከል
ፋንታ "ብላ፥ አትብላ" ሳትል ሁሉንም ነገር ጠረጴዛው ላይ እንዳለ
ትታ መኝታ ቤቷ ገብታ ተኛች።

ይህቺ ሴት ራሷን መቆጣጠር ብትችል ኖሮ፥ ብዙ ጥፋት አት
ሠራም ነበር። "ክርስቲያን ብዬ ራሴን ከጠራሁ፥ ባሌንም ሆነ ሌላ
ሰው መሳደብ፥ ክፉ ቃል ከአፌ ማውጣት ይገባኛል ወይ?" ብላ
ብታስብ ኖሮ ራሷን መቆጣጠር ትችል ነበር። እንዲሁም ትዕግሥት
ኖሯት ምክንያቱን ብታዳምጥ ኖሮ፥ ከላይ የሰማነውን ዓይነት ክፉ
ቃል ከአፏ አይወጣም ነበር። አንዳንድ ክርስቲያኖች ኃጢአት
ምን እንደሆነ የገባቸው አይመስሉም። ለነርሱ ኃጢአት ማለት
"መስረቅ፥ ዝሙት ማድረግ፥ መግደል..." ብቻ ነው። በአሁኑ ጊዜ
መሳደብ ፈጽሞ ኃጢአት የማይመስላቸው ብዙ ናቸው። በየክርስቲ
ያን ቤቱ የሚደረገውን ይቃል ልውውጥ የሚቀዳ መቅረፀ ድምጽ
(tape recorder) በስውር ለአንድ ወር ያህል ቢቀመጥ ምን ዓይነት
የሚያሳፍር፥ "እነዚህ ክርስቲያኖች ናቸው ወይ?" በማለት የሚያስ
ጠይቅ የስድብ ቃል ይሰማ ነበር። ሚስቶቻቸውን በመስደብ የሚያ
ዋርዱ፥ በጥርጣሬ ተሞልተው "የት ሄድሽ? ...የት ገባሽ? ...ማን
አየሽ?" እያሉ መከራ የሚያሳዩ ወንዶች አሉ፥ እንዲሁም፥ ባላቸ
ውን የማያከብሩ፥ "...አንተም ወንድ ተብለህ ትጠራለህ?... የወንድ
አልጫ..." ብለው የሚሳደቡ ሴቶች አሉ። የሚያሳዝነው በዚህ ክፉ
በተናገሩበት፥ በተሳደቡበት ምላሳቸው ቤተ ክርስቲያን ሄደው የሚ
ዘምሩ፥ የሚሰብኩ መሆናቸው ነው። እንደነዚህ ዓይነቶቹን ለማሳ
የት ነው ሐዋርያው ያዕቆብ "ከአንድ አፍ ምስጋናና እርግማን ይወ
ጣሉ፥ ወንድሞቼ ሆይ! ይህ ሊሆን አይገባም። ከአንድ ምንጭ

ጊዜ ያለንበት ሁኔታ እጅግ ትዕግስትን የሚፈትን ከመሆኑ የተነሳ ረጋ ብለን ለመናገር ያስቸግር ይሆናል። ሆኖም እግ ዚአብሔር ጸጋውን እንዲያበዛልን በመጸለይ ትዕግሥትና ዕርጋታ የተሞላበት ንግግር ለማድረግ በየጊዜው ጥረት ልና ደርግ ያስፈልጋል።

(ለ) በጨዋነት የሚናገር ሰው በፊቱ ገጽታ ላይ የሚታየው ሁኔታ የሚስብ እንጂ የሚገፋተር አይደለም። አንዳንዶቻችን ብዙ ጊዜ አሳባችንን የምንገልጸው በቁጣ ምክንያት ስሮቻችን ተግተርትረው፣ ዓይኖቻችን ፈጥጠው፣ ከንፈሮቻችን እየተን ቀጠቀጡ፣ ቁና ቁና እየተነፈስን ነው። እነዚህ ሁሉ የጨዋነት ምልክት አይደሉም።

(ሐ) ጨዋን ሰው "ጨዋ" የሚያሰኘው አንደኛ ከአፉ በጎ እንጂ ክፉ ቃል ስለማይወጣ ነው። እርግጥ ነው ጨዋነት በራሳችን ጥረት አይመጣም። ጨዋነት ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች መካከል አንዱ ነው። *ስድብ፣ ወቀሳ፣ ማጉረምረም፣ በደል ቆጠራ፣ የፍርድ ቃል የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ እንዳልሆነ ግልጽ ነው።* ጨዋ የሆነውን ኢየሱስን በሕይወታችን ስናስገባ፣ መንፈስ ቅዱስ ውስጣችንን እንዲለውጥ ስንፈቅድለት፣ የክ ርስቶስ ጨዋ የሆነ መንፈስ በእኛ ሕይወት ውስጥ በግልጽ መታየት ይጀምራል። ጨዋነታችንም የሚታወቀው ከአፋችን በሚወጣው ቃል ነው። ጨዋነታችንን የሚያሳይ ነገር ከአፋ ችን የማይወጣ ከሆነ፣ የፈለግነውን ዓይነት የሃይማኖት ሥር ዓት ብንፈጽምም፣ ከጌታ ጋር ቅርበት እንደሌለን በግልጽ ይታወቃል።



# ምዕራፍ ፯

# ውሸተኛ ምላስ

*"እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፣ ምክንያቱም አሮጌውን ሰው ከነሥራው አውልቃችሁ ጥላችሁታል። አዲሱንም ሰው ለብሳችሁታል፣ ይህም አዲስ ሰውነት እርሱን በሙላት ወደማወቅ ያደርሳችሁ ዘንድ ፈጣሪው እግዚአብሔር በራሱ መልክ ምሳሌ ዘወትር እንዲታደስ የሚያደርገው ነው።"*
(ቆላስይስ 3፥9)

ዓለማችን የመልካም ሥነ ምግባር ሥርዓተ ሕግ የሚጣስበት፣ ውሸት ጎልቶ የሚታይበት ዓለም ነው። ውሸት በዓለማችን ውስጥ ምን ያህል እንደ ሰለጠነ ለማየት በምሁራን ተጠንተው የቀረቡትን አንዳንድ እስታትስቲክስ መመልከቱ ይጠቅማል። ለምሳሌ፣ ከአሜ ሪካ ሕብረተሰብ ውስጥ፣

- *ታክስ ከሚከፍለው ሕዝብ ሰላሳ አምስት ከመቶ (35%) እውነቱን ሪፖርት አያደርግም፣*
- *የበላይ ባለሥልጣናት በዓመት 40 ቢሊየን ዶላር ከመሥ ሪያ ቤታቸው እየዋሹ ይሠርቃሉ፣*

➡ *ከመሥሪያ ቤታቸው "ጊዜ" የሚሠርቁ፣ ይኸውም ሳይታመሙ "ታምሜአለሁ" ብሎ በመቅረት የሚያባክኑት ጊዜ በገንዘብ ተተምኖ ከ$150 እስከ $350 ቢሊየን ዶላር እንደሚሆን ታውቋል።*

➡ *በሥራ ዓለም ውስጥ ከተሰማሩት ሰዎች መካከል አንድ ሦስተኛው እውነት ያልሆነ የትምሕርት መረጃ (የምስክር ወረቀት) አቅርበው እንደሆነ ተረጋግጧል።*

➡ *የክርስቲያኑ የሥነ ምግባር አቋምም ከዚህ እምብዛም የተሻለ አይደለም።*

እኛ በክርስቶስ በማመን የዳንን ክርስቲያኖች የምንኖረው ከላይ እንደተመለከትነው መልካም ሥነ ምግባር በሚጣስበት፣ ውሸት ባየለበት ዓለም ውስጥ እንደሆነ ግልጽ ነው። በሥራችን ቦታ በየቀኑ አብረናቸው የምንሠራቸው ሰዎች ደግሞ በሥነ ምግባር አቋማቸው፣ በእምነታቸው፣ ባላቸው የሕይወት ፍልስፍና፣ በምርጫቸው፣ በውሳኔ አሰጣጣቸው ከእኛ ፍጹም የተለዩ መሆናቸውን እናውቃለን። እግዚአብሔር እኛን አማኞችን በእነርሱ መካከል ያስቀመጠን ብርሃን (ምሳሌ) እንድንሆን ስለሆነ፣ ምሳሌነታችን ጉልህ ሆኖ መታየት አለበት። ጳውሎስ *"...የዚህን ዓለም ሰዎች ክፉ ጠባይ አትከተሉ"* (ሮሜ 12፥2) ሲል፣ "የዓለም ሥርዓትና ፍልስፍና አይለውጣችሁ፣ ወይም ዓለምን አትምሰሉ" ማለቱ ነው። ዓለም ከእኛ ከክርስቲያኖች ብዙ ይጠብቃል። ይሁን እንጂ፣ በአሁኑ ጊዜ በእኛ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ የሚያየው ግብረ ገባዊ አቋም የላላ በመሆኑ፣ ብዙ ጥያቄዎችን በውስጡ እየፈጠረበት ነው። እውነት ያልሆነውን የመናገር ድካም በሥጋ ከአዳም የወረስነው በመሆኑ፣ በተፈጥሯችን የመዋሸት ዝንባሌ አለን። ይሁን እንጂ እውነት ላልሆነ ነገር እራሳችንን ላለመስጠት ወይም "እምቢ!" ለማለት የሚያስችል ኃይልና ምርጫ እንዳለን እናውቃለን። ሥጋ ለባሾች በመሆናችን ከውሸት ሁሉ ፍጹም ነጻ መሆን ባንችልም፣ እውነትን ለመናገር፣ ስለ እውነት ለመኖር ራሳችንን ማለማመድ እንችላለን።

እግዚአብሔር የእውነት አምላክ ስለሆነ፣ ለሰው ልጅ ምላስን የሰጠው እውነት የሆነውን እንዲናገርበት ነው። በውሸት ሕይወት ውስጥ መኖር የሚያስከትለውን ጉዳት በሕይወቱ አይቶ የተለማመደው ዳዊት በዝማሬው *"አንተ ቅንነትንና እውነትን ስለምትወድ የጥበብህን ምስጢር አስተምረኝ"* አለ (መዝ. 51፥6)። እግዚአብሔር እውነትን እንደሚወድ፣ ውሸትን እንደሚጠላ ሠለሞን ሲገልጽ እንዲህ ይላል። *"እግዚአብሔር ሐሰተኞችን ይጠላል፣ ቃላቸውን በሚጠብቁ ታማኝ ሰዎች ግን ይደሰታል"* (ምሳሌ 12፥22)። መዋሸት፣ እግዚአብሔር ለሙሴ ከሰጠው ከአሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ ዘጠነኛውን ይኸውም፣ *"በማንም ሰው ላይ በሐሰት አትመስክር"* የሚለውን ሕግ ማፍረስ ነው (ዘጸ.20፥16)። በእግዚአብሔር እንድንታመን የሚያደርገን በባሕሪው ውሸትን የሚጠላ፣ እውነትን የሚወድ አምላክ መሆኑን ስለምናውቅ ነው። *"እግዚአብሔር እንደ ሰው አይዋሽም፣ እንደ ሰውም አሳቡን አይለውጥም፣ እርሱ የሚናገረውም ቃል ሁሉ ይፈጸማል"* (ዘኍልቁ 23፥19)። ሰይጣን ግን "የውሸት ሁሉ አባት" እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"...እውነት በእርሱ ስለሌለ ከእውነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፣ እርሱ ሐሰተኛና የሐሰት አባት ስለሆነ ሐሰት በሚናገርበት ጊዜ ከገዛ ራሱ አውጥቶ ይናገራል"* ይላል (የዮሐ. 8፥44)። ከላይ ያነበብናቸው፣ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በልዩ ልዩ ሥፍራ የተጻፉ ጥቅሶች ዓላማቸው እግዚአብሔር እውነትን እንደሚወድ፣ ውሸትን እንደሚጠላ ለማሳየት ብቻ ሳይሆን፣ በእውነት ውስጥ እንድንኖርና እውነትን ብቻ እንድንናገር ለማሳሰብም ነው።

## 1. ውሸት ምንድነው?

በኃጢአት በወደቀ፣ ዓለም ውስጥ ስለምንኖር፣ መጠኑና ዓይነቱ ይለያይ እንጂ፣ ማናችንም ውሸት ከመናገርም ሆነ ውሸት ከሚያስከትለው ችግር ነጻ አይደለንም። አብዛኛዎቻችን በቀን ቢያንስ በያንስ ከ200 ጊዜ በላይ እንደምንዋሽ የሥነ ልቦና ምሁራን ይናገራሉ። ለራሳቸው ነጻነት ለመስጠት አንዳንድ ሰዎች "ይሄ ውሸት ነው፣ ያ ውሸት አይደለም" በማለት ሲከራከሩ መስማት ለብዙዎቻችን እንግዳ ነገር አይደለም። ለመሆኑ ውሸት ምንድነው? ባጭሩ ውሸት "እውነት ያልሆነውን ነገር በመናገር፣ እንዲሁም እውነት ያልሆነውን ነገር በማድረግ ሌላውን ማሳሳት" ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "ውሸት"

የሚለውን ቃል፥ "እውነት የሆነውን ነገር በቃልም ሆነ በተግባር መካድ" መሆኑን ይገልጻል። እንዲሁም በጎ ነገር "እውነት"፥ ክፉ ነገር ደግሞ "ውሸት" እንደሆነ ያመለክታል። ሰይጣን ክፉ መሆኑንና የውሸት አባት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል። *"...እርሱ ከመጀመሪያ አንሥቶ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፥ እውነት በእርሱ ስለ ሌለ ከእውነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፥ እርሱ ሐሰተኛና የሐሰት አባት ስለሆነ ሐሰት በሚናገርበት ጊዜ ከገዛ ራሱ አውጥቶ ይናገራል"* ይላል (የዮሐ. 8፥44)።

ውሸት የሆነውን ቃል በቀጥታ ባንናገርም፥ እውነት ያልሆነው ነገር እውነት እንዲመስል ካደረግን ያም ውሸት ነው። እውነቱ እንዳይታወቅ እውነቱን በከፊል ብቻ መናገርም፥ ውሸት ነው። ለዚህ ነው ፍርድ ቤት ሰዎች ለምስክርነት ሲቀርቡ፥ "እውነቱን ብቻ ሳይሆን ሙሉውን እውነት እናገራለሁ" (not merely the truth but the whole truth" ብለው ቃል እንዲገቡ የሚያደርጓቸው። እርግጥ ነው አንዳንድ ውሸቶች በማንም ላይ ጉዳት የማያደርሱ ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁን እንጂ፥ ጉዳት የማያደርሱ ውሸቶችን እንድንዋሽ ተፈቅድሎልናል ማለት አይደለም። ለምሳሌ አንዷ የለበሰችውን ልብስ እያሳየችን "ያምርብኛል ወይ?" ብላ ብትጠይቀን፥ "አያምርብሽም" ብንላት ቅር ይላት ይሆናል ብለን ስለምናስብ፥ የማያምርባት መሆኑን ብናውቅም አንዳንዶቻችን "ጥሩ ነው፥ ያምርብሻል" ማለታችን አይቀርም። የሰጠናት አስተያየት እውነት አለመሆኑን ብታውቅም፥ "ያምርብሻል" ስንላት ደስ ሊላት ይችላል። እንደማያምርባት እያወቅን "ያምርብሻል" ማለታችን ኃጢአት ነው ወይ? እውነት ያልሆነ፥ ወይም አሳሳች የሆነ አስተያየት ስለሰጠን ውሸት መናገራችን ነው። ውሸት ደግሞ ትልቅም ሆነ ትንሽ፥ ኃጢአት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

ብዙዎቻችን በባሕሪያችን የወጣንበትን ቤተሰብ፥ ያደግንበትን አካባቢ እንመስላለን። አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸው በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑም፥ ሁልጊዜ እውነትን ብቻ መናገር እንዳለባቸው፥ ከዋሹ ግን ከፍተኛ ቅጣት የሚቀጡ መሆናቸውን አስጠንቅቀው ይነግሯቸዋል። በዚህ ዓይነት ሕግ ውስጥ የሚያድጉ ልጆች እውነትን እንጂ ውሸትን መናገር ይከብድብናል። ውሸትን መናገር የማያስቀጣ በሆነበት ቤተሰብ ውስጥ የሚያድጉ ልጆች ግን፥ ልማድ ሆኖባቸው ያለአንዳች ምክንያት፥ ወይም ምንም ዓይነት የሚያስጨንቅ ነገር ሳይደርስባቸው ዝም ብለው የሚዋሹ አሉ። ማርክ ትዌይን *"ጥርጥር ውስጥ ስትሆን፥ እውነቱን ተናገር፥ ይህን በማድረግህ ጠላቶችህን ታስታለህ፥ ወዳጆችህን ደግሞ ታስደንቃለህ"* አለ። "ራስህን ለማሳደግ ከጠቀመህ፥ የምትፈልገውን ነገር እንድታገኝ ከረዳህ መዋሸት መጥፎ አይደለም" በሚል ሕብረተሰብና ዘመን ውስጥ ስላለን፥ አንዳንዶቻችን የፈለግነን ያህል ብንዋሽ ሕሊናችንን አይቆረቁረውም። ሌላው አሳዛኝ ነገር ደግሞ በአንዳንድ ሁኔታ ላይ መዋሸት ጥሩ ነው ብለው የሚያምኑና የሚያስተምሩ የሃይማኖት መሪዎች መኖራቸው ነው። "እውነት" ብዙ ጠቃሚ ጓደኞች አሉት---*መተማመን፣ እምነት፣ ሐቀኝነት፣ ዋስትና፣ ጽናት ወዘተ.* የመሳሰሉት ናቸው። በተቃራኒ፥ "ውሸት" ደግሞ የራሱ የሆኑ ተባባሪዎች አሉት። እነርሱም፥ *አለመተማመን፥ ጥርጥር፥ ግጭት፥ ቂማና ወዘተ* ናቸው። "እውነት"፥ እውነት ባልሆነ ነገር ሲተካ፥ ሁልጊዜ ከላይ የገለጽናቸው የውሸት ተባባሪዎች ይገኛሉ። ቅዱስ አጉስቲን *"እውነት ሲጠፋ፥ ሌላው ነገር ሁሉ ያጠራጥራል"* አለ። በውሸት ምክንያት በሰዎች መካከል መተማመን ሲጠፋ፥ የሰው ግንኙነት ሁሉ የተበላሸ ወይም የፈረሰ ይሆናል። ውሸት ባለበት፥ የቤተሰብ አንድነት ይፈርሳል፥ የመንግሥት አስተዳደር መሠረቱ ይናጋል።

እግዚአብሔር "እውነትን" የመረጠበት ምክንያት፥ የራሱ ተፈጥሮ "በእውነት" ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር የእውነት አምላክ ነው (መዝ. 31፥5). እግዚአብሔር እንደ ሰው ፈጽሞ አይዋሽም (ቲቶ 1፥2)። "አደርጋለሁ" ያለውን ያደርጋል። ኢየሱስ ክርስቶስ "በጸጋና በእውነት" የተሞላ ነው (የዮሐ. 1፥14)። መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ ነው፥ ሥራውም እኛን ወደ እውነት መምራት ነው (ዮሐ. 14፥17፥ 16፥13)። እግዚአብሔርንም የምናመልከው በእውነት ነው (የዮሐ. 4፥24)። ስለዚህ እውነትን ስንናገር፥ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት መፍጠራችን ነው። ውሸት ስንናገር ደግሞ "የውሸት አባት" ከሆነው ሰይጣን ጋር መተባበራችን ነው። የእግዚአብሔር ልጆች ሆነን መኖራችን የልጁን መልክ እንድንይዝ ነው። የእግዚአብሔር ቃል *"...የእግዚአብሔር ልጅ በብዙ*

*ወንድሞች መካከል በኩር እንዲሆን፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ የመረጣቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ ሰለ ወሰነ ነው"* (ሮሜ 8፥29) ይላል። የተቤዠነው የእርሱን መልክ በሕይወታችን እንድናንጸባርቅ ነው። የእርሱ መልክ "እውነት" እንጂ፣ ውሸት አይደለም። የውሸት ተባባሪዎች ስንሆን፣ የእግዚአብሔር ክብር በእኛ ሕይወት ውስጥ እንዳይታይ መሸፈናችን ነው። እግዚአብሔር "እውነት" ስለ ሆነ የእግዚአብሔርን ውበት በሕይወታችን ለማሳየት እውነተኞች መሆን አለብን።

ምንም ዓይነት ዋጋ ቢያስከፍለንም፣ ሁልጊዜ እውነትን ብቻ እንድንናገር መጽሐፍ ቅዱስ ያዘናል። ይህንን ስንል ወግ አጥባቂዎች መሆናችን አይደለም። ሠለሞን *"ደጋግ ሰዎች ሐሰትን ይጠላሉ..."* ይላል (ምሳሌ 13፥5)። ጳውሎስም *"እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፣ ምክንያቱም አሮጌውን ሰው ከነሥራው አውልቃችሁ ጥላችሁታል። አዲሱንም ሰው ለብሳችሁታል፤ ይህም አዲስ ሰውነት እርሱን በሙላት ወደማወቅ ያደርሳችሁ ዘንድ ፈጣሪው እግዚአብሔር በራሱ መልክ ምሳሌ ዘወትር እንዲታደስ የሚያደርገው ነው"* (ቆለ. 3፥9) ሲል ይመክረናል። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "መዋሸት ትችላላችሁ፣ ወይም ብትዋሹ ምንም አይደለም" ያለበት ጊዜ ፈጽሞ የለም። ውሸትን ስንለማመድ፣ ወይም በውሸት ሕይወት ውስጥ ስንኖር ህሊናችን በእግዚአብሔር ፊት እንደማያርፍና ሰላም እንደማይሰጠን፣ ደስታችንም የተሟላ እንደማይሆን የታወቀ ነው። እውነትን ስንናገር ራሳችንን ለእግዚአብሔር ማስገዛታችን፣ በፈቃዱ ሥር መኖራችን ነው።

## 2. ከውሸት ነጻ የሆነ ሰው ይኖር ይሆን?

ከውሸት ፍጹም ነጻ የሆነ ሰው እንደሌለ ከላይ ገልጸናል። ከእግዚአብሔር ጋር ቅርብ ግንኙነት አላቸው ተብለው ይገመቱ የነበሩት ቅዱሳንም እንኳን አልፎ አልፎ በሕይወታቸው ይዋሹ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

- ➤ አብርሃምና ይስሀቅ ሚስቶቻቸውን፣ "እህቴ ናት" ብለው ዋሹ (ዘፍ. 12፥13፥ 20፥2፥ 26፥7)



- ➤ *ያዕቆብ አባቱን ይስሀቅን ዋሸ* (ዘፍ. 27፥19)።
- ➤ *ራሄል አባቷን ላባን ዋሸች* (ዘፍ. 31፥35)
- ➤ የያዕቆብ ልጆች "ዮሴፍን አውሬ በላው" ብለው አባታቸውን ዋሹት (ዘፍ. 37፥29-35)።
- ➤ ለዳዊት ሲል ዮናታን አባቱን ሳኦልን ዋሸ።

"ዩ. ኤስ. ኤ. ቱዴይ" (USA Today) የተባለው ዕለታዊ ጋዜጣ በ1992 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) "መዋሸት" የአሜሪካውያን የመኖር ዘይቤ ነው አለ። ጄምስ ፓተርሰን "አሜሪካ እውነቱን የተናገረችበት ቀን" (The Day America Told the Truth) በሚለው መጽሐፉ ውሸትን በሚመለከት ሀሳብ ላይ የተገኘውን የጥናት ውጤት እንዲህ ሲል ይገልጻል። *"አሜሪካ ውስጥ ከሚኖሩት ሰዎች መካከል 91 ከመቶ (91%) አንዳንድ ጊዜ እንደሚዋሹ ያምናሉ። 86 ከመቶ (86%) ሁልጊዜ ወላጆቻቸውን ይዋሻሉ። 75 ከመቶ (75%) ጓደኞቻቸውን ይዋሻሉ። 73 ከመቶ (73%) ወንድሞቻቸውንና እህቶቻቸውን ይዋሻሉ። 69 ከመቶ የትዳር ጓደኞቻቸውን ይዋሻሉ።"* ይህን መግለጫ ስንሰማ ያስደነግጠን ይሆናል። ይሁን እንጂ "ፈጽሞ አንዋሽም" ያሉት 9 ከመቶዎቹ (9%) እንኳን እውነቱን አልተናገሩም። መጽሐፍ ቅዱስ *"ሰው ሁሉ ሀሰተኛ ነው..."* (መዝ. 116፥11) ይላል። እንዲሁም መዝሙር 12፥2 ላይ *"ሁሉም እርስ በርሳቸው ሐሰት ይናገራሉ፤ አንዱ ሌላውን በማቆላመጥ እየተናገረ ያታልለዋል"* ይላል።

ብናምንም ባናምንም ሁላችንም የምንዋሸው ሳናውቅና ተሳስተን፣ አሊያም ሆን ብለንና እያወቅን ነው። ወይም ተሳስተን፣ ሆን ብለን ወይም እያወቅን ነው። ስለራሳችንም ሆነ ስለ ሌላ ሰው መግለጫ ስንሰጥ እያወቅን፣ እውነት ያልሆነውን ነገር እንሰጣለን። ብዙ ዓይነት ውሸት አለ። ማታለል፣ ከሆነው በላይ አጋኖ ወይም አስመስሎ መናገር፣ እውነትን መደበቅ፣ እውነትን ከውሸት ጋር ቀላቅሎ ማቅረብ፣ እውነት ያልሆነ አሉባልታ ማውራት ከውሸት ዓይነቶች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። እውነትን የማይናገር ምላስ ከፍተኛ አደጋ በሰው ላይ ሊያደርስ እንደሚችል ልንረዳ ያስፈልጋል። ሞኝ ሰው ጥይት በጎረሰና በተቀባበለ ሽጉጥ በመጫወት፣

ቀርበን፥ በሀሰት መስክረን ማንንም አላስቀማንም። በማንም ላይ የሞት ቅጣት አላስፈረድንም። በዚህ በኩል ሕሊናችን እንደማይከሰን እርግጠኞች ነን። በሌላ በኩል ግን ከዚህ ኃጢአት ፍጹም ነጻ አይ ደለንም። ሁላችንም ለአንድ ጌታ፥ ለአንድ መንግሥት አገልግሎት የምንሰጥ መሆናችንን ብናውቅም፥ በእግዚአብሔር ቤት ፉክክርና እሽቅድምድም ሊኖር እንደማይገባ እያወቅን በአገልግሎት ቀድመ ውን የሄዱ የመሰሉንን፥ ወይም ይቀድሙናል ብለን የፈራናቸውን ስለ እነርሱ ጎጂ የሆነ፥ የሐሰት ወሬ በማውራትና በማስወራት፥ የሀ ሰት ምስክርነት በመስጠት፥ ያላሉትን "አሉ"፥ የሚያምኑትን "አያ ምኑም" በማለት አገልግሎታቸው ተቀባይነት እንዳያገኝ፥ ሰው ሸሽ ቷቸው ብቻቸውን እንዲቀሩ አላደረግንም? እግዚአብሔር የተከለ ውን ማንም ሊነቅለው አይችልም እንጂ፥ እንደ ሰዎች ክፋትና ተን ኮል ቢሆን ኖሮ አንዳንዶቻችን ጠፍተን በቀረን ነበር። በዚህ ዓይነት ተገፍተው የቆሙት ይቁሙ እንጂ፥ ሌሎች ደግሞ ልባቸው ተሰ ብሮ፥ "ከውጪ የሚመጣብኝን ጦርነት ልቻለው እንጂ፥ ከውስጥ፥ ከክርስቲያኖች መካከል የሚመጣብኝን ትግል ግን አልችልም" ብለው አገልግሎታቸውን ጥለው የወጡትን፥ የልብ ስብራት የደረሰባቸውን ቤታቸው ይቁጠረው። ዛሬ ክርስቲያኖች ይበልጥ የሚፈሩት የዓለ ማዊውን ሳይሆን፥ የክርስቲያኑን፥ የተራውን ምዕመን ሳይሆን፥ የአ ገልጋዩን ክፉ ምላስ ነው። ከላይ በገለጽነው ዓይነት መንገድ ተጠ ቅመን፥ በመንገዳችን ላይ የቆሙ የመሰሉንን ሁሉ ገፍተን፥ ጥለን የምንሰጠው አገልግሎት "እግዚአብሔርን ያከብራል፥ በጌታ ፊት ያሸልመኛል፥ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል" ብለን ከሆነ፥ በትልቁ ተሳስተናል።

የእግዚአብሔር ሰዎች የእግዚአብሔርን ሥራ ሲያደናቅፉ በየ ትኛውም ዘመን የታየ ነው። በነህምያ ላይ የደረሰው ትግል አንደ ኛው ምስክር ነው። የባቢሎን መንግሥት በዘመኑ ታላላቅ መንግ ሥታትን ያንበረከከ ታላቅ መንግሥት ነበር። በ586 ዓመት ዓለም (ቢ.ሲ.) ኢየሩሳሌምን ያዘ። ከአምላካቸው ጋር እንዳይገናኙ ቤተ መቅደሳቸውን አፈረሰ። ሥርዓት ያለው መንግሥት እንዳይኖራቸው ቤተ መንግሥታቸውን አፈረሰ፥ ሰዎች መጠለያ እንዳያገኙ ቤቶች ንና ከተማዎችን አቃጠለ። ለውጪ ጠላት የተጋለጡ እንዲሆኑ የከ ተማይቱን ቅጽሮች አፈራረሰ። ምርጥ ምርጥ ሕዝቦቿን በምርኮ



ወሰደ። በምርኮ ከተወሰዱት መካከል አንደኛው ነህምያ ነበር። ይህ ሰው ትልቅ ስልጣን የነበረው፥ ተመችቶት የሚኖር ቢሆንም፥ ስለ አገሩ ስለ ሕዝቡ ግድ ይለው ነበር። እግዚአብሔር የፈረሰውን የኢየሩሳሌምን ቅጥር መልሶ እንዲሠራ ሸክም ሰጠው። የእግዚአብ ሔር ዓላማ ሊፈጸም ሲል፥ በጣም የሚቆረቁረው የእግዚአብሔር ጠላት የሆነው ሰይጣንን ነው። ስለሆነም፥ ባለው ኃይል ሁሉ ለማጥ ፋት ቆርጦ ይነሳል። የሚያስደንቀው አንዳንድ ጊዜ ዓላማውን ለማ ስፈጸም ውጪ ያሉትን ሰዎች ሳይሆን፥ ከውስጥ ያሉትን፥ ራሳቸውን የእግዚአብሔር ልጆች (ወገኖች) ነን የሚሉትን ይጠቀምባቸዋል። ነህምያም ይህንን ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ታላቅ አደራ ለመፈ ጸም ሲነሳ፥ ተቃዋሚ ሆነው የተነሱት አሕዛብ ሳይሆኑ፥ ከአይሁድ ወገን የነበሩት ናቸው። *"ሖሮናዊውም ሰንባላጥና ባሪያው አሞናዊ ጦብያ ለእስራኤል መልካም ነገር የሚሻ ሰው እንደ መጣ በሰሙ ጊዜ ተበሳጩ"* ይላል (ነህምያ 2፥10)።

የተጀመረውን የግንባታ ፕሮጀክት ለማጨናገፍ፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላት የሆነው ሰይጣን፥ የእግዚአብሔርን ሰዎች በመጠቀም፥ ልዩ የተንኮል ብልሀቶችን አዘጋጀ።

*(1) የግንባታው ሥራ እንዲጨናገፍ ሀሜትና አሉባልታ አሰራጨ (ነህምያ 6፥6-7)።*

*(2) "ሥራቸው የማይረባ ነው" በማለት ተስፋ እንዲቆርጡ ለማ ድረግ ሞከረ (ነህምያ 4፥1-3)።*

*(3) የማስደንገጥና የማስፈራራት ዘዴ ተጠቀመ (ነህምያ 6፥10)።*

*(4) የሕንጻውን ሥራ ወደ ኋላ ለመጎተት፥ ከውጪ ሳይሳካለት ሲቀር የውስጥ ጠላቶችን ለማነሳሳት ሞከረ (ነህምያ 6፥19)።*

*(5) በጦር ወግተው ሥራውን ለማስቆም ሞከር (ነህምያ 4፥8))።*

ይሁን እንጂ፥ ሰይጣን ዓላማው አልተሳካለትም ነበር። ሰይጣን የማበላሸት ሥራውን ለመሥራት ከውስጥ ተባባሪ ካገኘ፥ የውጪ እርዳታ እንደማይፈልግ ግልጽ ነው። ውሸትን በማስራጨት፥ አሉ ባልታን በመበትን፥ በማታለል ክርስቲያኖች የሰይጣን ተባባሪዎች ሆነው ማየት በጣም ያሳዝናል።

ክርስቲያኖች እያወቁ የሰይጣን አፈ-ጉባኤ መሆንን አይመርጡም። ሰይጣን ይህንን ስለሚያውቅ፥ በተዘዋዋሪ እንጂ ጥያቄውን በግልጽ አያቀርብም። ይህንን በመረዳት ሳናውቅ የሰይጣን መጠቀሚያ እንዳንሆን ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። የመዋሸት፥ የማታለል ምላስ ሰይጣን ሌላውን ለማጥፋትና ለመግደል ሊጠቀምበት እንደሚችል ማወቅ አለብን። በአንደኛ ሳሙኤል መጽሐፍ ላይ የሚያሳዝን ታሪክ እናነባለን (1 ሳሙ. 21፥1-9፥ 22፥6-23)። ዳዊት ሳኦልን በመፍራት በሽሽት ላይ ነበር። ከሳኦል ተከታዮች መካከል አንዱ ዶይቅ የተባለው ሰው የብዙዎች ሕይወት መጥፊያ ምክንያት የሆነውን ወሬ ለሳኦል ስለ ዳዊትና ስለ ካህኑ ስለ አቤሜሌክ በመናገሩ፥ 85 ሰዎች በአንድ ጊዜ እንደ ተገደሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"...ሳኦል አጠገቡ ወደቆሙት ዘብ ጠባቂዎች መለስ ብሉ እነዚህን የእግዚአብሔርን ካህናት ግደሉ! ምክንያቱም እነርሱ ከዳዊት ጋር በእኔ ላይ ዐምፀውብኛል፥ እንዲሁም ሁሉን ነገር እያወቁ ዳዊት መኮብለሉን እንኳ አልነገሩኝም አላቸው። ዘብ ጠባቂዎቹ ግን የእግዚአብሔርን ካህናት አንገድልም አሉ። ስለዚህም ሳኦል ዶይቅን አንተው ግደላቸው አለው! ዶይቅም ተነሥቶ ሁሉንም ገደለ! በዚያን ቀን የፈጃቸው ኤፉድ የሚለብሱ ካህናት ብዛት ሰማንያ አምስት ነበር"* (1 ሳሙ. 22፥17-18)። በዶይቅ በምላስ ምክንያት ብዙ ሕዝብ እንደሞተ በማስታወስ ዳዊት በመዝሙሩ እንዲህ አለ። *"...ሌሎችን ለማጥፋት ለምን ታስባለህ? አንደበትህ እንደ ተሳለ ምላጭ ነው፥ ዘወትር የሐሰትን ነገር ታውጠነጥናለህ"* (መዝ. 52፥2)። ዝቅ ይልና *"አንተ ሐሰተኛ ሰው! ሰዎችን የሚጎዳ ቃል መናገር ትወዳለህ"* ይለዋል (መዝ. 52፥4)።

## 5. <u>እግዚአብሔር እኛን ለመባረክ፥ የእኛን ዕርዳታ አይፈልግም</u>

እግዚአብሔር የማንንም እርዳታ ሳይጠቅ የፈለገውን ዓይነት ተአምር ለብቻው መሥራት ይችላል። እኛን ለመርዳት በውሸታችን አይጠቀምም። በጠቅላላው በዓለም ውስጥ ያለው ወርቅና ብር ሁሉ የእርሱ ናቸው። ሠርቀን፥ አጭበርብረንና፥ ዋሽተን "እንካ" ብለን ልንሰጠው አንችልም። የእውነት አምላክ ስለሆነ፥ በሰይጣን መሣሪያ (በውሸት) በተገኘው ነገር መጠቀም አይፈልግም። ከትምህርት ማጣት የተነሳ አንዳንድ አማኞች እውነት ባልሆነ መንገድ ያገኙትን ነገር፥ ከእግዚአብሔር የመጣላቸው በረከት አድርገው እንደሚወስዱ እናውቃለን። ለምሳሌ፥ ዕቃ ለመግዛት ሱቅ ገብተው፥ የሚፈልጉትን ከገዙ በኋላ ሂሳቡን ለገንዘብ ተቀባዩ ይሰጣሉ። ዕቃውን በ$2 ብር ገዝተው፥ $5 ሰጥተው $3 ብር ምላሽ ሲጠብቁ፥ ገንዘብ ተቀባዩ $20 የተቀበለ መስሎት $18 መልስ ይሰጣቸዋል። ስህተት መሆኑን እያወቁ ገንዘቡን ተቀብለው ይሄዳሉ። ይሄ በውሸት መበልጸግ ነው። የራሳቸው ያልሆነውን ገንዘብ ከመውሰዳቸውም ሌላ፥ ቤተ ክርስቲያን ሄደው *"ጌታ ድንቅ ሥራ ሠራልኝ። $15 በጣም ያስፈልገኝ ስለነበረ፥ ጌታን ለመንኩት። ፈጣን የሆነ መልስ ይሰጠኛል ብዬ አልጠበቅሁም ነበር። ታምረኛው ጌታ በአንድ ሰዓት ውስጥ ከጠየቅሁት በላይ ጨምሮ ሰጠኝ"* ብለው መስክረው፥ ተጨብጭቦላቸው ይወርዳሉ። ገንዘቡን እንዴት እንዳገኙት ግን አይናገሩም። ቢናገሩም አብዛኛው ሕዝብ ያለው የመንፈሳዊ ብስለት ስለሌለው፥ "ይሄማ ዘረፋ ነው፥ ማጭበርበር ነው፥ ስርቆት ነው" ብለው የሚያስቡ ጥቂቶች ናቸው። ይህንን ምስክርነት የሚሰማው፥ እውነትን የሚወድ፥ ውሸትን የሚጠላው እግዚአብሔር ያንን ነጣቂ ሰው *"ጎሽ የእኔ ልጅ! ዋሽተህም ቢሆን አስከበርከኝ፥ አስጨበጨብክልኝ"* ብሎ ሜዳልያ እንደማይሰጠው ያውቅ ይሆን? እግዚአብሔር እኛን ለመርዳት አቅቶት ዋሽተን፥ ነጥቀን እንድናገኝ አያደርግም። ከላይ የሰማነው ምስክርነት ከእግዚአብሔር የመጣ በረከት ሳይሆን፥ ንጥቂያ ነው።

ውሸተን ተጠቅመው "እግዚአብሔር ይህን አደረገልን" የሚሉ ክርስቲያኖች በአሁኑ ጊዜ ጥቂቶች አይደሉም። አንድ ጊዜ አረብ አገር የምትኖር አንዲት ክርስቲያን እህት "ጌታ ያደረገልኝን ተአምር ልመስክርልህ" አለችኝ። "እንደምታውቀው እዚህ አገር ከ15 ዓመት በላይ ኖሬአለሁ። ጌታ ከዚህ ክፉ አገር እንዲያወጣኝ ብዙ ጸልያለሁ። የጌታ ጊዜ ሲደርስ በሩን ወለል አድርጎ ከፈተልኝ። አሁን በቅርቡ አሜሪካ መሄዴ ነው" አለችኝ። እኔም ይህች እህት ብዙ ዓመት አረብ አገር እንደተንገላታች ስለማውቅ ይህንን ዜና ስሰማ ምን ያህል የደስታ ስሜት ውስጤን እንደፈነ

ቀለው የምገልጽበት ቋንቋ ያንሰኛል። እጅግ በጣም ደስ አለኝ። "ለመሆኑ እንዴት ነው የተሳካልሽ? ቪዛ ሎተሪ ደረሰሽ ወይ?" ብዬ ጠየቅኋት። "እኔ አልደረሰኝም፣ ግን እንደ ሚስቱ አድርጎ የሚወስደኝ ሰው አግኝቼ ሁሉን ነገር ጨርሼአለሁ። በቅርቡ ወደ አሜሪካ እንበራለን። ድንቅ አይደለም?" አለችኝ። ደስታዬ ወዲያው ደፈረሰ። እኔም በድፍረት "ይሄማ ውሸትና ማጭበርበር ነው። የእግዚአብሔርን አጥር ዘሎ እንደመሄድ ነው። እግዚአብሔር አንቺን አሜሪካ በትክክለኛው መንገድ ማስገባት አቅቶት በውሸት መንገድ እንድትሄጂ ያደርጋል ብዬ አላምንም" አልኳት። "ኃሌሉያ" ብሎ ያጨበጭባል ብላ ስትጠብቀኝ፣ ሌላ ዓይነት መልስ በመስጠቴ ሳይደንቃት እንዳልቀረ እገምታለሁ። በዚህ ብቻ አላበቃሁም። "የእግዚአብሔርን አጥር ዘለሽ ስትሄጂ፣ አይሮፕላኑ ዓየር ላይ እንዳለ ቢቃጠልስ?" አልኳት። ክፉ እንዲደርስባት መመኘቴ፣ ወይም ላስፈራራት ብዬ አልነበረም። መንገዱ የእግዚአብሔር መንገድ እንዳልሆነ ማየት እንድትችል ብዬ ነው። እንደዚያ ማለቴ የበለጠ ሳያናድዳት እንዳልቀረ እገምታለሁ።

ከዚህ በኋላ ለምን ይህንን መንገድ እንደተጠቀመች እራሷንም እኔንም ለማሳመን ሞከረች። ይሁን እንጂ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሚመለከት አሳብ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው ውጪ መቀበል እንደማልችል ገለጥኩላት። ይህች እህት እንዳቀደችው ተሳክቶላት አሜሪካ መጥታለች። አሜሪካ ከገባች በኋላ ሁሉ ነገር ቢሳካላትና ጥሩ ደሞዝ ያለው ሥራ ብታገኝና ብዙ ገንዘብ ብታጠራቅም፣ መኪና ብትገዛ፣ የተሟላ የቤት ዕቃ ቢኖራት፣ ጥሩ ጥሩ ልብስ ብትለብስ፣ የወሰደችው እርምጃ ልክ መሆኗን የሚያረጋግጥ ምልክት አድርጋ ብታምን፣ ወይም ጥሩ ስላደረገች፣ እግዚአብሔር በእርሷ በጣም ስለተደሰተ የሰጣት በረከት እንደሆነ አድርጋ ብትወስድ ትልቅ ስህተት ነው። በዚህ ዓይነት በውሸት ከብረው "ምንም ያልሆንኩት፣ የተሳካልኝ፣ መንገዴ ትክክል በመሆኑ ነው" ብለው የሚያስቡ እንደማይጠፉ እርግጠኞች ነን። እግዚአብሔር ውሸትን እንደሚጠላ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ እያነበብን፣ እውነቱን እያወቅን፣ "ተቸግሬ፣ ሌላ መንገድ ስላጣሁ ያደረግሁት ነው። የተቸገረን ዋሽቼስ ቢሆን ብረዳ ምን አለበት?" ማለት አያዋጣንም።



ጊዜና ቦታ አይበቃንም እንጂ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሚመለከት ነጥብ ላይ እንደ ምሳሌ ስለተጠቀምንባት እህት ብዙ መግለጽ ይቻል ነበር።

የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽ እየጣስን፣ ቃሉ ከሚናገረው ውጪ እየኖርን፣ የምንፈልገውን ማግኘታችን፣ በረከት ብለን የምንቆጥረውን ቁሳቁሳዊ ነገር ማግኘታችን፣ እግዚአብሔር ስለ ኃጢአት፣ ወይም ስለ ውሸት ፈጽሞ ግድ ስለሌለው ሳይሆን፣ ከምሕረቱና ከጸጋው ብዛት የተነሳ እንደሆነ እንወቅ። የእግዚአብሔርን አጥር ጥሰው፣ ከፈቃዱ ውጪ የሆነውን ነገር አድርገው፣ ሌላ ጥሩ ነገር በመሥራት ለማካካስ፣ የእግዚአብሔርን ልብ ወደ ራሳቸው ለመሳብ የሚሞክሩም አሉ። "እግዚአብሔር በማይወደው መንገድ ተጠቅሜ አሜሪካ ብመጣም፣ ይኸውና ኳየር ገብቼ በዝማሬ አገለግለዋለሁ፣ ሰባኪ ሆኜ እሰብክለታለሁ፣ ሁለትና ሦስት ሥራ እየሠራሁ አሥራቱን በታማኝነት በመስጠት አገልግሎቱን (ቤተ ክርስቲያኑን) በገንዘቤ እየደገፍኩ ነው" የሚሉ አይጠፉም። በዚህ ዓይነት መልክ የመጡ ሁሉ "አያገልግሉ" ወይም "አይስጡ" ማለታችን ሳይሆን፣ "ስለ ምሕረቱና ስለ ጸጋው፣ ሁለተኛ ዕድል ስለሰጣቸው እግዚአብሔርን ያመስግኑት እንጂ፣ የውሸት መንገዳቸውን ትክክል እንደሆነ አድርገው አያቅርቡ ማለታችን ነው።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ እየዋሹ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ከሞከሩት ሰዎች መካከል ሀናንያና ሰጲራ ይገኙበታል። እነዚህ ባልና ሚስት "ቤታችንን ይህን በሚያህል ገንዘብ ሸጥነው" በማለት ያላቸውን ገንዘብ ሁሉ እራግፈው ለጌታ ቤት እንደሰጡ አድርገው በማቅረብ፣ መንፈስ ቅዱስን ለመዋሸት እንዴት እንደሞከሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ጴጥሮስም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ፣ *"ሀናንያ ሆይ! በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንድትዋሽና ከመሬቱም ሽያጭ ከፊሉን እንድታስቀር ያደረገህ ሰይጣን ስለምን ወደ ልብህ ገባ?"* አለው (የሐዋ. 5፥3)። መንፈስ ቅዱስን በመዋሸቱ ምክንያት በባሏ በሀናንያ ላይ የደረሰውን ያላወቀችው ሳጲራ፣ በተራዋ ከሐዋርያት ፊት ቀርባ በምን ያህል ዋጋ ቤታቸውን እንደሸጡት ስትጠየቅ፣ እግዚአብሔርን ለመዋሸት በመሞከሯ በባሏ ላይ የደረሰው ሞት በእርሷም ላይ የደረሰ መሆኑን እናውቃለን። ይሄም በቤተ ክርስቲ

ያን አካባቢ ትልቅ ድንጋጤን ፈጥሮ ነበር። *"በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህን ነገር በሰሙ ሰዎች ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ"* ይላል (የሐዋ. 5፥11)። በዘመናችን የእግዚአብሔርን መንፈስ እየዋሹ በሚኖሩ ኃጢአተኞች ላይ ፍርዱ ፈጥኖ ባለመምጣቱ ብቻ እግዚአብሐር ስለ ኃጢአት ግድ የሌለው መስሏቸው በኃጢአት ውስጥ ተዝናንተው የሚኖሩ ሰዎች እንዳሉ የታወቀ ነው። እግዚአብሔር ይታገሳል እንጂ፥ በእውነት ከማይመላለሱት ጋር አይተባበርም። እግዚአብሔር የእውነት አምላክ ስለሆነ፥ በእውነት ከማይኖሩ ሰዎች ጋር ሕብረት የለውም። ከእውነት ውጪ እየኖሩ በሃይማኖታቸው የሚኮሩትን የሃይማኖት መሪዎች ሕብረታቸው ከማን ጋር እንደሆነ ኢየሱስ ሲገልጽ፥ እንዲህ ይላቸዋል። *"እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ ልጆች ናችሁ፥ ፍላጎታችሁም የአባታችሁን ምኞት መፈጸም ነው፥ እርሱ ከመጀመሪያ አንሥቶ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፥ እውነት በእርሱ ስለሌለ ከእውነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፥ እርሱ ሐሰተኛና የሐሰት አባት ስለሆነ ሐሰት በሚናገርበት ጊዜ ከገዛ ራሱ አውጥቶ ይናገራል"* (የዮሐ. 8፥ 44)።

በሰይጣን ውሸት በተሞላው ዓለም ውስጥ ክርስቲያኖች የዓለም ብርሃንና ጨው ለመሆን ከፈለጉ፥ ሁልጊዜ እውነተኞች ሆነው መኖር አለባቸው። በውሸት የሚገኝ ደስታ ጊዜያው ነው። *"የሐሰት ዕድሜ አጭር ነው፥ እውነት ግን ለዘላለም ትኖራለች"* ይላል (ምሳሌ 12፥ 19)። እግዚአብሔር የምንናገረውን ብቻ ሳይሆን፥ ከውስጥ የሚገፋፋንን ሐሳብ ወይም ምክንያት ጭምር ይመረምራል። የተናገርነው እውነቱን ለመሸፈን፥ ወይም ለማታለል ከሆነ፥ የተናገርነው ቃል እውነትነት ያለው እንኳን ቢሆን፥ እግዚአብሐር በልባችን ተንኮል ምክንያትም ይፈርድብናል። ቀደም ሲል በ1 ሳሙ. 21 ላይ ከሳኦል ተከታዮች መካከል አንዱ ዶይቅ የተባለው ሰው የብዙዎች ሕይወት መጥፊያ ምክንያት የሆነውን ወሬ ለሳኦል ስለ ዳዊትና ስለ ካህኑ ስለ አቤሜሌክ በተናገረው ነገር፥ 85 ሰዎች በአንድ ጊዜ የተገደሉ መሆናቸውን እናስታውሳለን። ዶይቅ ይህን ወሬ ለሳኦል ያወራበት ምክንያት፥ ሌሎችን በማጥፋት ራሱን ለማሳደግ ወይም ለመሾም እንደነበረ ግልጽ ነው። ሌላውን ለማጥፋት ምላሳቸውን በሚጠቀሙ ሰዎች ላይ የእግዚአብሐር ፍርድ ከባድ እንደሆነ ዳዊት ይናገራል።



ውሸት ግለሰብን ብቻ ሳይሆን፥ ሰፊውን ሕብረተሰብ ጭምር ይጎዳል። ውሸት በበዛበት ሀቀኛ የሆነ ፍርድ አይኖርም። ወንጀለኞች በነጻ ይለቀቃሉ፥ ንጹሆች ያለአግባብ ይፈረድባቸዋል። እግዚአብሔር ከሚጠላቸው ሰባት ነገሮች መካከል አንደኛው "ሐሰት የሚናገር ምላስ" እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ምሳሌ 6፥17)። በዘመናት ክርስቶስን በሚጠሉ ሰዎች ምክንያት በሀሰት ተከስሰው ሕይወታቸውን ያጡ ክርስቲያኖች ብዙ እንደሆኑ ታሪክ ይመሰክራል።

አንድ ጊዜ አንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢና ሚስቱ አንዳንድ ችግር ያለባቸውን ሴት ልጆች እቤታቸው እያመጡ ይረዱ ነበር። ከተረጂዎቹ መካከል አንዷ በአንዳንድ ምክንያት ከነርሱ ጋር መስማማት ባለመቻሏ፥ ለማጥቃት ፈልጋ "የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ አስገድዶ የሩካቤ ሥጋ ፍላጎቱን ሊፈጽምብኝ ሞከረ" ብላ ወሬውን በአካባቢው አዳረሰች። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ልጅቷ የተናገረችው ነገር እውነት እንዳልሆነ፥ መጋቢውን ለመጉዳት ስትል ፈጥራ ያወራችው መሆኑን ተናዘዘች። የሚያሳዝነው እውነት አለመሆኑን የተናገረችው ብዙ ነገር ከተበላሸ በኋላ ነበር። ያ መጋቢ በዚሁ እውነት ባልሆነ ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱ ተባሯል፥ የነበረበት "ቤተ እምነት" (Denomination) የክህነት ፈቃዱን ወስዶበታል፤ እንዲሁም የነበረው ዝናና ስም ተበላሽቷል።

የጠሉትን፥ ሊያጠፉት የፈለጉትን ሰው፥ ይህን ዓይነቱን በውሸት የተሞላ የተንኮል ወሬ በማውራት የብዙዎችን ትዳር ያፈረሱ፥ ከአገልግሎት እንዲባረሩ፥ ማንም ሰው እንዳይቀበላቸው ያደረጉ ሰዎች ሁልጊዜ ከመካከላችን አይጠፉም። ልባቸው በቅናት የነደደ፥ በጥላቻ የተሞሉ የጠሉትን ሰው ለመጉዳት የሀሰት ወሬ የሚያወሩ ተንኮለኞች ሰዎች ሁሉጊዜ ሊኖሩ እንደሚችሉ በማወቅ፥ ክፉ ወሬ በተወራበት ሰው ላይ በችኮላ ከመፍረድ መጠንቀቅ ያስፈልገናል። እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት የተወራው ወሬ እውነት መሆን አለመሆኑን ጉዳዩ ከሚመለከተው ሰው መስማቱ ትክክል ያልሆነ ፍርድ ከመፍረድና ያለአግባብ ሌላውን ከመጉዳት ይጠብቀናል። <u>የአንዱን ወገን ብቻ ሰምተን አንፍረድ... አደራ! አደራ! አደራ! አደራ!... ሚሊዮን ጊዜ አደራ።</u> *"እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ ምክንያቱም አሮጌውን ሰው ከነሥራው አውልቃችሁ ጥላችሁ*

*ታል"* (ቆለ. 3፥9) የሚለውን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ብናውቀውም፥ አንዳንዶቻችን እርስ በርሳችን እውነት አንነጋገርም። እግዚአብሔር ሐሰትን በሚናገሩ ሰዎች ላይ የሚወስደውን እርምጃ ዘማሪው ሲገልጽ፥ *"ሐሰት የሚናገሩትን ሁሉ ታጠፋለህ..."* ይላል (መዝ. 5፥6)። የሚያጠፋው ግለሰቡን ብቻ ሳይሆን፥ ሐሰተኛውንም ሕዝብ ጭምር ነው። *"...ሁላችሁም ሐሰት ተናጋሪዎች ናችሁ። ስለዚህ በኃጢአታችሁ ምክንያት እናንተን ለማጥፋትና ለመደምሰስ ተነሥቻለሁ"* (ሚክያስ 6፥13) ይላል።

እኔና እናንተ ስንዋሽ፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት በማፍረስ፥ የራሱን የጨለማ መንግሥት ለመገንባት ከሚጥረው፥ የውሸት አባት ከሆነው ከሰይጣን ጋር እንተባበራለን። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሰይጣን ጋር ከተባበሩት መካከል፥ *ይሁዳ አስቆሮቱ፥ ሐናንያስና ሴልጳስ* (የሐዋ. 13፥8፥ 5፥3) ይገኙበታል። የምንዋሸው ውሸት አንዳንድ ጊዜ ትልቅ ባይመስለንም፥ ስንዋሽ፥ ከሰይጣን ቡድን ጎን ተሰልፈን፥ ሰይጣን ላለበት ቡድን ጎል ማስገባታችን መሆኑን እንወቅ። ይህንን ስናደርግ እግዚአብሔርን መካዳችንና እንዲሁም የራሳችንን ቡድን ማጥቃታችን ይሆናል። ለመለወጣችን እውነተኛ ማረጋገጫ፥ ወይም ምልክት የሚሆነው፥ ከአፋችን የሚወጣው የእውነት ቃል ነው (ቆላስይስ 3፥9-10)። ለክርስቲያን አንድነት ማሠሪያ ያው እውነትን መናገር ነው። አንዱ የሰውነት ክፍል ሌላውን የሰውነት ክፍል እንደማይዋሸው ሁሉ፥ በክርስቲያኖችም መካከል አንዱ ሌላውን መዋሸት እንደሌለበት ጳውሎስ ሲናገር፥ *"ስለዚህ ውሸት አትናገሩ! ሁላችንም የአንድ አካል ክፍሎች ስለሆንን እርስ በርሳችን እውነት እንናገር"* ይላል (ኤፌ. 4፥25)።

ብዙ ጊዜ ስንዋሽ የራሳችንን ጥቅም እንጂ፥ በእኛ መዋሸት ምክንያት ሌላው ሰው የሚጎዳው ጉዳት፥ የሚከፍለው ዋጋ ፈጽሞ አይታየንም። ለምሳሌ አሜሪካ የምንኖር ሰዎች፥ የዓመት ገቢያችንን በየዓመቱ ለመንግሥት ሪፖርት ስናደርግ፥ መክፈል ያለብንን ተገቢ የሆነውን ቀረጥ ላለመክፈል በተለያየ መንገድ ዋሽተን ሪፖርት በማድረግ ከዕዳ ራሳችንን ነጻ እናደርጋለን፥ ወይም ከመንግሥት ተመላሽ ገንዘብ እናገኛለን። ይሁን እንጂ፥ የራሳችንን ጥቅም ለመጠበቅ ስንል ቀረጥ ሰብሳቢውን ክፍል መጉዳታችን፥ እኛ መክፈል ያለብንን ሌሎች እንዲከፍሉ ማድረጋችን አይታወቀንም። አንዳንዶቻችን ይህን ዓይነቱን ማታለል እንደ ውሸት ስለማንቆጥረው፥ በዚህ ዓይነት ዋሽተን ወይም ቀጥፈን የምናገኘውን ተጨማሪ ገንዘብ፥ እግዚአብሔር እንደባረከን አድርገን እንቆጥራለን።

መጽሐፍ ቅዱስ *"ብዙ ሀብት ከሚኖርህ ይልቅ መልካም ስም ቢኖርህ ይሻላል"* ይላል (ምሳሌ 22፥11)። መልካም ስም አንደኛው፥ እውነትን መናገር፥ በእውነት መመላለስ ነው። ምንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍልም እውነተኛነት ለክርስቲያን ትልቅ ሀብቱ ነው። በእውነት ውስጥ ስንኖር "እውነት" የሆነውን ኢየሱስን መምሰላችን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። *"ነገር ግን የጠራችሁ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ እናንተም በኑሯችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፥ ምክንያቱም 'እኔ ቅዱስ ስለ ሆንሁ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ተጽፏል"* ይላል (1 ጴ. 1፥15-16)። የምንኖርባት ዓለም ውሸት የገነነባት ዓለም ናት። አብረናቸው የምንሠራቸው የዓለም ሰዎች ከእኛ ፍጹም የተለየ እምነትና የግብረ ገብ አቋም ያላቸው በመሆናቸው፥ የእነርሱ አቋምና ሥርዓት እኛን አማኞችን እንዳይበርዘን፥ በእነርሱ የሕይወት ፍልስፍና እንዳንመራ መጠንቀቅ ያስፈልገናል። ጳውሎስም *"...የዚህን ዓለም ሰዎች ክፉ ጠባይ አትከተሉ"* (ሮሜ 12፥2) በማለት ይመክረናል። እግዚአብሔር እኛን አማኞችን በጨለማው ዓለም ውስጥ ያኖረን ብርሃናችን በነርሱ ፊት እንዲበራ ነው። ዓለም ከእኛ ከአማኞች ብዙ ይጠብቃል። ይሁን እንጂ፥ ብዙ ጊዜ በእኛ ሕይወት ውስጥ የሚያየው በዓለም ውስጥ ካለው የተለየ ባለመሆኑ በጣም ያሳዝናል። እውነትን ስንናገር፥ በእውነት ውስጥ ስንመላለስ ካልታየን፥ ለማያምኑት እንቅፋት እንሆናለን።

# ምዕራፍ ፲

# ትዕቢተኛ ምላስ

*"ሌሎች ያመስግኑህ እንጂ፥ ራስህን አታመስግን፥*
*ሰዎች ስለ አንተ ይመስክሩ እንጂ፥*
*አንተ ስለ ራስህ መልካምነት አትናገር።"*
(ምሳሌ 27፥2)

ሁላችንም "እኔ" የሚል ተፈጥሯዊ ባህሪ አለን። መታወቅ፥ መፈለግ፥ ከሌሎች ሁሉ በልጠን መታየት እንፈልጋለን። የምንሮጠው፥ የምንታገለው፥ የምንሠራው፥ እኛነታችንን ለመንከባከብና ለማሳደግ ነው። እኛን የሚያንቀሳቅሰን ኃይለኛ ሞተር ያ ነው። ይህን እውነት በልባችን ውስጥ ሰውረን መያዝ ብቻ ሳይሆን፥ በአፋችንም ይህንኑ ገልጸን የምንናገርበት ጊዜ እንዳለ የታወቀ ነው።

## 1. "እኔ" ባይነት በሁላችንም ላይ ይታያል

*"እኔ ባይነት"* ሲይዝ ማንንም አይመርጥም። በወንድም ሆነ በሴት ላይ የሚታይ ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው። ሁላችንም ዘንድ አለ። ያለ እርሱ መሥራትና መንቀሳቀስ አንችልም። ለራሳችን ያለን ስሜት፥ ለራሳችን ያለን አመለካከት ወሳኙ፥ ያለን *"የእኔ ባይነት"* ባሕሪ መጠን ነው። በክርስትያኖች ሕይወት ውስጥ መካከለኛውን



ሥፍራ ይዞ ሙሉ በሙሉ ሊቆጣጠር የሚገባው መንፈስ ቅዱስ መሆን እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ኤፌ. 5፥ 18)። *"እኛነታችን"* ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ሲውል፥ ሕይወታችን ውጤታማ ይሆናል። እግዚአብሔር በሕይወታችን መካከለኛውን ሥፍራ ሲይዝ፥ መንፈሳዊ ድል፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትና እንዲሁም ሌሎችን የማገልገል ጥማትና ፍላጎት ይኖረናል። በራሳችን ፍቅር ስንሞላ፥ *"እኛነታችን"* እግዚአብሔር ብቻ ሊይዘው የሚገባውን ሥፍራ ሲይዝ፥ ወይም ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ውጪ ሲሆን ደግሞ፥ ብዙ ችግሮች ውስጥ እንገባለን። ችግር ውስጥም የሚከተን ዋናውና ትልቁ ምክንያት ምላሳችን ነው። ይህንን የተገነዘበው ዘማሪ፥ *"እግዚአብሔር ሆይ! እነዚያን የሚያቀላምጡ ምላሶች ጸጥ አድርጋቸው፥ ትዕቢት የሚናገሩትንም አፎች ዝጋ። ምክንያቱም እነርሱ በመናገራችን የፈለግነውን እናገኛለን፥ እንደ ፈቀድን እንናገራለን፥ ከእኛ በላይ ሆኖ ሊከለክለን የሚችል ማን ነው? ይላሉ"* (መዝ. 12፥3-4) በማለት ይጸልያል።

አንዳንዶቻችን በምላሳችን የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ገናናነት ልናውጅ ሲገባን፥ ስለ ራሳችን ማንነት ከሆንነው በላይ አተልቀንና አጋንነን የማውራት ዝንባሌ ይታይብናል። "በትዕቢት መናገር" (bragging) ራስን መሸንገል ወይም መዋሸት ነው። አንዳንዶቻችን ስለራሳችን ያስተላለፍነው መልዕክት ተጋንኖ የተወራ መሆኑ በሌሎች ዘንድ ይታወቅ ይሆናል የሚል ፍርሃት የለብንም። *"ሌሎች ያመስግኑህ እንጂ፥ ራስህን አታመስግን፥ ሰዎች ስለ አንተ ይመስክሩ እንጂ፥ አንተ ስለ ራስህ መልካምነት አትናገር"* (ምሳሌ 27፥2) የሚለውን ቃል በተግባር ላይ አናውለውም። ሌሎችን ለመማረክ ወይም ስለ እኛ ያላቸው ግምትም ሆነ አስተያየት ከፍ እንዲል፥ ጥሩ የሆነውን ጎናችንን ከሚገባው በላይ አተልቀን፥ ድካማችንን ግን ፍጹም አሳንሰን፥ ወይም ምንም ዓይነት ድካም እንደሌለብን አድርገን ለማሳየት እንሞክራለን። ሌላው ቀርቶ ስለ ራሳችን "ብንሆን" ብለን የምንመኘውንም ገና ሳንሆን፥ "ነን" ብለን እናወራለን። አጋንኖና አተልቆ የማውራት ልማድ ያለው ሰው፥ ለማግኘት የሚመኘውን ነገር፥ ገና ሳያገኝ ልክ እንዳገኘ አድርጎ ያወራል። ለምሳሌ ትምህርት ቤት ሳይገባ፥ ያገኛቸውን የዲግሪ ዓይነቶቹን ዝርዝር መመለጫ ይሰጣል። ንግድ ገና ሳይጀምር፥ ነግዶ ያተረፈውን የገን

ዘብ መጠን ያወራል። ስለ ራሱ ብዙ የሚያወራ፥ ትዕቢተኛ ምላስ
ያለው ሰው "ሆንልኝ" የሚለውን ነገር ከሆነለት የበለጠ አሳድጎና
አተልቆ ለማሳየት ይሞክራል።

## 2. ራስን አተልቆ የሚያወራ ምላስ

አንዳንድ ሰው *"ራስን ከፍ አድርጎ መውራትን"* እንደ መዝናኛ
ወይም እንደ ጊዜ ማሳለፊያ አድርጎ የሚጠቀምበት ይመስላል።
እንዲህ ዓይነቱ ሰው ከልቡ እየተናገረ፥ የሚቀልድ ይመስላል። አንድ
ጊዜ አንዲት ስለራሷ ትልቅነት ብዙ ማውራት የምትወድ ወጣት፥
እጮኛዋና እርሷ ስላሳለፉት ጥሩ ጊዜ ለጓደኛዋ ስታወራላት እንዲህ
አለች። *"እጮኛዬ ፓይለት እንደሆነ ታውቂያለሽ። አንድ ቀን በአ
ይይሮፕላን ሊያንሸራሽረኝ ፈልጎ ጥዋት ከቦሌ ተነስተን እየበረ
ርን ሰበታ አረፍን"* አለቻት። የምታዳምጣት ጓደኛዋም *"እንዴ!
...'አንቺ ሰበታ አይሮፕላን ማረፊያ አለ እንዴ?"* አለቻት።
ልጅቷም፥ *"ሰበታ አልኩ፥ ወልቂጤ ማለቴ ነው"* አለቻት። አሁንም
ጓደኛዋ *"አንቺ! አሁንስ አበዛሽው! ...ወልቂጤ ደግሞ አይሮፕላን
ማረፊያ አለ እንዴ?"* አለቻት። መልሳ አሁንም *"ሆለታ ማለቴ
ነው"* አለቻት። በዚህ ዓይነት ብዙ ከተማዎች ስትጠራ ቆየች።
በመጨረሻም ጓደኛዋ *"...ዛሬ አታርፊያት..."* አለቻት ይባላል።
ታሪኩ ተረት ይሁን እንጂ፥ ከሆነው በላይ ነገርን አተልቀው የሚያ
ሳዩትን፥ እንዲሁም ያልሆነውን "ሆነ" ብለው ስለራሳቸው የሚያወሩ
ትን ሰዎች ጥሩ አድርጎ ያሳያል። ስለ ራሳቸው ብዙ ማውራት
የሚወዱ ሰዎች ሰሚ ካገኙ ሁልጊዜ እነርሱን በሚመለከት ነጥብ
ላይ ብቻ፥ ይኸውም ስለሆኑት፥ ስለሆነላቸውና እንዲሁም ስላደረጉት
ነገር ሃያ አራት ሰዓት ቢያወሩ ደስ እንደሚላቸው የታወቀ ነው።
ሰው የእነርሱን ታሪክ መስማት ይሰለቸዋል ብለው አያስቡም።
ራሳቸውን ካላሞጋገሱ፥ ሌላ የሚያሞጋግሳቸው፥ ራሳቸውን ካላደነቁ
ሌላ የሚያደንቃቸው ሰው፥ እንዲሁም ራሳቸውን ካልወደዱ ሌላ
የሚወዳቸው ሰው የሚያገኙ አይመስላቸውም። እንዲያውም አንዳ
ንዶቹ ራሳቸውን በመስታወት እያዩ፥ ስማቸውን እያቆላመጡ በመ
ጥራት "...እንትንዬ! የእኔ ጌታ..." እያሉ እጃቸውን ሳም የሚያደር
ጉም እንደማይጠፉ እንገምታለን። እንደነዚህ ዓይነቶቹ በራሳቸው



ፍቅር ፍጹም የሰከሩ ስለሆኑ "ራስን ማቆላመጥ" በሕብረተሰብ ውስጥ
ተወዳጅነት ወይም ተቀባይነት የማያሰጣቸው መሆኑን አያስተው
ሉም። በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ ስለ ራስ ማውራት፥ እንኳን ያልሆነ
ውን የሆነውንም አጋንኖ ማውራት ትዝብት ያተርፋል እንጂ ተወ
ዳጅ አያደርግም።

በስፖርት ዓለም ውስጥ "የራስን ኃያልነት" እያጋነኑ ማውራት
የተለመደ ነው። ተወዳዳሪያቸውን ለማስደንገጥ ይመስላል፥ ያላቸ
ውን ጉልበት፥ ያደረጉትን ትልቅ ዝግጅት ወይም ልምምድ አተል
ቀውና አሳድገው ያወራሉ። ይህንንም የሚያደርጉት ራሳቸውን
ማተለቃቸው እንዳይታወቅባቸው ረቂቅ የሆነ ዘዴ በመጠቀም ሳይ
ሆን በግልጽ ነው። "የራሱን ኃያልነትና ታላቅነት" በመናገር" በጣም
የታወቀው ጥቁር አሜሪካዊው ሞሐመድ ዓሊ (ካሲየስ ክሌይ) ነው።
ሞሐመድ ዓሊ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሲሰጥ ብዙ ጊዜ *"በዓለም ተወ
ዳዳሪ የሌለኝ! ታላቁ በከሰኛ! የዓለም ቻምፒዮን እኔ ነኝ! ማንም
እንደ እኔ የለም!... እኔ መልከ መልካም ነኝ..."* ይል ነበር። እውነት
እንኳን ቢሆን፥ ስለራሳቸው ትልቅነት የሚያውጁ ሰዎች፥ በአካባቢ
ያቸው ተወዳጅነትን ያተረፉ እንዳልሆኑ እናውቃለን። ትዕቢት
የሚናገሩትን አፎች የሚጠላው ሰው ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔርም
እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ሥፍራ ተጠቅሷል። ለመሆኑ
ይህን ዓይነቱ ጠባይ በአማኞች ሕይወት ውስጥ ይታይ ይሆን?
ይህንን ገሰፌው እንመለከታለን።

## 3. እግዚአብሔር ትዕቢተኛ ምላስን ይጠላል

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በትዕቢት ንግግሩ በጣም የታወቀው
ሰው ማን ነው? ተብለን ብንጠየቅ ወደ አዕምሯችን ቶሎ የሚመጣው
ሰው ጎልያድ እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ። ፍልስጤማውያን እስራኤ
ልን ለመውጋት በተሰለፉበት አንድ ወቅት፥ ፍልስጤማዊው ጎልያድ
በእስራኤል ሠራዊት ፊት እንዲህ እያለ ይደነፋ ነበር *"አሁን በዚያ
ቦታ ለጦርነት የተሰለፋችሁት ከቶ ምን ልታደርጉ ነው? እኔ ፍልስ
ጥኤማዊ ነኝ! እናንተ ደግሞ የሳኦል ባሪያዎች ናችሁ! እንግዲህ
ከእኔ ጋር የሚዋጋ አንድ ሰው ከወታደሮቻችሁ መካከል ምረጡ፥
እርሱ እኔን አሸንፎ ከገደለኝ እኛ የእናንተ ባሪያዎች እንሆናለን፥*

*ይጠቅማል። በመንፈሳዊ ሕይወትም ዕድገታችንን አያሳይም። ዲ. ኤል ሙዲ "አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ብዙ ርቆ እንደሄደ ማወቅ የሚቻለው ስለ ራሱና እንዲሁም ስለ ጥሩነቱ ብዙ የተናገረ እንደ ሆነ ነው"* አለ።

ስለራሳቸው ብዙ የሚያወሩ ሳይሳካላቸው 'ተሳካልን"፣ ሳይኖራቸው "አለን"፣ ሳያገኙ "አገኘን"፣ ሳይማሩ "ተማርን" የሚሉት ብቻ አይደሉም። ያላቸውና የሆነላቸውም አንዳንዶች ስለራሳቸው ብዙ ያወራሉ። እዚህ ላይ ማወቅ ያለብን እውነት ቢኖር፣ ያገኘነውንና የሆነልንን ለወዳጆቻችን፣ ዕድገታችንን ለሚመኙና በዕድገታችን ደስ ለሚላቸው ሰዎች አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ብቻ ብንናገር፣ ጉረኞች እንደማያሰኙን የታወቀ ነው። "እራስን ማሞካሸትና" እውነቱን አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ስለ ራሳችን ማውራት፣ በሁለቱ መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። ይኸውም፣ ያገኘነውንና የሆንልንን በአግባቡ መግለጽ ዓላማው፣ ወዳጆቻችንን ትክክለኛውን ነገር ለማሳወቅ ብቻ ሲሆን፣ የጉራ ንግግር ግን ዓላማው ሰዎች እንዲያደንቁን ለማድረግ ነው። የጉራ ንግግር ራስን ከሌሎች ማስበለጥንና ፉክክርን ስለሚያመጣ፣ ሕብረተሰቡን ይከፋፍላል እንጂ አንድ አያደርግም። ትክክለኛ መንፈስ ኖሮት የሚያወራ ሰው፣ የራሱን ዜና ወይም የሆነለትን ላላ ወቀው ማካፈል፣ ወይም መናገር ብቻ ሳይሆን፣ የሌላውንም ሰው ዜና ያዳምጣል፣ ለራሱ መደነቅን ብቻ የሚፈልግ ሳይሆን፣ ሌላውንም ያደንቃል። ስለራሱ ስሜት ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ሰው ስሜት ይጠብቃል። ሌላው የተጎዳ ሲመስለው የርህራሄ ስሜቱን ይገልጻል። በትዕቢት የሚናገር ሰው ግን ንግግሩ በራሱ ላይ ያተኮረ፣ ስለሌላው ሰው ስሜት ፈጽሞ ግድ የሌለው፣ ሁልጊዜ የሚደነቅበትን መንገድ ብቻ የሚፈልግ ነው።

"ትዕቢተኛ ምላስ" ሰዎችን ወደ ራስ ከመሳብ ይልቅ፣ ሰውን ያሸሻል። ተጠይ ያደርጋል እንጂ፣ ተወዳጅ አያደርግም። "ያ ጉራ መንዛት የሚወደው ሰው መጣ" በመባል ይናቃል እንጂ፣ አይከበርም። ጥሩ ውይይት ወይም ጨዋታ የሚባለው፣ ውይይቱ በአንድ ግለሰብ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በሌሎች ሰዎችም ፍላጎት ላይ ያተኮረ እንደሆነ ብቻ ነው። "ትዕቢተኛ ምላስ" ያላቸው ሰዎች ከማን ጋር እንደዋሉ፣ ጓደኞቻቸው እነማን እንደሆኑ፣ ዘመዶቻቸው እነማን



እንደሆኑ መናገር ደስ ይላቸዋል። ያለፉበትን፣ ያደጉበትን የድህነት ኑሯቸውን ደብቀው፣ የጠገቡ ሀብታሞች እንደነበሩ፣ ተንቀባረው እንዳደጉ፣ "ይህን ሳወራ የሚታዘበኝ ሰው ይኖራል" ብለው ሳይፈሩ በድፍረት ያወራሉ። "ድህነት" የሚያሳፍር በሽታ ይመስላቸዋል። የሚያሳፍረው ድህነት ሳይሆን፣ ሳይሠሩ እጅን አጣምሮ ተቀምጠ "የእከሌ ልጅ ነኝ!" ማለቱ ነው። ብዙ ጊዜ በምስክርነቴ ጌታን የተቀበልኩት የተቀደደ ቁምጣ ለብሼ እንደሆነ እገልጻለሁ። እንዲህ ለማለት በበኩሌ ፈጽሞ አያሳፍረኝም። ብዙ ሀብት ቢኖረኝ፣ ከቤተሰቤ የወረስኩት ነው ከማለት፣ "ለፍቼ ያገኘሁት" ወይም "ጌታ የሰጠኝ ነው" ማለቱ የበለጠ ያኮራኝ ነበር። ጃንሆይ ከዙፋን ከመውረዳቸው በፊት፣ ትልቅነታቸውን ለማሳየት፣ ከጃንሆይ የዘር ግንድ የወጡ ለመሆናቸው፣ ዘር የሚቆጥሩ ብዙ ሰዎች አጋጥመውኛል። እነርሱ ሆነው ባገኙት ደስ ሊላቸው ሲገባ፣ በሌላው ታዋቂነት ራሳቸውን ለማተለቅ የሚሞክሩ ሰዎች አሉ። ይኼም ከንቱ ነው።

"የትዕቢት ንግግር"፣ እግዚአብሔር በሕይወታችን ጎልቶ እንዲታይ ከሚፈልገው "ከትህትና መንፈስ" በጣም የራቀ ነው። የእግዚአብሔር መመዘኛ፣ ከሰው መመዘኛ በጣም የተለየ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። በእግዚአብሔር ሚዛን ትልቅ ለመሆን፣ ዝቅ ማለትን ይጠይቃል። *"...ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላል፣ ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ይላል"* (የሉቃ. 18፥14)። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አማኞች አንዳንዶቹ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያልበሰሉ በመሆናቸው፣ *ሥጋዊ* የሆነ ባሕሪ ይታይባቸው ነበር። *"...አንዱ እኔ የጳውሎስ ነኝ፣ ሌላው ደግሞ እኔ የአጵሎስ ነኝ..."* (1 ቆሮ. 3፥1-4) እያሉ የትዕቢት ቃል ይናገሩ ነበር። በእግዚአብሔር ጸጋ መዳናቸውን የሚያውቁ ክርስቲያኖች ለምንም ዓይነት ትዕቢት ራሳቸውን መስጠት የለባቸውም። ምክንያቱም ከጌታ ውጪ ማናችንም ብንሆን ዋጋ የሌለን በመሆናችን ነው። "ራሱን የሚያቆላምጥ" ሰው፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያለበትን አቋም ያሳያል። ከሌሎች የተሻልን ሆነን ለመታየት፣ በሌሎች ዘንድ የተደነቅን ለመሆን ውስጣዊ ረሀብ ይታይብን ይሆን? ከውስጣችን ራሳችንን የማተለቅ ከፍተኛ ጥማት ካለን፣ ዕድሉ ባጋጠመን ቁጥር፣ ወይም መንገድ ፈልገን ስለራሳችን ታላቅነት ትንሽም ሳይሰቀጥጠን እናወራለን። ጉራ መንዛት ወይም ትዕቢት፣ "አጣነው"፣ ወይም "አላገኘነውም" የምንለውን

ቀዳዳ የሚደፍንልን ይመስለናል። ባዶነት በሚሰማን ሥፍራ ላይ ጌታ የራሱ የሆነውን ነገር ሲሞላበት፥ ትዕቢትና ጉራ መንዛት በሕይወታችን አይታይም። በእግዚአብሔር ውስጥ ማንነታችንን፥ በእርሱ ዘንድ ከፍተኛ ዋጋ እንዳለንና እንዲሁም እርሱ ባዘጋጀልን ቤት ለዘላለም የሚኖረንን ሥፍራ እናውቃለን። ጳውሎስ የሚመካበት ወይም የሚኮራበት ምክንያት ምን እንደሆነ ሲገልጽ፥ *"እኔ ግን ዓለም ለእኔ ከሞተበት፥ እኔም ለዓለም ከሞትሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ የምመካበት ነገር የለኝም"* ይላል (ገላት. 6፥14)።

ስለራሳችን በማውራት ፋንታ ስለ ክርስቶስ በትክክለኛው መንገድ ጉራ ብንነዛ፥ ወንጌልን መስበካችን ነው። እኛ ስላገኘነው፥ ስለ ሆነልን ለሌሎች ከማውራት ይልቅ ስለ አዳኙ ኢየሱስ ታላቅነትና ሕይወት ሰጪነት ለሚሰማን ሁሉ ማውራት ሥጋዊነት የለበትም። የክርስቶስ ተከታዮች ሆነን ምን ዓይነት ባሕሪ ሊኖረን እንደሚገባ ጳውሎስ ሲመክረን፥ *"በትሕትና ተሞልታችሁ፥ ሌሎች ሰዎች ከእናንተ እንደሚሻሉ አድርጋችሁ ቁጠሩ እንጂ ወገን በመለየትና በራስ ወዳድነት ወይም ያለ እኔ ማን አለ በሚል ትምክሕት ምንም ነገር አታድርጉ። እንዲሁም እያንዳንዱ የራሱን ጥቅም ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ሰው ጥቅም ያስብ። በዚህ ዐይነት ኢየሱስ ክርስቶስ ያሳየው የትሕትና ጠባይ በእናንተም ሕይወት ሊኖር ይገባል"* ይለናል (ፊልጵ. 2፥3-5)። ስለራስ አጋኖ ማውራት እንኳን በመንፈሳዊው ዓለም፥ በሥጋዊውም ዓለም በጣም የተጠላ ነው። ስለዚህም ብዙ ፈላስፋዎችና ጸሀፊዎች ጽፈዋል፥

- ➡ *አርስቶትል... "ጉራ መንዛት፥ ከማንኛውም ውሸት በጣም የከፋ ነው"* አለ።
- ➡ *ሌላው ጸሀፊ-- "ከውሸት ሁሉ አሳፋሪው በምላሳችን የምንናገረው ውሸት ሳይሆን፥ የምንኖረው የውሸት ኑሮ ነው" አለ።*
- ➡ *ፕሉተርክ... "ሁሉን ማድረግ አለመቻል ነውር የለበትም፥ ማድረግ የማንችለውን እንደምንችል አድርገን ማስመሰል ግን አስነዋሪና አሳፋሪ መሆን ብቻ ሳይሆን፥ ችግርና አዘቅትም ውስጥ ይከታል።"*



- ➡ *ሠለሞን... "ሀብታም መስሎ በችግር ከሚኖር ሰው ይልቅ፥ ተራ ሰው መስሎ እየሠራ ኑሮውን የሚያሸንፍ ይሻላል" (ምሳሌ 12፥9)።*

ጉራ መንዛት የከፋ የሚሆንበት ትልቁ ምክንያት፥ የምንዋሸው ሌሎችን ብቻ ሳይሆን ራሳችንንም ጭምር በመሆኑ ነው። ክርስቲያኖች ሆነን ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን መዋሸት አይገባንም። በራሳችን ከምንመካ ይልቅ ትምክህታችንን በክርስቶስ ላይ ብቻ እናድርግ። በእርሱ ከተመካን ምንጊዜም አናፍርም።

# 4. ስለራሳችን ብዙ ማውራት...

## 4.1. *ባዶነታችንን ማክበራችን ነው*

ጳውሎስ *"...በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ..."* ሲል ይመክረናል (ፊልጵ. 2፥3)። *"ከንቱ ውዳሴ"* የሚለው ቃል፥ ከሁለት የግሪክ ቃል የወጣ ሲሆን፥ ትርጉሙም *"ባዶ ክብር"* ማለት ነው። ጳውሎስ *"ከንቱ"* ሲል፥ ባዶ ለሆነ ነገር ክብር መስጠት ማለቱ ነው። ስለዚህ *"ጉራ ስንነዛ"* ባዶ የሆነውን *"እኛነታችንን"* አተልቀን ማሳየታችን ነው። ጳውሎስ ስለ ራሱ ሲገልጽ *"በእኔ ወይም በእኔ ሥጋዊ ባሕርይ ምንም መልካም ነገር እንደሌለ አውቃለሁ..."* ይላል (ሮሜ 7፥18)። ኢሳያስም ስለ ሰው ቅድስና ሲናገር *"... ጽድቃችንም እንደ መርገም ጨርቅ ሆናአል..."* ይላል (ኢሳ. 64፥6)። ኢየሱስም በራሳችን ምንም ኃይል እንደሌለን ሲገልጽ፥ *"...ያለ እኔ ምንም ማድረግ አትችሉም..."* ይላል (የዮሐ. 15፥5)። ስለዚህ ራሳችንን ከፍ ከፍ ስናደርግ፥ ባዶነታችንን ማክበራችን ይሆናል። እንደምናውቀው 'ባዶ ዕቃ ብዙ ድምፅ ያሰማል።' ይህም ማለት በራሱ ምንም የሌለው ሰው፥ ስለራሱ ብዙ ያወራል ማለት ነው። *ጆሴፍ ስቶል "ዜሮ (0) ምንም ያህል ትልቅ አድርገን ብንጽፈው፥ ያው ዜሮ (0) ነው"* አለ። ስለራሳችን ጉራ ስንነዛ፥ ዜሮነታችንን ትልቅ ማድረጋችን ወይም ማክበራችን ነው። ይሄም "ከንቱ ውዳሴ" ነው። ሕይወታችን፥ "ሠራን" የምንላቸው ሥራዎቻችን፥ በጠቅላላው የሆንነው ሁሉ ትርጉም ሊኖረው የሚችለው በክርስቶስ

ውስጥ ብቻ ነው። ጳውሎስ *"እኔ ከክርስቶስ ጋር እንደተሰቀልሁ ያህል ስለምቆጥር ከእንግዲህ ወዲህ ክርስቶስ በእኔ ይኖራል እንጂ እኔ ለራሴ ሕይወት የምኖር አይደለሁም..."* ይላል (ገላት. 2፥20)። ይህን ሲል *"በእኔ ውስጥ ምናልባት አንድ በጎ የሆነ ነገር ቢደረግ፥ ያ የክርስቶስ ሥራ እንጂ የእኔ አይደለም"* ማለቱ ነው።

## 4.2. ትምክህተኞች መሆናችን ነው

ትምክህተኞች፥ ምንም ሳይኖራቸው ብዙ እንዳላቸው አድርገው ይናገራሉ። የሠሩትን፥ ያደረጉትን፥ ያገኙትን ከሆነው በላይ አሳም ረውና አተልቀው ያወራሉ። አንድ ጊዜ የሆቴል ንግድ የነበረው ሰው፥ ከሚያቀርባቸው የምግብ ዓይነቶች መካከል አንደኛው በእንቁራሪት ሥጋ የተዘጋጀ ምግብ ነበር። የዚህ ሰው ትልቁ ችግር እንቁራሪት የሚያቀርብለት ሰው ማጣቱ ነው። ይህንን ችግሩን ሲያወራ የሰማው አንድ ሰው፥ "እኔ ከሺ በላይ አቀርብልሃለሁ" አለው። "በአንድ ጊዜ ያን ያህልም ባይሆን፥ ለመጀመሪያ ጊዜ እስቲ ጥቂቱን አቅርብልኝ" አለው። በማግሥቱ "ሺ እንቁራሪት አቀርባለሁ" ያለው ሰው አንዲት እንቁራሪት ብቻ አንጠልጥሎ ይዞለት መጣ። ባለሆቴሉም በመደነቅ፥ "ምነው አንድ ብቻ ይዘህ መጣህ? ሺ እንቁራሪት ማቅረብ እችላለሁ ብለኸኝ አልነበረም እንዴ?" ብሎ ጠየቀው። ሰውየውም ሲመልስ፥ "እቤቴ አጠገብ ትንሽ የውሃ ጉድጓድ አለ። እዚያ ጉድጓድ ውስጥ ማታ ማታ የእንቁራሪት ጩኸት አላስተኛም ይለኛል። እኔ ድምጹን ስሰማ ሺ እንቁራሪት የሚጮኸ መስሎኝ ነበር። ለካስ ያን ሁሉ ጩኸት የምታሰማው ይህቺው አንዷ እንቁራሪት ነች!" አለው። ትምክህተኛ ሰው ብዙ ድምጽ ያሰማል። አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ሁከት የሚፈጥሩ፥ የምዕመናኑን አንድነትና ሰላም የሚነሱ ብዙዎች መስለውን ተስፋ እንቈረጥ። ጥቂት እንቁራሪቶች መሆናቸውን አንርሳ። ብዙ ስለሚጮኹ፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ሁሉም የሚያጉረመርም፥ ሁሉም ሰላምና አንድነት የሚነሳ ይመስለናል እንጂ፥ አይደለም።

ጉረኛ የሆኑ ሰዎች ስለ ብዙ ነገር ጉራ ይነዛሉ፥ ሊያደርጉ የማይችሉትን ተስፋ ይሰጣሉ። *"ነገ ሂጄ ይህንና ያንን አደርጋለሁ።... ከተቸገርክ እኔ ብዙ ገንዘብ አለኝና ላበድርህ እችላለሁ... የማልጠቀምበት ብዙ ዕቃ አለኝና የምትፈልገውን እሰጥሃለሁ..."* ይላሉ። ይሁን እንጂ፥ ከተናገሩት ነገር አንዱንም መፈጸም ስለማይችሉ፥ ተስፋ ከገቡለት ሰው ጋር ይጋጫሉ። አንድ በቅርብ የማውቀው አንድ ሰው ለትምህርት ውጪ አገር ሊሄድ ሲዘጋጅ፥ ፎቴውን ቢያንስ ቢያንስ ለአሥር ሰው "እሸጥላችኋል..." በማለት ቃል ገብቶላቸው ነበር። ገዢዎቹ አሥር ይሁኑ እንጂ፥ ፎቴው ያው አንድ ብቻ ስለሆነ መጨረሻ ላይ ከብዙዎቹ ጋር ተጋጨ። ጉረኛ የሆኑ ሰዎች ማድረግ የሚችሉትንና የማይችሉትን ለይተው የሚያውቁ አይመስሉም። ያዕቆብ ሲመክረን፥ *"...ይልቁንስ እናንተ ማለት የሚገባችሁ እግዚአብሔር ቢፈቅድና ብንኖር ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ነው። እናንተ ግን ይህን በማለት ፈንታ በትዕቢታችሁ ትመካላችሁ፥ እንዲህ ያለው ትምክህት ሁሉ ክፉ ነው"* ይላል (ያዕ. 4፥16)። በሕይወታችን የምናገኛቸው ድሎች በራሳችን ችሎታ ወይም ጉልበት የተገኙ ሳይሆኑ፥ ከእግዚአብሔር እንደሆነ መርሳት የለብንም። ድሎችን ከራሳችን እንዳገኘናቸው አድርገን ማውራት፥ የእግዚአብሔርን ክብር መንጠቅ ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ያዕቆብ *"ትምክህት ሁሉ ክፉ ነው"* (ያዕ. 4፥16) ያለው።

## 4.3. የእግዚአብሔርን ክብር መስረቃችን ነው

ክራስ ወዳድነት ውስጥ በጣም የሚከፋው፥ የሌላውን ምስጋና ነጥቆ ለራስ ማድረግ ነው። ክብር ለሚገባው ክብር መስጠት ተገቢ ነው። እግዚአብሔር ክብሩ በዓለም ዙሪያ እንዲታይ የወሰነ ስለሆነ፥ ለእኛ ያለው ዓላማም፥ የራሳችንን ሳይሆን የእርሱን ክብር እንድናንጸባርቅ ነው። በሁኔታችንና በምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ የእርሱን ክብር እንድናሳይ ይጠበቅብናል። ጳውሎስ የቆሮንቶስ አማኞችን *"ሰውነታችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁትና በውስጣችሁም የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ መሆኑን ታውቁ የለምን? እንግዲህ እናንተ የእግዚአብሔር ናችሁ እንጂ የራሳችሁ አይደላችሁም"* ይላቸዋል (1 ቆሮ. 6፥19)። ብዙዎቻችን ሙሴ ወደ ተስፋይቱ ምድር ያልገባበት ምክንያት ይቆረቁረናል። "ትክክል አይደለም" ለማለትም ይቃጣናል። "አንድ ትንሽ ስህተት በመሥራቱ እንዴት ይህን ዓይነት ከፍተኛ ቅጣት ይሰጠዋል?" በማለት ቅሬታችንን የገ

በብዙ ሰው ንግግር ውስጥ የሚታይ ነው። ድካማችንን እንኳን አልፎ አልፎ አንዳንዶቻችን እንደ ጀብዱ አድርገን የምናወራበት ጊዜ አለ። በሥጋም፥ በመንፈሳዊ ሕይወታችንም ልጆች በነበርንበት አንድ ዘመን፥ አንድ ሰው ቤተ ክርስቲያናችን መጥቶ *"እባካችሁን እንዲት በአጋንንት የተያዘች ሴት አለችና ኑና ጸልዩላት"* ብሎን እኔና ሁለት ወንድሞችን ይዞን ሄደ። እኛም ኃይሉና ጉልበቱ በእኛ ውስጥ ያለ ይመስል ሰይጣንን "ድራሽህን ልናጠፋ መጣንልህ! ዋ!" እያልን እየፎከርን ሄድን። ዘመዶቿ በአጋንንት የተያዘችውንና እኛን ቤቱ ውስጥ ትተውን ወጡ። የሚሆነውን ከውጪ በመስኮት ይመለከቱ ነበር። ምንም እንኳን ስንገስጽ በጣም እየጮኽን "በኢየሱስ ስም" እንበል እንጂ፥ ውስጣችን ያለው ያ አልነበረም። በውስጣችን የራስ የሆነ ከፍተኛ ትምክህት ስለነበረብን፥ አጋንንቱን ለማስወጣት የሞከርነው በራሳችን ኃይል ስለነበረ፥ ጸሎታችን ምንም ኃይል አልነበረውም። አጋንንቱን ሊያስወጣው ቀርቶ፥ ትንሽም ሊያስደነግጠው አልቻለም። እንዲያውም አጋንንቱ ረግጦ፥ ልብሳችንን ቡጭቅጭቁን አውጥቶ ለቀቀን። ምንም ማድረግ እንደማንችል መጨረሻው ላይ ስንረዳ ከሁኔታው ለመሸሽ አንድ ዘዴ ፈጠርን፥ ከየት እንዳገኘነው አላውቅም "ለምን አስረነው አንሄድም!" ብለን "በኢየሱስ ስም የታሠርክ ሁን" ብለን ወጣን። ምን ማለታችን እንደሆን ግን አልገባኝም። "የታሰርክ ሁን" ስንል፥ "ሌላ ቦታ እንዳት ሄድ፥ ሰውየው ውስጥ እንድትቆይ" ማለታችን እንደሆን በጊዜው አልገባኝም።

በዚያን ወቅት የእኛን ውጤት ለመስማት ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ይጠብቁናል። ከእኛ መካከል አንዱ "ተሸን ፈን፥ ተዋርደን፥ በአጋንንት ተደብድበን" መጣን በማለት ፋንታ፥ በድል አድራጊነት እንደተመለስን ማወጅ ጀመረ። የአጋንንቱን ኃይለኛነት ከገለጸ በኋላ፥ "አስወጣነው" በማለት ፈንታ፥ "በየሱስ ስም የታሠርክ ሁን ብለን አሥረነው መጣን" አላቸው። ያኔ እንዳሁኑ ዘመን ማጨብጨብ ቢኖር ኖሮ ትልቅ ጭብጨባ እንደምናገኝ እርግጠኛ ነኝ። ደግነቱ ያኔ ነገሩ ካልመሰለው፥ ሌላው ስላጨበጨበ ብቻ ሌላው የሚያጨበጭብ አልነበረም። እንዲያውም አንዱ የማንረሳውን በጣም ጥሩ ትምህርት ሰጠን። "ኢየሱስ በምድራዊ



አገልግሎቱ ወንጌልን ሲሰብክ በሽተኞች ሲመጡ ይፈውስ፥ በአጋንንት የተያዙትን ነጻ ያወጣ ነበር እንጂ፥ እየዞረ አጋንንት አያድንም ነበር። አሁን እናንተ የያዛችሁት አጋንንት ማደን ይመስላል" አለን። እውነቱን ነበር። ያ ሁኔታ ጥሩ ትምህርት ሰጠን። ይህን ምሳሌ ያመጣሁት አንዳንዶቻችን ስናጋንን፥ ሽንፈታችንን እንኳን እንደ ገድል የምናወራ መሆናችንን ለመግለጽ ነው።

አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸው ሲያናድዷቸው "ሁለተኛ ይህን ብታደርግ አንስቼ ነው የማፈርጥህ!... ከግድግዳ ጋር ነው የማጋጭህ..." ይላሉ። ለመሆኑ ያሉትን ያደርጉታል? ማጋነን በመጠቀም የሚያደርጉት እጅ ጥምዘዛ (manipulation) ነው። ናቡከደናጾር ሲድራቅ፥ ሚሳቅና አብደናጎን ለማስፈራራት ተጠቅሞበታል። *"...እጅግ ተቆጥቶ እሳቱ ከቀድሞው ይበልጥ በሰባት እጥፍ ከፍ ብሎ እንዲነድድ ትእዛዝ ሰጠ"* ይላል (ዳንኤል 3፥19)። መጀመሪያ ላይ የነበረው እሳት እነዚያን ሦስት ሰዎች ለማቃጠል በቂ ኃይል ነበረው። ይሁን እንጂ፥ ትንሽም ቢሆን አላስደነገጣቸውም ነበር። ሰዎች በእኛ ላይ እምነታቸው እንዲጨምር፥ እኛም ስለራሳችን ያለን ግምት ከፍ እንዲል፥ አጋንነን የምናወራበት ጊዜ አለ። እውነት ሁልጊዜ "እውነት" ነው። እኛ ስበን ልናሳድገው አንችልም። ማጋነናችን ሲበዛና፥ ሰዎችም በዚህ ባሕሪያችን እያወቁን ሲመጡ፥ በእኛ ላይ ያላቸው እምነት እየቀነሰ ወይም እየጠፋ ይመጣል። ይህም ከሰው ጋር የሚኖረንን ግንኙነት ያበላሽብናል። ያ ብቻ አይደለም፥ እግዚአብሔርም ያልሆነውን "ሆነ" ብለን ማውራታችንን ስለሚጠላ፥ ከእርሱ ጋር ያለንንም ግንኙነት ያበላሽብናል። ጸሎታችን እንደ ዘማሪው፥ *"እግዚአብሔር ሆይ! አንተ መጠጊያዬና ቤዛዬ ነህ፥ ንግግሬም ሆነ አሳቤ፥ በአንተ ዘንድ ይወደድ"* የሚል ይሁን (መዝ. 19፥14)።

ንግግራችንን ከሚመርዙት ነገሮች መካከል አንደኛው ጉራ መንዛት ነው። አንዳንዶቻችን በግልጽ ስናደርገው፥ ሌሎቻችን ደግሞ ጉራ መንዛታችን እንደሆነ እንዳይታወቅብን በጣም በረቀቀ መንገድ ነው። ሁለት ሰዎች ስለ አገልግሎታቸው ሲመሰክሩ አንደኛው፥ *"እግዚአብሔር በኃይል ተጠቀመብኝ፥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቼ ስሰብክ ሃያ ሰዎች ጌታን ተቀበሉ፥ ብዙዎች ደግሞ በሰጠሁት*

ጌታ እንዲህ አለኝ" የሚሉ፥ እግዚአብሔርን እንደ ቀሎ ጓደኛቸው አድረገው ለማሳየት የሚሞክሩ ባሁኑ ጊዜ ብዙ እንደሆኑ የታወቀ ነው። "አንቺን እንዳገባ ጌታ ነግሮኛል፥... መኪና ገዝታችሁ እንደምትሰጡኝ ጌታ ነግሮኛል... ፓስተር እንድሆን ጌታ ነግሮኛል... አሜሪካ እንደምሄድ ጌታ በግልጽ ነግሮኛል..." በማለት እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር ያደርግ የነበረውን ዓይነት ንግግር ከእነርሱም ጋር እንደሚያደርግ በዘዴ፥ የሚናገሩ አሉ። እግዚአብሔር በእርግጥ እንደሚናገር አምናለሁ። በተለያየ መንገድ እግዚአብሔር እንደተናገረኝ አምናለሁ። ወደ አገልግሎትም የገባሁት እግዚአብሔር ጠርቶኝ ነው እንጂ፥ ሥራ አጥቼ ሥራ ለመፍጠር አይደለም። ሌላው መረዳት ያለብን እውነት ቢኖር እግዚአብሔር ከተናገረ በምንም ዓይነት ሳይፈጸም እንደማይቀር የታወቀ ነው። እንደ ሰው አሳቡን በየጊዜው አይለዋውጥም። "አደርጋለሁ" ያለውን ያደርጋል። ነገር ግን፥ እነዚህ በሁሉም ነገር ላይ "እግዚአብሔር ነገረኝ" የሚሉ አንዳንድ ሰዎች ያሉት ሳይፈጸም ሲቀር፥ እግዚአብሔር በየጊዜው ሀሳቡን እንደሚለዋውጥ አድርገው ይስሉታል። በዚህ መሐል፥ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" የሚል የሀሰት ትንቢት ተናግሮላቸው፥ ትንቢቱን ቁጭ ብለው የሚጠብቁ ምስኪን ሰዎች መኖራቸው ያሳዝናል።

መጠኑና ዓይነቱ ይለያይ እንጂ ሁላችንም "ክርስቶስ ነኝ ባይነት መልክ" (Messiah complex) አለብን። ለማድረግ የምንፈልገውን ነገር ሁሉ "እግዚአብሔር ነገረኝ" እንላለን። የሚያስደንቀው ነገር፥ እግዚአብሔር ክርስቶስን እንድንመስል ይፈልጋል። *"እንግዲህ እግዚአብሔር የሚወድዳችሁ ልጆቹ እንደመሆናችሁ መጠን እርሱን ምሰሉ፥ ክርስቶስ እንደወደደንና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መልካም መዓዛ ያለው መባና መሥዋዕት አድርጎ ሕይወቱን ስለ እኛ አሳልፎ እንደሰጠ እናንተም በፍቅር ኑሩ"* ይላል (ኤፌ. 5፥1-2)። ኢየሱስ ሲጸልይ፥ *"እኛ አንድ እንደሆንን፥ እነርሱም አንድ እንዲሆኑ ለእኔ የሰጠኸኝን ክብር ሰጥቼአቸዋለሁ"* አለ (የዮሐ. 17፥22)። *ታዲያ* ኢየሱስን መምሰላችን በምን ይታወቃል? በጉራ መንዛታችን፥ ስለራሳችን አጋነን በማውራታችን፥ በትዕቢታችን ሳይሆን በትህትናችን ነው። ከኃይል ሁሉ በላይ የሆነ ኃይል ያለውን፥ ሁሉን ነገር የሚያውቀውን፥ በአንድ ጊዜ ሁሉ ቦታ መገኘት የሚችለውን ጌታ መምሰል የምንፈልገው፥ እንደ እርሱ ኃያል ለመሆን፥ ሁሉን ለማወቅ፥ በአንድ ጊዜ ሁሉ ቦታ ለመገኘት ሳይሆን፥ እንደ ሕጻን ለመሆን ሊሆን ይገባል። የእርሱ መልክ እንዲኖረን፥ ወይም እርሱን መምሰል የምንፈልገው ኃይለኛ ለመሆን ሳይሆን ደካማ ለመሆን፥ ለመገልገል ሳይሆን ለማገልገል መሆን እንዳለበት ማወቅ ይገባናል።



እግዚአብሔር ክርስቶስን እንድንመስል ይፈልጋል። ይህም ማለት ትልቅ የመሆን ጥማት እንዲኖረን አይደለም። አለቆች እንድንሆን ሳይሆን፥ እርሱ ዝቅ ብሎ ሌሎችን እንዳገለገለ እኛም አገልጋዮች፥ ባርያዎች እንድንሆን ማለት ነው። ጀግንነታችንን፥ ታላላቅ ሥራችንን በአደባባይ ማወጅ ሳይሆን፥ ማንም በማያየን ጊዜ ሁሉ ፍቅር፥ ርህራሄና ቸርነት ያለበትን አገልግሎት ለሌሎች መስጠት በሥጋም ሆነ በመንፈስ የተራቡትን መመገብ፥ የተራቆቱትን ማልበስ፥ የተጠሙትን ማጠጣት ነው። የክርስቶስ ተከታዮች የሆንን ክርስቶስን የምንመስልበትን መንገድ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ፥ *"በትህትና ተሞልታችሁ ሌሎች ሰዎች ከእናንተ እንደሚሻሉ አድርጋችሁ ቁጠሩ እንጂ ወገን በመለየትን በራስ ወዳድነት ወይም ያለ እኔ ማን አለ በሚል ትምክህት ምንም ነገር አታድርጉ። እንዲሁም እያንዳንዱ የራሱን ጥቅም ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ሰው ጥቅም ያስብ። በዚህ ዐይነት ኢየሱስ ክርስቶስ ያሳየው የትሕትና ጠባይ በእናንተም ሕይወት ሊኖር ይገባል። እርሱ የመለኮት ባሕርይ አለው፥ ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የሚያደርገውን የመለኮት ባሕርይ እንደያዘ መቅረት አልፈለገም። ይልቁንም ያለውን ክብር በገዛ ፈቃዱ ትቶ አገልጋይ መሆንን መረጠ፥ እንደ ሰው ሆኖም በትሕትና ራሱን ዝቅ አደረገ፥ እስከ ሞት ድረስ፥ ያውም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ"* ይላል (ፊልጵ. 2፥3-5)። እዚህ ላይ እንደምንረዳው ክርስቶስን መምሰል፥ ራስን ዝቅ ማድረግ ነው።

አንዳንዶቻችን እናገለግላለን። አገልግሎትም እንደበዛልን እና ወራለን። ቁም ነገሩ ማገልገላችን፥ አገልግሎት የበዛልን መሆናችን ሳይሆን፥ የክርስቶስን ባሕሪ ይዞ ዝቅ ብሎ ማገልገሉ ላይ ነው። የተራብ የምናበላው፥ የተጠማ የምናጠጣው፥ የተራቆተ የምናለብ ሰው፥ ለመታወቅ፥ መልካም ሥራችን በሕዝብ ሁሉ ዘንድ እንዲ

ወራ ከሆነ፥ ኢየሱስን እንመስልም። በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ የሚያስገኘው ራስን ፍጹም ባዶ ማድረግ፥ ትሁት መሆን፥ አገልጋይ ወይም አሽከር መሆን ነው። እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው ናቸው ክርስቶስን እንድንመስል የሚያደርጉን። ምንድነው መሆን የምንፈልገው? ሰዎች እንዲያጨበጭቡልን፥ እንደ ድል አድራጊዎች በትከሻቸው ተሸክመውን እንዲዞሩ፥ ዕልል እያሉ እንዲሞሁልን ነው? እግራችን ሥር እንዲወድቁልን፥ ዘውድ በራሳችን ላይ እንዲደፉልን ነው? የአበባ ምንጣፍ እንዲያነጥፉልን ነው? ስለራሳችን እጋነን ስናወራ፥ "ይህን የምነግራችሁ ለጌታ ክብር ብዬ ነው" ብለን ትህትና በሚመስል ብርድ ልብስ ጠቅልለን ብናቀርበውም፥ ውስጣችን የሚፈልገውን፥ ሰው አውቆ ባይታዘበንም፥ ሁሉን የሚያውቅ ጌታ ግን አውቆ ይታዘበናል።

ክርስቶስን እንድንመስል እግዚአብሔር ሲጠራን፥ አገልጋዮች እንድንሆን መጥራቱ ነው። እርሱን ስንመስል ሥራችንን በአደባባይ "ይህን ሠራሁ፥ ያንን ሠራሁ" እያልን እያጋነንን አናወራም። በጎ ተግባራችንን በስውር እናደርጋለን። ባይጨበጨብልንም፥ ሰዎች ባያመሰግኑንም ለተጠራንበት ዓላማ እንሠራለን። ደስ ቢለንም ባይለንም፥ ቢሰማንም ባይሰማንም፥ ሁልጊዜ እንሠራለን። አሽከር ሥራው ሁልጊዜ ማገልገል ስለሆነ፥ እኛም አሽከሮች ከሆንን ቢመችንም ባይመችንም ማገልገል አለብን። እውነተኛ አገልጋይ የሆነ ሰው፥ "አያችሁልኝ ወይ?" በማለት ጉራ አይነዛም፥

መንፈሳዊ የሆነውንና መንፈሳዊ ያልሆነውን ሰው ሊለይ የሚችል ነገር ምን ይሆን? ከቤተ ክርስቲያን ውጪ የሆኑትን ሰዎች፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀታችን፥ የማስተማር ችሎታችን ይህን ያህል አይስባቸውም። ነገር ግን ዝቅ ብለን ስናገለግል ማየታቸው፥ ያ ይስባቸዋል። *ዝነኛ ወይም ታዋቂ የሆነውን ሠራተኛን የሚያንቀጠቅጥ፥ መሬት አይንካኝ፥ በር ክፍታችሁ አስገቡኝ፥ ለምን አያችሁኝ፥ ወይም "ከዚህ አነስተኛ ሰው ጋር መነጋገር አልፈልግምና ከአጠገቤ አጥፉልኝ"* የሚለውን፥ በትዕቢት የተሞላው ሰው ሳይሆን፥ ትልቅ ሆኖ እንደ ትንሽ ራሱን ዝቅ የሚያደርገውን ሰው፥ ዓለማውያንም ቢሆኑ ያደንቁታል፥ ይወዱታል። ፊሊፒንስ ውስጥ አንድ ጊዜ የአንድ የሀብታም ልጅ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ለመማር ገባ።

ተማሪዎች ትምህርታቸውን ለመጀመር በሚመጡበት በመጀመሪያው ቀን፥ ይሄም የሀብታም ሰው ልጅ ሻንጣውን ይዞ ትምህርት ቤቱ ደረሰ። ከትምህርት ቤቱ በራፍ ላይ ሲደርስ አንድ ሸሚዝ የለበሰ፥ ተራ ሰው የሚመስል ተቀበለውና ሻንጣውን ተሸክሞ ወደ ክፍሉ ይዞት ሄደ። ሰውየው ከመሄዱ በፊት ልጁ ሽንት ቤቱን ተመለከተና ጽዳት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ቅሬታውን ነገረው። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ያ ሰው ብሩሽና ውሃ በባልዲ ይዞ መጥቶ ሽንት ቤቱን የሚችለውን ያህል ፈትጎ ካጠበ በኋላ ሄደ። በዚያው ቀን ምሽት፥ የተማሪዎች መቀበያ ፕሮግራም ላይ ንግግር ያደርግ የነበረው ያ በራፍ ላይ ሻንጣውን ተቀብሎ ያስገባውና እንዲሁም ሽንት ቤቱን ያጸዳለት ሰው ነበር። ለካስ ያ ሰው ዘበኛ ወይም የጽዳት ሠራተኛ ሳይሆን፥ የኮሌጁ ፕሬዚደንት ነበር። ያ ወጣት በሕይወቱ ምን ጊዜም የማይረሳው ከፍተኛ ትምህርት ተማረ። መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሲገባ፥ አለቃ ሊሆን ሳይሆን፥ አገልጋይ ወይም አሽከር ሊሆን እንደሆነ ገባው።

*የናቪጌተርስ* (Navigators) መሥራች የሆነው *"ሎርኒ ሳኒ"* በአገልግሎት ውስጥ ያለ ሰው እውነተኛ አሽከር መሆኑ በምን ይታወቃል? ተብሎ ሲጠየቅ፥ *"እንደ አሽከር ሲቆጠር ወይም ሲታይ በሚያሳየው ሁኔታ ነው"* አለ። ከላይ ያየነው ታሪክ ሰውየው "እኔ የኮሌጁ ፕሬዚደንት ነኝ" ብሎ ራሱን ስላላስተዋወቀ፥ ልጁ የተመለከተው እንደ ተላላኪ ወይም እንደ ጽዳት ሠራተኛ ነበር። ይሁን እንጂ፥ የልጁ ግምትና ትዕዛዝ አሰጣጥ ያንን የኮሌጁን ፕሬዚደንት ቅር አላሰኘውም። ማንነቱን ለመግለጽ ወይም ራሱን ለማስተዋወቅ አልቸኮለም። ሻንጣውን የተሸከመለት፥ ሽንት ቤቱን ያጸዳለት፥ "እንዴት ዓይነት ትሁት ሰው ነው?" ብሎ እንዲያደንቀውም አልነበረም። ሰውን በኃይል እንዲሠራ የሚያደርገው ኃይል ቢኖር፥ "በሌሎች መደነቅ" ነው። ሁላችንም ላደረግነው ነገር ሌሎች እንዲያደንቁንና እንዲያመሰግኑን እንፈልጋለን። የበለጠ እንድንሠራ ያደርገናል። ጥያቄው ግን፥ ምስጋናውንና መደነቁን ካላገኘነውስ? ሰዎች እንዲያውቁልን ብልሃት ፈልገን ከሆንነው በላይ ስለ ራሳችንን እናወራ ይሆን? የመጀመሪያው የአሜሪካ ፕሬዚደንት፥ *ጆርጅ ዋሽንግተን* ከተከታዮቻቸው ጋር በፈረስ ሲጓዙ፥ ፈረሳቸው ስትዘል የድንጋይ አጥሩን በመንካቷ ጥቂት ድንጋዮች ቦታቸውን ለቀው ነበር።

*"እነዚያን ድንጋዮች ቦታቸው መመለስ አለብን" አሉ። "ምንም አይደለም፣ ሌሎች ያደርጉታል"* ሲል አንዱ መልስ ሰጣቸው። በዚህ ጊዜ ከፈረሳቸው ወርደው እነዚያን ድንጋዮች ቦታቸው መለሱት። ሁኔታው በጣም ያስደነቀው ተከታያቸው፣ *"ክቡር ጀኔራል! ይሄ ሥራ ለእርሶ ያንስቦታል"* አላቸው። እርሳቸውም *"የለም አያንሰኝም፣ ልኬ ነው"* አሉት። ራስን ዝቅ በማድረግ ማገልገል ስንፈልግ፣ ሁል ጊዜ ላንመሰገን እንችላለን። ባንመሰገንም እግዚአብሔር እንድናደ ርገው የሚፈልገውን በማድረጋችን ደስ ይለናል። ስለዚህ *በትህትና እናገልግል እንጂ፣ "ታላቅነቴን፣ ሥራዬን አያችሁልኝ ወይ?" እያ ልን ስለራሳችን ማስታወቂያ ከመናገር እንጠንቀቅ።*



# ምዕራፍ ፱

# ሰሚ ያጣ ምላስ

*"የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ! ይህን አትርሱ፣ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፣ ለመናገርና ለቁጣም የዘገየ ይሁን።"*
ያዕቆብ 1፥19

እግዚአብሔር መናገር እንድንችል ምላስ ብቻ ሳይሆን፣ መስማ ትም እንድንችል ጆሮ ሰጥቶናል። መናገር ችለን መስማት ባንችል ኖሮ፣ ከሰው ጋር የሚኖረን ግንኙነት የተሟላ አይሆንም ነበር። ንግግራችን የተሟላ እንዲሆን፣ የግድ መስማት መቻል አለብን። ሌላው ቢቀር ተናግረን መሰማታችንን ማወቅ የምንችለው፣ መስማት የቻልን እንደሆነ ብቻ ነው። እኛ መስማት መቻል ብቻ ሳይሆን፣ የምናነጋግረውም ሰው መስማት መቻል አለበት። ንግግራችን ሰሚ ካላገኘ፣ መናገራችን ጥቅም እንደሌለው እናውቃለን። ስለዚህ ከመ ናገራችን በፊት የምናነጋግረው ሰው መስማት የሚችል መሆኑን በቅድሚያ ማወቅ አለብን።

ምላሳችን ያለንበትን የጤና ሁኔታ እንደሚያመለክተው ዓይነት ጆሮአችንም ማንነታችንን ያሳይ ይሆን? በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ ምላሳችን ውስጣዊ ማንነታችንን እንደሚገልጽ በሰፊው ተመል

ክተናል። ያን ያህል ሰፊ ትንተና ውስጥ ባንገባም ምሁራን የጆሮአችንን ቅርጽ ካለን የተፈጥሮ ባሕሪና ችሎታ ጋር በማያያዝ ያቀረቡትን በመጠኑም ቢሆን እንመለከታለን። የሰውን ጆሮ በሚመለከት ሁኔታ ላይ የሥነ ልቦና (አዕምሮ) ሊቃውንት በደረጉት ጥናት መሠረት የደረሱበትን ግንዛቤና የሰጡትን አስተያየት እናምን ይሆን? የሰው ተፈጥሯዊ ባሕሪ ባለው የጆሮ ቅርጽና መጠን ይታወቅ ይሆን? ለምሳሌ፥

- *ትልቅ ጆሮ ያላቸው ሰዎች፥ ብርቱ የሆነ ተፈጥሮ ያላቸው፥ ለእውነት፥ ለአዲስ አሳብ ግድ የሚላቸውና የሚጓጉ ናቸው።*
- *ጆሮአቸው እጅግ በጣም ትልቅና ደንዳና ከሆነ፥ ትዕቢተኛና አስመሳይ የሆነ ጠባይ ያላቸው ናቸው።*
- *ትናንሽ ጆሮ ያላቸው ሰዎች፥ ጠንቃቃ፥ ብልህ፥ ጽኑ የሆኑ፥ የራሳቸው ጠንካራ የሆነ ፈቃድ ያላቸውና እንዲሁም ንቁ የሆነ አዕምሮ ያላቸው ናቸው።*
- *ሞላላ (Oval) ጆሮ ያላቸው ሰዎች፥ የጥበብ ሰዎች ናቸው፥ የማጥናት፥ የመመራመር ርሃብ (ጥማት) ያላቸው ናቸው።*
- *ጥቅል አበባ የሚመስል ጆሮ ያላቸው፥ ብስጩ፥ ስድነት የሚታይባቸው፥ የደስ ደስ የሌላቸው ናቸው።*
- *ሁለቱ ጆሮአቸው የተለያየ መጠን ያላቸው፥ ይኸውም አንዱ ትልቅ፥ ሌላው ትንሽ የሆኑ ሰዎች የራሳቸው የሆነ የተፈጥሮ ባሕሪ አላቸው፥*
  - *(ሀ) ቀኙ ጆሮው በግራ ካለው ጆሮው የሚበልጥ ከሆነ፥ እንዲሀ ዓይነቱ፥ በተፈጥሮ ችሎታው የሚሠራ፥ (instinctive ways) በአዕምሮው ከማመዛን ይልቅ፥ በቅዠት የሚያስብ ነው።*
  - *(ለ) ግራ ጆሮው ከቀኙ ጆሮው የሚበልጥ ከሆነ፥ የአዕምሮ ሰው ነው፥ ወዲያው ውሳኔ የሚያደርግ ሰው አይደለም።*

ከላይ የገለጽነው አሳብ፥ የሥነ አዕምሮ ምሁራን ያቀረቡት መላምት እንጂ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ብለን ያቀረብነው ስላልሆነ፥ ልትቀበሉትም ላትቀበሉትም ትችላላችሁ። ምርጫው የራሳችሁ



ነው። ትኩረት የምንሰጠው ከላይ ለሚታየው ጆሮ ሳይሆን፥ ከውስጥ ስላለው መንፈሳዊ ጆሮ ነው። ሰዎች ለመስማት የሚፈልጉት ምንድነው? በመጨረሻው ዘመን ስላሉት ሰዎች ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት፥ *"...ሰዎች ንጹሑን ቃል ለመስማት የማይፈልጉበት ጊዜ ይመጣል፥ ነገር ግን ለወሬ በመጎምጀት እነርሱ ራሳቸው የሚወዱትን ነገር የሚነግሩአቸውን አስተማሪዎች ይሰበስባሉ። እውነትን መስማት ትተው ተረትን መስማት ይወድዳሉ"* አለ (2 ጢሞ. 4፥3-4)።

## 1. <u>መስማት መቻል ከእግዚአብሔር የተሰጠን በረከት ነው</u>

ከሌላው ሰው ጋር የሚያገናኘን አንደኛው መንገድ ሰሚ ጆሮ ነው። መስማት ከማይችሉ ሰዎች ጋር መወያየት አንችልም። ምክንያቱም ሰምተው መልስ ሊሰጡን ስለማይችሉ ነው። ምንም ያህል የንግግር ችሎታ ቢኖረን፥ ንግግራችን ሰሚ ከሌለው ወይም ካጣ፥ ፍጹም ዋጋ የለውም። የማይሰማ መሆኑን እያወቅን ዝም ብለን ብንናገር፥ በአካባቢያችን ያሉት ሁሉ እኛን የሚመለከቱን ሞኞች አድርገው ነው። መናገርና መስማትን ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ለማስኬድ ከባድ ይሆናል። ሁለት የተጋጩ ሰዎች በንዴት ተሞልተው የሚያደርጉትን ንግግር ስንሰማ፥ አንዱ ሌላውን የሚያዳምጥ አይመስልም። ሁለቱም መናገራቸውን እንጂ፥ ሌላው የሚሰማቸው መሆኑን እርግጠኞች አይደሉም። በደንብ መደማመጥ ከፈለጉ፥ ሁለቱም በአንድ ጊዜ ከመናገር፥ ከሁለት አንደኛቸው የግድ መናገራቸውን ማቆምና ሌላው የሚናገረውን ማዳመጥ አለባቸው። ዝም ባልን ቁጥር የመስማት ችሎታችንም እየጨመረ ይመጣል።

እግዚአብሔር አንድ ምላስ፥ ሁለት ጆሮ ሲፈጥርልን ምክንያት አለው። አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት "በመጠኑ ተናገሩ፥ በብዛት ስሙ" የሚለውን መልዕክት ለማስተላለፍ ብቻ አይመስለኝም። አንደኛው ጆሯችን ቢታመም፥ በሁለተኛው ጆሮአችን መስማት እንችላለን። ያለን ያው አንዱ ምላሳችን ቢታመም፥ መናገር የሚያስችለን ሌላ መንገድ አይኖርም። ነገር ግን መናገር ባለመቻላችን

ምክንያት ከሚደርስብን አደጋ የበለጠ፥ መስማት ባለመቻላችን የሚደርስብን ጉዳት የበለጠ ነው። ስለዚህም ይሆናል አንዱ ጆሮአችን ቢታመም በሌላው እንድንጠቀም እግዚአብሔር እስቦ ሁለት ጆሮዎች የሰጠን። መስማት መቻላችን ምን ያህል ትልቅ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ መረዳት የምንችለው፥ በአንዳንድ ምክንያት ለጊዜው መስማት ሲያቅተን ብቻ ነው። ከጥቂት ወራት በፊት፥ ጆሮዬን አሳከከኝና አላግባብ ነካክቼ አቆሰልኩት። ሕክምና ወዲያው በማድረግ ፈንታ "ትንሽ ቆይቶ ይሻለኛል" እያልኩ ችላ አልኩት። ነገር ግን በመሻል ፈንታ የበለጠ ጆሮዬ አካባቢ እያበጠ መጣ። ቀምሳችሁ ላላያችሁት ከጥርስ ሕመም የበለጠ የጆሮ መጠዝጠዝ በጣም ያሰቃያል። ሌሊት መተኛት እያቃተኝ ተነስቼ ቁጭ የምልበት ጊዜ ነበር። የበለጠ እያመመኝ ሲመጣ፥ ሁኔታው አሳሰበኝና ሀኪም ለማየት ወደ ክሊኒክ ሄጄ ተመረመርኩ። ሀኪሙ ያዘዘልኝን መድኃኒት እየወሰድኩ ሁኔታውን መመልከት ጀመርኩ። አሁንም እየባሰብኝ ሄደ እንጂ አልተሻለኝም። የሚያሳዝነው ይሄ ከመሆኑ በፊት ከሁለቱ ጆሮዎቼ መካከል በደንብ የሚሰማው አንዱ ብቻ ነበር። አሁን በደንብ የሚሰማው ጆሮዬ ሲቆስልና ሲታመም፥ ሁሉም ነገር ጸጥ አለብኝ። ከሰዎች ጋር በስልክ መነጋገር አልቻልኩም። የመኪና ጩኸት፥ የሰዎች ንግግር፥ በየምግብ ቤቱ ያለው የሙዚቃ ድምጽ ሁሉ ጸጥ አለብኝ። ዓለም በጠቅላላው በጸጥታ የተሞላች መሰለችኝ። ወደ ጆሮ እስፔሻሊስት ዘንድ ሄድኩ። ድንጋጤና ፍርሃት ልቤን ሞላው። ጆሮዬ መስማት ካልቻለ፥ እንዴት እሰብካለሁ፥ እንዴት አስተምራለሁ፥ እያልኩ አስብ ነበር። የጸጥታ ዓለም ለጥቂት ቀናትም ቢሆን ምን ያህል ከፉ እንደሆነ አየሁት።

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ አንድ ቀን ጥዋት ከትልቁ ልጄ ከሙሴ ጋር ሆቴል ቁርስ ስንበላ፥ የተለመደውን ጭውውታችንን ለማድረግ በጣም ተቸግሬ ነበር። እኔ እንድሰማው በኃይል መጮኽ ነበረበት። ያም ደግሞ በጸጥታ ቁርሱን መብላት የሚፈልገውን ሰው ጸጥታ መንፈጋችን ሆኖ ስለተሰማኝ፥ ምቾት አልሰጠኝም ነበር። በዚያ ምግብ ቤት የማያቋርጥ ለስላሳ ሙዚቃ ይሰማል። ሰው ሁሉ በዚያ ሙዚቃ ደስ እንደሚለው አምናለሁ። እኔ ግን ምንም ስለማልሰማ፥ አካባቢው ሁሉ በጸጥታ የተሞላ ይመስለኝ ነበር። በዚህ መካከል አፍንጫዬን አሳከከኝና፥ መሀረቤን አውጥቼ ስናፈጥ፥ በእብጠቱ



ምክንያት ዝግት ያለው ጆሮዬ፥ ድንገት ክፍት አለና ከሁለት ሳምንት ጸጥታ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰዎችን ንግግር፥ የሙዚቃውን ድምጽ፥ የመኪናዎችን እንቅስቃሴ መስማት ቻልኩ። በዚያን ደቂቃ ምን ዓይነት ደስታ እንደተሰማኝ የምገልጽበት ቋንቋ ያንሰኛል። በመስማት ውስጥ ያለውን በጎ ነገር በማሰብ እግዚአብሔርን ማመስገን ጀመርኩ።

የብዙ ሰው ችግር መስማት አለመቻሉ ሳይሆን፥ መስማት እየቻለ መስማት አለመፈለጉ ነው። አንዳንድ ሰዎች የራሳቸውን እንጂ የሌላውን ሰው ድምጽ መስማት የማይፈልጉ ይመስላሉ። ምክንያቱ ዕውቀትን ከሌላ ሰው መስማት ስለማይፈልጉ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"ራስ ወዳድ የሆኑ ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር ተስማምተው መኖር አይሆንላቸውም። ሌሎች ሰዎች ትክክል መሆኑን ዐውቀው የሚያምኑበትን ነገር እነርሱ ይቃወማሉ። ሰነፍ የራሱን አስተያየት ብቻ መግለጥ ይፈልጋል እንጂ፥ ዕውቀትን ከሌላ ሰው መገብየት ደስ አያሰኘውም"* ይላል (ምሳሌ 18፥1-2)። መናገር እንጂ ሰምተው መልስ መስጠት አይፈልጉም። በዚህም የሚገልጡት ራስ ወዳድነታቸውን ብቻ ሳይሆን ሞኝነታቸውንም ጭምር ነው። መስማት ከሌለ ጥሩ ውይይት ማድረግ አይቻልም።

## 2. ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን፥ ጥሩ አዳማጭ መሆን ያስፈልጋል

ጥንት ግብጻውያን *"ጥሩ የመስማት ችሎታ ሲኖረን፥ ጥሩ ተናጋሪ መሆን ያስችለናል"* የሚል አባባል ነበራቸው። በዕድሜ ከኀለመሱትም ሆነ ከህጻናት ጋር መነጋገር የምንችለው፥ ማዳመጥ ስንችል ብቻ ነው። ካልሰማን፥ የተናገርነው ነገር ሰሚ ማግኘቱን ማወቅ አንችልም። ሰሚ ከሌለን ደግሞ ዝም ብለን መናገራችን ጊዜአችንና ጉልበታችንን ማቃጠላችን ይሆናል። ለዚህ ነው ሠለሞን *"መልስ ከመስጠትህ በፊት አዳምጥ፥ አለበለዚያ ሞኝና የተናቅህ መሆንህን ታሳያለህ"* (ምሳሌ 18፥13) ሲል የሚመክረን። በደንብ ሳናዳምጥ የምንሰጠው መልስ ያሳፍረን ይሆን? የሌላው ሰው ስም ሲጠራ፥ ባለመስማቴ ምክንያት የተጠራሁ መስሎኝ በሕዝብ መካከል "አቤት"

ብዬ መልስ ብሰጥ ምን ያህል ትዝብት ውስጥ እገባ ይሆን? ለምሳሌ፥ የመኪናችን ጎማ ተንፍሶ አድሮ ለመቀየር ስንታገል፥ ልጃችን አጠገባችን መጥቶ "ምን ልርዳህ?" ብሎ ሲጠይቀን፥ ምን እንዳለ ሳንሰማ ገና ለገና "ገንዘብ ሊጠይቀኝ ይሆናል የመጣው" ብለን፥ እየጮኽን "እኔ ለአንተ ገንዘብ መስጠት ሰልችቶኛል! ከአጠገቤ ጥፋ" ብንለው፥ ልጃችን "ምን ነካው አባቴ? አበደ እንዴ?" ብሎ ያስባል እንጂ እንደ ጤነኛ ሰው ላይቆጥረን ይችላል። ሠለሞን *"መልስ ከመስጠትህ በፊት አዳምጥ፥ አለበለዚያ ሞኝና የተናቅህ መሆንህን ታሳያለህ"* ሲል ይህን ዓይነቱን ስህተት ያጠቃልላል። ይሄን ዓይነት ሁኔታ የተፈጠረው ከልጃችን ጋር መሆኑ ቀርቶ ከሌላ ሰው ጋር ቢሆን፥ ምን ያህል የበለጠ ጉዳት እንደሚያደርስብን፥ እንዲሁም ከሚወደንና ከምንወደው ሰው ጋር የሚያቆራርጥ ይሆን እንደነበር የታወቀ ነው። "መልስ ከመስጠቴ በፊት ምነው ባዳመጥኩ ኖሮ" በማለት ራሳችንን እንዳይጸጸተን በቅድሚያ በደንብ እናዳምጥ።

ሐዋርያው ያዕቆብ "...*ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፥ ለመናገርና ለቁጣም የዘገየ ይሁን*" (ያዕ. 1፥19) ሲል፥ ሦስት ሀሳቦችን እንደ ገለጸ እናያለን። ብዙዎቻችን የዚህ ዓይነቱ ችግር እንዳለብን ስለሚያውቅ ነው ሐዋርያው ያዕቆብ "...*ሰው ሁሉ*" ያለው። ሦስት ሀሳቦች ያልነው፥ 1) *መስማት*፥ 2) *መናገርና* 3) *መቆጣትን* ነው። ሦስቱም እርስ በርሳቸው የተያያዙ ናቸው። በደንብ ማዳመጥ፥ ብልህ የሆነ መልስ መስጠት ወይም ንግግር ማድረግ ያስችላል። ብልህ የሆነ መልስ ስንሰጥም ቁጣን ያበርዳል። ለዚህ ነው ጠቢቡ ሠለሞን *"ልዝብ አነጋገር ቁጣን ያስታግሣል፥ ግልፍታ የተሞላበት አነጋገር ግን ቁጣን ያባብሳል"* ያለው (ምሳሌ 15፥1)። ሰው ቁጣውንና ንግግሩን መቆጣጠር የሚያስችለው፥ በደንብ "ማዳመጥ" ወይም መስማት ነው። ተቆጥተን የምንናገራቸው ንግግሮች አንዴ ከአፋችን ከወጡ ልንመልሳቸው ስለማንችል ብዙ እንድንጸጸት፥ እንድናዝንና እንድናፍር ያደርጉናል። ዋልተር ዋንገሪን የተባለ ክርስቲያን ጸሀፊ፥ አንድ ጊዜ ከሚስቱ ጋር በነበረው ጭቅጭቅ ምክንያት፥ ንዴቱ ያደረሰበትን ትልቅ ሀፍረት ይገልጻል። ዋልተር ከሚስቱ ጋር ሲጋጭ፥ ተናጋሪው እርሱ ሲሆን፥ የማትናገረው፥ ወይም ዝም የምትለው ሚስቱ ነች። የሚፈልገውን ከባድ ቃል ከወረወረና እርሷም ትንሽ ካለቃቀሰች በኋላ ግን፥ ጭቃ ጅራፏን ታመጣዋለች።



የቆየና ጊዜ ያለፈበት ቢሆንም ከዚህ በፊት የበደላትን በደል ጥቃቅን ሁሉ ሳይቀር እየዘረዘረች ወቀሳዋን ስታፈስበት ይበሳጭና ቤቱን ለቆ በመውጣት ለሦስት ሰዓት ያህል ውጪ ይዞራል። ጊዜው ክረምት በነበረበት አንድ ወቅት ከሚስቱ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ተጋጭቶ ተበሳጭቶ እንደተለመደው በሩን በኃይል ዘግቶ ወጣ። የሚያሳዝነው ኮቱን ሳይለብስ በሸሚዝ ብቻ ነበር። የመኪናውንም ሆነ የአፓርትመንታቸውን የበር ቁልፍ ኮቱ ውስጥ ነበር። ሁለት ምርጫ ነበረው። አንደኛው ራሱን ዝቅ አድርጎ "እባክሽን ክፈችልኝ" ብሎ ማንኳኳት፥ ሁለተኛው ትዕቢቱን እንደያዘ ውጪ በብርድ መሰቃየት ነበር። ምንም ድምጽ ሳያሰማ ወይም ሳይናገር ማንኳኳት ጀመረ። ሚስቱም ያለበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ተግንዝባ መሳቅ ጀመረች። ባደረገው ሁኔታ ይቅርታ በመጠየቅ ፈንታ፥ ራሴን ዝቅ አላደርግም ብሎ በብርድ መንከራተት ጀመረ። በሁኔታው አዝና ያለቀሰችውን ለቅሶዋንም ሆነ ይቅርታ ለመስጠት የሳቀችውን ሳቅ አልሰማም። ባደረገውና በወሰደው እርምጃ ተዋረደ። ሁላችንም ለመስማት ፈቃደኞች ባለመሆናችን ምክንያት "ደረሰብን" የምንለው ተመሳሳይ ታሪክ ሊኖረን ይችላል።

ምሁራን፥ ምንም የማይናገሩ ሁለት ዓይነት ሰዎች እንዳሉ ይገልጻሉ። እነርሱም አንደኛው፥ የሚናገረው ነገር ምንም የሌለው ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ሁልጊዜ የሚናገር ሰው ነው። የምንናገረው ምንም ነገር ከሌለን፥ መናገር ያለብን መስሎን ዝም ብለን እንናገር። መቼ ዝም ማለት እንዳለብን እንወቅ። በአንድ ኮሌጅ ቅጥር ግቢ (ካምፓስ) ውስጥ ንግግር እንዲያደርግ የተጋበዘ አንድ የታወቀ ሰው፥ ከመናገሩ በፊት ፕሮግራሙን የሚመራውን ሰው "ምን ያህል መናገር እችላለሁ?" ብሎ ጠየቀው። ሰውየውም *"የፈለግኸውን ያህል መናገር ትችላለህ፥ ተማሪዎቹ ግን ልክ በድስት ሰዓት ሲሆን ይሄዳሉ"* አለው። በዚህ ዓይነት ንግግሩን መቼ ማብቃት እንዳለበት በትህትና መንገሩ ነው። ምሁራን ጥሩ ተናጋሪ የሚያስኘውን ሦስት ጠቃሚ ነጥቦች ሲሰጡ፥ (1) "እንድትታይ ቆመህ ተናገር፥ (2) እንድትሰማ ድምጽህን ከፍ አድርገህ ተናገር፥ (3) እንድትደነቅ፥ ንግግርህን በወቅቱ አቁም" ይላሉ። የምንናገረውን ነገር ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ መቼ መጨረስ ወይም ዝም ማለት እንዳለብን ማወቁም

ነይነት መልስ ልስጥ?" በማለት በውስጣቸው ያሰላስላሉ፥ መከላከያቸውን ያዘጋጃሉ። ተናጋሪው ጨርሶ መልስ እስከሚሰጡ ይቸኩላሉ። በዚህ ወቅት ተናጋሪው የሚያዳምጠው የለም። ለብቻው እየተናገረ ነው። ሰሚ በሌለበት ብቻውን የሚናገር ሰው ጤነኛ ሳይሆን፥ ራሱን የታመመ ሰው ብቻ ነው። ተናጋሪው አዳማጭ እንደሌለው ከገባው "ብቻዬን የምናገረው እኔ እብድ አይደለሁም" ብሎ ንግግሩን ያቆማል።

## 4.4. <u>ለመፍረድ እናዳምጣለን</u>

ብዙዎቻችን ብዙ ጊዜ የምናዳምጠው በጥሩ መንፈስ ሳይሆን፥ በተናጋሪው ላይ ለመፍረድ ብቻ ነው። የማዳመጥ ጊዜያችንን "አይረባም... ሰነፍ ነው... የራሱን ጥቅም ብቻ ፈላጊ ነው... ስለሌላው ሰው ፈጽሞ ግድ የለውም... ለመለወጥ ፈቃደኛ የሆነ ሰው አይደለም..." በማለት እየፈረድን እናዳምጣለን። ሁሉን የማወቅ ችሎታ ያለን ይመስል፥ የሰው አዕምሮ ለማንበብ እየሞከርን "እንዲህ ነው" በማለት መፍረድ እንጀምራለን። ስለ ሌሎች አዕምሯችን በአሉታዊ ነገር የተሞላ ይሆናል። እውነተኛውን ነገር እኛ በአዕምሮአችን "ይሆናል" ብለን ከምንገምተውና ከምናስበው ነገር መለየት አንችልም።

ይህንን የበለጠ ለመረዳት የሁነኛውንና የቴዎድሮስን ውይይት እንመልከት። ቴዎድሮስና ሁነኛው ጓደኝነታቸው አሜሪካ አገር ከመጡ በኋላ ሳይሆን ገና ኢትዮጵያም እያሉ የሚተዋወቁ ጓደኞች ናቸው። አንድ ቀን ሁነኛው ቴዎድሮስን "መኪናዬ ገራዥ ነችና አባክህን ባለኝ በነዚህ በሦስት ቀናት ውስጥ ከአገር ቤት የመጣ ዘመድ አለኝና ሚሽገን ስቴት ሄጄ እንዳየው መኪናህን አውሰኝ" አለው። በነዚያ ቀናት ውስጥ ቴዎድሮስ የራሱ ዕቅድ ነበረው። "ሁነኛው በጣም አዝናለሁ፥ ቀደም ሲል ያወጣሁት ዕቅድ አለ። ከአስር ዓመት በፊት አብረን የተመረቅነው የኮሌጅ ጓደኞቼ ጋር ለመገናኘት ዕቅድ ስላወጣን ወደዚያ እሄዳለሁ። የትም የማልሄድ ቢሆን ኖሮ ታውቃለህ ደስ ብሎኝ እሰጥህ ነበር" አለው።

ሁነኛው የጠበቀውን ዓይነት መልስ ባለማግኘቱ ተበሳጭቶ ለአስማማው እንዲህ አለው። "በጣም አዝኛለሁ... ተናድጃለሁ... በሰው ተስፋ ቆርጫለሁ" አለው።



አስማማውም "ምነው? ምን ሆንክ? ምን ችግር አጋጠመህ? አለው።

አስማማው፥ "በቴዎድሮስ ልቤ በጣም አዘነ፥ ልቤ በጣም ተሰበረ። በእርሱ ከፍተኛ እምነት ነበረኝ። ሙትልኝ ብለው እንኳን የሚሞትልኝ ይመስለኝ ነበር። መኪናውን እንዲያውሰኝ ጠይቄው ከለከለኝ። እኔ ብሆን እንኳን መኪናዬን ያለኝን ንብረቴን ሁሉ እሰጠው ነበር። ቴዎድሮስ በጣም ጉረኛ ነው! መንገድ ፈልጎ የኮሌጅ ምሩቅ መሆኑን መናገር ይፈልጋል። ገንዘብ የሚወድ፥ የራሱ የሆነውን ለማንም የማይሰጥ ንፉግ ሰው ነው። እኔ የጠየቅሁት በጓደኛነታችን ተማምኜ ብቻ ነው። መኪና ተከራይቼ መሄድ እችል ነበር" አለው። ሁነኛው የጠበቀውን ዓይነት መልስ ባለማግኘቱ ተበሳጭቶ በቴዎድሮስ ላይ መፍረድ ጀመረ። የአስማማውን ድጋፍ ለማግኘት፥ ቴዎድሮስ ለምን መኪናውን እንዳልሰጠው ምክንያቱን በደንብ አልነገረውም። የሚያሳዝነው አስማማውም "ምን ዓይነት ምክንያት ሰጠህ?" ብሎ ያልጠየቀው መሆኑ ነው። ቴዎድሮስ "መኪናዬን አልሰጥህም" አላለውም። በሌላ ቀን ቢጠይቀው ያለማመንታት ይሰጠው ነበር።

ለመፍረድ ሲል ብቻ ከሌላው መስማት የሚፈልግ ሰው፥ ያ እውነተኛ ሰው አይደለም። ለምሳሌ አንዱ ተጨንቆ "እባክህን ጸልይልኝ። እኔና ባለቤቴ ትልቅ ችግር አለብን። ችግራችንም ልጃችን ነው። አንድ ልጅ ብቻ በመሆኑ ያሳደግነው እያሳሳንለት ነው። ትምህርት ቤት እሄዳለሁ እያለ የትም ውሎ ይመጣል። ከትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ተደውሎልን ዛሬ ሄደን ነበር። ይሆናል ብለን የማንገምተውን ዓይነት መጥፎ ዜና ሰማን። ጌታ እጁን ካልዘረጋልን በስተቀር በእኛ ኃይልና ጉልበት ምንም ማድረግ አንችልም። እባክህን ጸልይልን" ብሎ ይነግረዋል። ሰሚው የሰውየውን ጭንቀት እየሰማ በአዕምሮ ውስጥ የሚመላለሰው የሀዘኔታ፥ የርህራሄ መንፈስ ሳይሆን፥ የራሱን ቅድስና፥ የራሱን ድል በመቁጠር በሌላው ላይ እንዲህ እያለ ይፈርዳል። "የእንደዚህ ዓይነቱ መጥፎ ልጅ ወላጅ ስላላደረገኝ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። ፈሪሃ እግዚአብሔር ባለው መንገድ ቢያሳድጉት ኖሮ፥ ዛሬ ይህን የመሰለ ውጤት በልጃቸው ላይ አያዩም ነበር። የእጃቸውን ፍሬ እያገኙ ነው። እያሞላቀቁ፥ 'አፈር አይንካህ' እያሉ ማሳደጉ ውጤቱ ይሄ ነው። የወላ

*ጆቹ የራሳቸው ድካም ነው። የእኛ ልጆች እንደዚህ ቢሆኑ ኖሮ እኔ አብድ ነበር። ተጠንቅቆ በማሳደግ ፈንታ መጨረሻ ላይ ማልቀሱ ጥቅም የለውም። 'አገልግሎት አለኝ' እያሉ ቀንና ማታ ቤተ ክርስቲያን ከመሮጥ አርፈው ልጃቸውን አያሳድጉም ነበር?"* በማለት የራሱን ቅድስና ለራሱ ይዘረዝራል።

## 5. <u>ማንን እናዳምጥ?</u>

ጆሮአችንን ለማግኘት የሚሻሙ ብዙ ሰዎች አሉ። የመጣውን ሁሉ ማስተናገድ ከባድ ነው። ጸጋ የማይሰጠውን ነገር መስማት ጸጋን ይገፋል። አሉባልታ የጠማቸው፥ ወሬ የሚያመላልሱ፥ ተናግረው የሚያናግሩ፥ ሁልጊዜ ነገርን አጨልመውና አጥላልተው የሚያወሩ ብዙ አሉ። የማይረባውን ሁሉ ቁጭ ብሎ መስማት ጊዜ ማጥፋት ከመሆኑም በላይ፥ የወሬ ሱሰኛ ያደርጋል። "አሉባልታ ካላወራን ልንፈነዳ ነው" የሚሉ ብቻ ሳይሆኑ፥ "በከተማው ምን ይወራል? ...ወሬ ተራብን፥ ...ወሬ ተጠማን.." የሚሉም እንዳሉ ማወቅ አለብን። ወሬኞች ሰሚ ካገኙ፥ ከወሬያቸው አይላቀቁም። ወሬኞችን ለማስቆም አንደኛውን ትልቁ መንገድ፥ ጆሮን መከልከል ነው። በሰው ሕይወት ውስጥ ጣልቃ ገብተው ወሬ በማመላለስ የሌላውን ሰው ሕይወት ለሚያምሱት አሉባልተኞች፥ ጆሮአችንን ከመስጠት ይልቅ ታላቁ ፍሬዴሪክ የሰጠውን ዓይነት መልስ መስጠት ብንችል ቁጥራቸውን መቀነስና ተንኮላቸውም ብዙ ሰው እንዳይጎዳ እናደርግ ነበር።

አንድ ጊዜ አንዲት ሴት የራሽያ ንጉሥ የነበረው ታላቁ ፍሬድሪክ ዘንድ አቤቱታ ይዛ ቀረበች። አቤቱታዋም "ንጉሥ ሆይ! ባሌ ያለማባብ ያንገላታኛል፥ ይደበድበኛል" የሚል ነበር። ንጉሡም በደንብ ካዳመጣት በኋላ "ያ እኔን አይመለከተኝም፥ ያንቺና የባልሽ ጉዳይ ነው" የሚል መልስ ሰጣት። ሴትዮዋም ተንኮለኛ ስለነበረች ባሏን ከንጉሡ ጋር አጋጭታ ለመጉዳትና ለመበቀል አስባ "ንጉሥ ሆይ! ስለ እርሶም ቢሆን ክፉ እንጂ በጎ ነገር አያወራም" አለቻቸው። ንጉሡም በጥበብ የተሞሉ ስለነበሩ፥ ተንኮሏም ስለገባቸው "ያ ደግሞ አንቺን አያገባሽም፥ ያ የእኔና የእርሱ ጉዳይ ነው" በማለት አፏን አስይዘው ላኳት።



## 6. <u>በደንብ ማዳመጥ እንዴት እንችላለን?</u>

መጽሐፍ ቅዱስ "ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ይሁን..." ሲል፥ መስማት የሰውን ጥረትና ጉልበት ይጠይቃል ማለቱ ነው። እውነተኛ፥ የፍቅር ሰው ለመሆን ጥሩ ማዳመጥ መማር አለብን። ጥሩ አዳማጭ ለመሆን፥

### 6.1. <u>በሁኔታው ውስጥ መገኘት ያስፈልጋል</u>

በአካል ተገኝተው ፈጽሞ ግን የማያዳምጡ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ የታወቀ ነው። ቤተ ክርስቲያን በየሳምንቱ ተገኝተው ሰባኪው ሲሰብክ ካንቀላፉ፥ ሥጋቸው እንጂ አዕምሮአቸው ስላልተገኘ በቤተ ክርስቲያን የሚሰበከውን ስብከት አይሰሙም። በደንብ ማዳመጥ የምንችለው አዕምሯችን ንቁ ሆኖ የሚነገረውን ሲከታተል ነው። አንዳንድ ሰዎች፥ ሰሚው ለመስማት ምንም ማድረግ የሌለበት፥ በብርጭቆ ውሃ እንደ መሙላት፥ ወይም ካሴት መቅጃ ድምጽን ዝም ብሎ እንደሚቀዳው ዓይነት የሚመስላቸው አሉ። ይሁን እንጂ የሰው አዕምሮ ከዝያ የተለየ ነው። ሰው የሚሰማውን ንግግር አዕምሮው እንዲያስብ፥ እንዲመዝን መፍቀድ አለበት። ለምሳሌ፥ ሰባኪው ሲሰብክ የሚናገረውን ዋና ዋና ሀሳብ በማስታወስ ደብተራችን ላይ እያሰፈርን ከሆነ፥ በአካል ብቻ ሳይሆን በአምዕምሮም ተገኝተን ንግግሩን ማዳመጣችንን የምናረጋግጥበት አንዱ መንገድ ነው። በስብሰባው ላይ ተገኝተን አዕምሮአችን በንግግሩ ላይ በማተኮር ፈንታ የፈለገውን እንዲያስብ ነጻነት ከሰጠነው፥ ተናጋሪው ሲናገር በወቅቱ እዚያ ብንገኝም፥ በአዕምሮአችን ስላልተገኘን የተናገረውን ማዳመጥ አንችልም። ተናጋሪው የእኛን አዕምሮ ለመሳብና እንድናዳምጠው ለማድረግ የራሱን ጥረት እንደሚያደርግ ሁሉ፥ እኛም ለመስማት የራሳችንን ጥረት ማድረግ አለብን።

### 6.2. <u>ንቁ ሆኖ በአዕምሮ ማመዛዘን ያስፈልጋል</u>

ሰው የማሰብ ፍጥነቱ ምን ያህል ነው? የሥነ ልቦና (አዕምሮ) ሊቃውንት በላቦራቶሪ ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ሙከራ አድርገዋል። የትኛውም ፈጣን ተናጋሪ ሰው ከሚናገረው የበለጠ፥ የማሰብ ፍጥነቱ እንደሚቀድም የታወቀ ነው። "ሀሳብ" በሰው አዕምሮ እንደ

ኤሌክትሪክ ከረንት ብልጭ የሚል በመሆኑ፥ ተናጋሪው የሚናገረውን እያዳመጥን ብዙ ነገር ማሰብ እንችላለን። ፈጣን የሆነውን የአዕምሯችንን የማሰብ ችሎታ እየተጠቀምን፥ ተናጋሪው የሚናገረው ነገር ልክ መሆኑንና አለመሆኑን እንመረምራለን፥ ልክ አይደለም ብለን የምናስብ ከሆነ ልክ ያልሆነባቸውን ምክንያቶች በአዕምሮአችን እናሰላስላለን። ተናጋሪው የሚናገረውን አሳብ አዕምሯችን እንዲያስብና እንዲያመዛዝን ስንፈቅድለት፥ እየሰማን መሆኑን እና ረጋግጣለን።

## 6.3. <u>*የሌላውን ሰው ስሜት መረዳት ያስፈልጋል*</u>

በደንብ ስናዳምጥ የሌላውን ሰው ችግርም ሆነ ስሜት እንደራሳችን አድርገን እናዳምጣለን። ጥሩ ሀኪም በሥራው ጥሩ ውጤት ከሚያስገኙለት ነገሮች መካከል አንደኛው በሽተኛው የሚሰማውን ሕመም እንደራሱ አድርጎ መውሰድ የቻለ እንደሆነ ነው። የሥነ ምክር አገልግሎት የሚሰጠውም ሰው ራሱን ከሰውየው ችግር ውጪ አድርጎ፥ ወይም ራሱን እሰውየው ሁኔታ ውስጥ ሳያስገባ ከውጪ ሆኖ ለመርዳት ቢሞክር፥ ጥሩ ውጤት ማግኘት አይችልም። ምክር ፈላጊው የሚሰማውን ስሜት፥ ብሶቱንና ጭንቀቱን እንደራሱ አድርጎ ከወሰደው እንዲህ ዓይነቱ ምክር ሰጪ አዳማጭ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ *"ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ፥ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ"* (ሮሜ 12፥15) ሲል፥ የሌላው ስሜት ተካፋይ ሁኑ ማለቱ ነው። የሌላውን ሰው ስሜት የበለጠ ለመረዳት፥ ተናጋሪውን እያዳመጥነው በአዕምሮአችን ልንጠይቃቸው የሚገቡ አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ። ምን እየተሰማው ይሆን? በእርሱ ላይ የደረሰው ነገር በእኔ ላይ ቢደርስ ኖሮ እንዴት እሆን ነበር? በዚህ ዓይነት ስሜት ሆነን የምንሰጠው መልስ ተራ ንግግር ሳይሆን፥ እውነተኛና የሚያረካው ይሆንለታል።

## 6.4. <u>*የግል ስሜታችንን ችላ አንበል*</u>

አዕምሮአችን የሚያስበው ተናጋሪው የሚናገረውን ወይም ተናግሮ ሲጨርስ ልንመልስለት የምንፈልገውን ነገር ብቻ የምናስብ ከሆነ፥ ጥሩ ሰሚ ለመሆን የሚያስችለንን ትልቁን ክፍል ችላ ብለ



ናል። ያም የግል ስሜታችን ነው። ተናጋሪው ሲናገር የሚሰማን ስሜት እንዳለ ግልጽ ነው። ለምሳሌ ባልና ሚስት ሲጋጩ፥ አንደኛው በራሱ በኩል ያለውን ሁኔታ ሲገልጽ፥ ሌላው ሲያዳምጥ፥ የሚያዳምጠው ሰው ስሜት ምን ዓይነት ነው። ስናዳምጥ እንደ ሁኔታው ይለያያል።--የደስታ፣ የሀዘን፣ የንዴት፣ የፍቅር፣ የጥላቻ፣ የፍርሃት፣ የስጋት፣ የተስፋ መቁረጥ፣ ወዘተ የመሳሰሉ ስሜቶች ሊሰሙን ይችላሉ። እነዚህ ስሜቶች ሲሰሙን፥ የተናጋሪውን እንባ ለመጥረግ፥ ...አይዞህ ብለን ለማቀፍ፥ ወይም በንዴት ተሞልተን ለመግፋት ይቃጣን ይሆናል። አንዳንዴም በሰውየው ላይ በኃይል መጮኽ ይከጅለናል። ብዙ ጊዜ ስሜታችንን አፍነን ወይም ደብቀን ለማለፍ እንሞክራለን። ይህን ስናደርግ ለጊዜው ምንም ላይሰማን ይችላል። ይሁን እንጂ፥ እየቆየና እየተጠራቀመ ሲመጣ አንዳንድ የጤና ቀውስ ሊያስከትል ይችላልና አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው። ለምሳሌ ባልና ሚስት አንዳቸው ሌላቸውን ክፉ ቃል ቢናገሩ ክፉ የተሰነዘረበት ወገን፥ የተሰማውን ስሜቱን ወይም ጉዳቱን በመግለጽ ፈንታ፥ ጠብ ለማብረድ ሲል ዝም ሲል፥ ችግሩን መፍታቱ ሳይሆን፥ ደብቆ ማቆየቱ ነው። ስለዚህ የሚሰማንን ስሜት ችላ በማለት ፈንታ ተገቢ በሆነው መንገድ መግለጽ መቻል አለብን።

## 1.4/ ብዙ የሚናገር ምላስ

ብዙ የሚናገር ሰው፥ ሳያስብ የመጣለትን ሁሉ ስለሚናገር፥ በንግግሩ ሊስት ይችላል። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ገንቢ ያልሆነ ክፉ ቃል ሊናገር ይችላል። ሠለሞን ብዙ ስለሚናገር ሰው እንዲህ ይላል። *"ከብዙ ንግግር ውስጥ ስሕተት አይጠፋም፥ ስለዚህ አስተዋይ ሰው ብዙ ከመናገር ይቆጠባል"* ይላል (ምሳሌ 10፥19)። ከንግግር ብዛት የተነሳ ገንቢ ያልሆነ ቃል ከሰው አፍ ይወጣና በሰዎች መካከል ግጭትን በመፍጠር ሊኖር የሚገባውን ሕብረት ሊያጠፋ ይችላል። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ለአንድነታቸው መደፍረስ ምክንያት የሆናቸው አንደኛው፥ ከመሥመር የወጣ ንግግራቸው እንደሆነ የታወቀ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ *"...በእናንተ ዘንድ ጥል፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣ የሰው ስም ማጥፋት፣ ሐሜት፣ ትዕቢት፣ ሁከት ይኖሩ ይሆናል ብዬ እፈራለሁ"* ይላቸዋል (2 ቆሮ. 12፥20)።

ቁጣና ንግግር አብረው እንደሚሄዱ ሐዋርያው ያዕቆብ በጻፈው መልዕክት ላይ ተመልክተናል (ያዕ. 1፥19)። ስንቆጣ፥ ሳናስብና ሳንጠነቀቅ የመጣልንን ሁሉ ዝም ብለን ስለምንናገር ክፉ ቃል ከአፋችን ሊወጣ ይችላል። በቁጣ ተሞልተን የምንናገረው ክፉ ቃል ደግሞ ብዙ ጊዜ ጠብን እንደሚያነሳሳ የታወቀ ነው። በመካከላችን የሀሳብ ልዩነት ቢኖር፥ ወይም ሀሳባችን የተለያየ ቢሆን ማናችንም አንጎዳም። ልንጎዳዳ የምንችለው፥ ጥንቃቄ በጎደለው ክፉ ምላስ ብቻ ነው። ብዙ የመናገር ዝንባሌ ያለው ሰው፥ ሁልጊዜ ንግግሩ ሥርዓት የጠበቀ አይደለም። ትክክለኛ ውይይት ለማድረግ አንዱ ብቻ ሳይሆን፥ ሁለቱም ወገን የመናገር ዕድል ሊኖራቸው ይገባል። የሚያሳዝነው ግን አንዳንድ ሰዎች ሌላው እንዲናገር ዕድል የማይሰጡ መሆናቸው ነው። አልፎ አልፎ ለመናገር ቢሞክር እንኳን፥ በመካከል ጣልቃ እየገቡ ንግግሩን ያስቆሙታል። ሌላው እንዲናገር ዕድል ነፍጎ "እኔ ብቻ ልናገር" የሚለውን ሰው መታዘብ ብቻ ሳይሆን ያስቆጣናል። ብዙ የሚናገሩ፥ "እኔን ብቻ ስሙኝ" የሚሉ ሰዎች ጓደኛ ማፍራት አይችሉም። ምክንያቱም ብዙ መናገር ስለሚያበዙ፥ የቀረባቸው ሁሉ እነርሱን ብቻ መስማት ይሰለቸውና ቶሎ ይሸሻቸዋል።

በሰው ዘንድ ተወዳጅነት የሚኖራቸው ብዙ የሚናገሩ ሳይሆኑ፥ ልባቸውን ሰጥተው የሚያዳምጡ ሰዎች እንደሆኑ የታወቀ ነው። "እኔ ብቻ ልናገር፥ ሰው ሁሉ እኔን ያዳምጠኝ" ማለት ተወዳጅነት የሚያስገኝ ጠባይ አይደለም። ይሉኝታ ይዟቸው ዝም ይበሉ እንጂ፥ የራሱን ድምጽ ብቻ ለመስማት ከሚፈልገው ሰው ጋር ወዳጅነት መፍጠር የሚፈልግ ሰው አይኖርም። የራሳቸውን ድምጽ ብቻ መስማት ለሚፈልጉ ሰዎች አንድ ጠቃሚ ምክር አለን። ይኸውም ንግግራቸውን በካሴት ቀድተው ቤታቸው ውስጥ ሲሆኑ፥ ቤታቸው ውስጥ ባለው የካሴት ማጫወቻ፥ ጉዞ ላይ ሲሆኑ ደግሞ መኪናቸው ውስጥ ባለ ካሴት ማጫወቻ እያስገቡ ሲገቡና ሲወጡ ሁልጊዜ ያዳምጡት። ለጥቂት ቀናት ይህን ካደረጉ፥ የራሳቸውን ድምጽ ደጋግሞ መስማት ስልችት እንደሚላቸውና እንዲሁም ለብዙ ጊዜ በትዕግሥት ላዳመጧቸው ሰዎች እንደሚያዝኑ እርግጠኞች ነን። እነርሱን ከሰለቻቸው፥ ሌላውም ሊሰለቸው እንደሚችል ተገንዝበው ንግግራቸውን በልክ እንደሚያደርጉ እምናለሁ። ብዙ የመናገር በሽታ ያለባቸው ሰዎች፥ ብዙ ሲናገሩ ድንቁርናቸውን፥ አለማወቃቸውን ማሳወቃቸው እንደሆነ አይገነዘቡም። ዝም ቢሉ አላዋቂ ቢሆኑ እንኳን፥ አላዋቂነታቸው ስለማይታወቅባቸው እንደ አዋቂዎች ይቆጠሩ ነበር። ሠለሞን *"በዕውቀቱ የሚተማመን ሰው ሁልጊዜ አይለፈልፍም፥ የረጋ መንፈስ ያለውም ሰው አርቆ ማስተዋል ይችላል። እንዲያውም ሰነፍ ዝም ቢልና አፉን ቢዘጋ፥ ጠቢብና አስተዋይ ሊመስል ይችላል"* ይላል (ምሳሌ 17፥27-28)። የምንናገረውን የማናውቅ ከሆነ ዝም በማለት አለማወቃችንን መደበቅ ይሻለናል።

## 1.5/ የማያዳምጥ ጆሮ

መናገርና ማዳመጥ አብረው የሚሄዱ ናቸው። በሕይወታችን መናገር ብቻ ሳይሆን፥ መስማትም ጠቃሚ የሆነ ነገር ነው። ስለዚህ ቀዶ ጥገና የሚያስፈልገው ምላሳችን ብቻ ሳይሆን፥ ጆሮአችንም ጭምር ነው። በአሁኑ ጊዜ ሰው ያጣው የሚያወራለት ሳይሆን፥ የሚያዳምጠው ሰው ነው። በልባቸው ውስጥ የሞላውን፥ ከውስጥ የሚሰማቸውን ጭንቀትና ሰላም ማጣት ሲገልጹ፥ ጆሮውንና ልቡን ከፍቶ የሚያዳምጣቸው ሰው ይፈልጋሉ። ቤተ ክርስቲያን ሁሉም ሰባኪ ለመሆን ስለሚፈልግ ተናጋሪ አላጣችም። ያጣችው ግን በጭ

እንዲለውጠው ፈቃደኛ ሆኖ ራሱን የሰጠ ሁሉ፥ ሙሉ ይቅርታን አግኝቶ በአዲስ ሕይወት ውስጥ መመላለስ ይችላል። እውነተኛ የሕይወት ለውጥ ያለው ሰው ከአፉ ክፉ ቃል፥ ለሚሰሙት ጸጋን የማይሰጥና ለማነጽ የማይጠቅም፥ ለሰዎች አስፈላጊ ያልሆነውን ቃል አይናገርም (ኤፌ. 4፥29)።

ሐዋርያው ጴጥሮስ ብዙ ደካማ ጎን እንደ ነበረው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ይሁን እንጂ፥ ሊሆን የሚፈልገውን (የሚመኘውን) እንዲሆን እግዚአብሔር አስቻለው። ጴጥሮስ በሕይወቱ ደካማ ጎን የነበረው ሰው ይሁን እንጂ፥ ኢየሱስን ከልቡ የሚወድና በፍጹም ልቡ ሊያስደስተው የሚፈልግ ሰው እንደነበረ እናውቃለን። ጴጥሮስ ሙሉ ለውጥ አግኝቶ ክርስቶስ እንደሚፈልገው መሆን ከቻለ፥ እኛም ሙሉ ለውጥ አግኝተን ጌታ ከሚፈልገው መንፈሳዊ ደረጃ ላይ መድረስ እንችላለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ከመንፈሳዊ ድካም የተነሳ ቁጠኞች፣ ችኩሎች፣ አሉባልታ አውራዎች፥ የማይገባንን የምንናገር ብንሆንም፥ ለነዚህ ሁሉ ይቅርታን አግኝተን አዲስ ሰዎች እንሆናለን ብለን እናምናለን። እውነተኛ የሆነ ለውጥ ሲኖረን፥ አዲስ ሕይወት፥ እንዲሁም የተፈወሰ ምላስ እንደሚኖረን የታወቀ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ዕቅድ ሲገልጽ፥ *"...በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር እንዲሆን እግዚአብሔር አስቀድሞ የመረጣቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ ስለ ወሰነ ነው"* ይላል (ሮሜ 8፥29)። በክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ልጆች ስንሆን፥ *"የልጁን መልክ"* ስንይዝ፥ የክርስቶስ ባሕሪ በውስጣችን ስለሚኖረን፥ ምላሳችን በማጥፋት ፋንታ ይፈውሳል። ተስፋ የቆረጡትን፥ በተስፋ ይሞላል፥ ያዘኑትን ያጽናናል፥ ለደከሙት ጉልበትን ይሰጣል።

ሰው በዚህ ዓለም ምን ያህል ዘመን እንደሚኖር አያውቅም። ምናልባት የቀራችሁ ዕድሜ ይህንን መጽሐፍ አንብባችሁ የምትጨርሱበትን ያህል ጊዜ ብቻ ይሆናል። ስለዚህም፥ በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ ማደግ መጀመር ያለባችሁ፥ ምላሳችሁ መፈወስ ያለበት ነገ ወይም ወደፊት ሳይሆን፥ ዛሬውኑ መሆን አለበት። ዕድገታችሁም አንድ ቦታ የሚቆም ሳይሆን፥ እስከ ሕይወታችሁ ማብቂያ ድረስ መሆን አለበት። ሰው በሕይወቱ ለውጥ የሚጀምረው፥ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት በእምነት ተቀብሎ ከእግዚአብሔር አብ



ጋር በመታረቅና ከእርሱ ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ሲፈጥር ነው። በአዲስ ሕይወት ካልተወለደ፥ በራሱ ጥረትና ትግል ምንም ዓይነት ለውጥ በሕይወቱ ማምጣት አይችልም። ያልተለወጠ፥ ወይም ያልዳነ ሰው ምላሱ አጥፊ ነው። ችግሩ ያለው ምላሱ ላይ ሳይሆን፥ ውስጣዊ ሕይወቱ ላይ ነው። ውስጡ በመንፈስ ቅዱስ ተነክቶ ሲለወጥ፥ ምላሱም የተፈወሰ ይሆናል። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ጊዜ በምላስ ጦርነት የሚቆሰሉ ሰዎች የሚኖሩበት ምክንያት፥ እውነተኛ የሆነ የሕይወት ለውጥ ሳያገኙ፥ ወይም ሳይድኑ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል፥ ወይም ለመምራት የሚፈልጉ ሰዎች በመኖራቸው ነው። የንግግር ደንብና ሥርዓት ማውጣት ብቻ ምላስን አይለውጠውም፥ ወይም ገንቢ አያደርገውም። ልቡ ሲለወጥ ምላሱም የተለወጠ ይሆናል። ስለዚህ ሰው ንግግሩ ጤናማ እንዲሆን ትልቅ ቀዶ ጥገና የሚያስፈልገው ምላሱ ሳይሆን ልቡ ነው።

በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግ የሚያደርገን መንፈስ ቅዱስ ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ ክርስቲያኖች እንዴት ማደግ እንዳለባቸው ሲዘረዝር፥ *"...በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፥ በበጎነትም እውቀትን፥ በእውቀትም ራስን መግዛት፥ ራስንም በመግዛት መጽናትን፥ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፥ እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፥ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ"* ይላል (2 ጴጥ. 1፥5-7)። እነዚህ ሐዋርያው ጴጥሮስ ከላይ የዘረዘራቸው ክርስቲያን ባሕሪዎች የምላሳችንን መልክና ውበት የሚለውጡ ናቸው። ዘማሪው፥ *"...የእግዚአብሔር ቸርነት፥ (በጎነት) ምድርን ሞላች"* ይላል (መዝ. 33፥5)። የተለወጠ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን በጎነት ለሌሎች ያሳያል። በጎነት፥ በጎ ሀሳብን በተግባር ለሌሎች መግለጽ ነው። በጎነት በተግባር ላይ የዋለ "ቸርነት" ነው። በፍቅር የተሞላው ሐዋርያው ዮሐንስ *"ወዳጅ ሆይ! በጎ የሆነውን እንጂ ክፉን አትምሰል። በጎ የሚያደርግ ከእግዚአብሔር ነው፥ ክፉን የሚያደርግ ግን እግዚአብሔርን አላየውም"* ይላል (3 ዮሐ. 11)። በዓለም ውስጥ ካለው ክፉ ነገር ውጪ ሆኖ መኖር ትልቅ የባሕሪን ጥንካሬ ይጠይቃል። ጳውሎስ *"መልካሙንና ደስ የሚያሰኘውን ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ እንድትችሉ፥ አእምሮአችሁ ታድሶ ሕይወታችሁ ይለወጥ እንጂ የዚህን*

ከሚያስኙት ነገሮች መካከል አንደኛው፣ አስፈላጊ በሆነው ጊዜና ቦታ ላይ ብቻ የሚናገር ሲሆን ነው። ሠለሞን *"...ለዝምታ ጊዜ አለው፥ ለንግግርም ጊዜ አለው..."* ይላል (መክብብ 3፥7)። ተገቢ የሆነውን ነገር በተገቢው ጊዜ መናገር፣ እንዲሁም ዝምታ በሚያስፈልግበት ጊዜ ዝም ማለት፣ መናገር በሚያስፈልግበት ጊዜ መናገር ያስደስታል። የብዙዎች ችግር አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ዝም ማለት አለመቻላቸው ነው። ዘማሪው የዝምታን አስፈላጊነት ሲጠቅስ፥ *"...በመኝታችሁ ሳላችሁ በልባችሁ አስቡ፥ ዝም በሉ"* ይላል (መዝ. 4፥4)። መናገር ልማድ የሆነባቸው አንዳንድ ሰዎች፥ ምላሳቸውን መግታት ባለመቻላቸው ምክንያት ራሳቸውን ትልቅ ችግር ውስጥ እንደሚከቱ የታወቀ ነው። ሠለሞን *"ከብዙ ንግግር ውስጥ ስሕተት አይጠፋም፥ ስለዚህ አስተዋይ ሰው ብዙ ከመናገር ይቆጠባል"* ያለው ለዚህ ነው (ምሳሌ 10፥19)። እንዲሁም ሐዋርያው ያዕቆብ *"...ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፥ ለመናገርና ለቁጣም የዘገየ ይሁን"* ይላል (ያዕ. 1፥19)። እኛ ግን ይህንን መመሪያ ችላ ብለን ለመናገርና ለመቆጣት የፈጠንን፥ ለመስማት ግን የዘገየን ነን።

ብዙ ጊዜ ከሰው ጋር ስንነጋገር፥ ተናጋሪው የሚለውን አናዳምጥም። የማናዳምጥበት ዋናው ምክንያት፥ ለሚናገረን ሰው የምንሰጠውን መልስ ስለምናስብ ነው። ተራችንን ጠብቀን መናገር ስንጀምር ደግሞ፥ የሚያዳምጠን ሰው፥ ለእኛ የሚሰጠውን መልስ ስለሚያስብ የምንናገረውን አይሰማም። በዚህ ዓይነት መንገድ ውይይታችን ከቀጠለ፥ ሁለታችንም የምንናገረው ሰሚ በሌለበት በመሆኑ ውይይታችን ፍሬ እንደሌለው ግልጽ ነው። አድማጭ በሌለበት መናገር ሞኝነት ነው። የምንሰማው ራሳችን ብቻ ከሆነ ከሌላው መማር አንችልም። ሠለሞን እንደነዚህ ዓይነቶቹን ሰነፍ ብሎ ይጠራቸዋል። *"ሰነፍ የራሱን አስተያየት ብቻ መግለጥ ይፈልጋል እንጂ፥ ዕውቀትን ከሌላ ሰው መገብየት አያስኘውም"* ይላል (ምሳሌ 18፥2)። ብዙ የሚናገር ሰው የሚናገረው ነገር ሲያልቅበት፥ ንግግሩን ማቆም እንዳለበት ስለማያውቅ፥ ያገኘውን ሁሉ፥ ጠቃሚነቱን ሳይመረምር ይናገራል። እውነቱን፥ እውነት ካልሆነው ጋር እየቀያየጠ፥ ለሰሚው ጸጋ የማይሰጠውን ሁሉ ዝም ብሎ ያወራል።



### 3.2/ <u>በምስጋና የተሞላ ይሆናል</u>

አንዳንድ ሰው በማመስገን ፈንታ ማጉረምረም፥ መውቀስ፥ መንቀፍ፥ ማማረር ወዘተ. ለምን ይቀለዋል? ብዙ ነገር ተደርጎለት ምስጋናው ትንሽ ነው፥ እንዲሁም ጥቂት ነገር ሳይሆንለት ሲቀር የሚያሰማው የምሬት ቃል ብዙ ነው። ብዙ ሲደረግለት ቆይቶ በአንድ ባልታወቀ ምክንያት አንድ ነገር ፈልጎ ማግኘት ያልቻለ እንደሆነ፥ ሲያደርግለት የቆየውን ሰው የወቀሳ፥ የነቀፋና የማጉረምረም መአት ያወርድበታል። መመስገን እንጂ ሌላውን ሰው ማመስገን አይፈልግም። መመስገን ለሚገባው ምስጋና መክልከል ሌላውን የሚጎዳ መሆኑን ማወቅ አለበት። ብዙ ጊዜ የሚያመሰግኑ ሰዎች ናቸው ሲመሰገኑ የምናያቸው። ኢትዮጵያውያን ብዙ ጥሩ ጥሩ ባህሎች አሉን። ሰው አክባሪነታችን፥ እንግዳ ተቀባይነታችን፥ ወላጆቻችንን መጠራችን፥ ታዛኸነታችን፥ እነዚህ ሁሉ ደስ የሚያሰኙና የሚያኮሩ ናቸው። የሚገርመኝ ግን "ማመስገን" ከባህላችን ውስጥ ለምን እንዳልተጨመረ ነው። የውጪ አገር ሰዎች ለሚደረግላቸው ለጥቃቅኑ ነገር ሁሉ "አመሰግናለሁ" ሲሉ እንሰማለን። ተሰደው አሜሪካን አገር መጀመሪያ የገቡ አውሮፓውያን ከጠበቁት በላይ ሁኔታዎች ስለተሳኩላቸው፥ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑበት ቀን ለዩ። ያንን ምክንያት በማድረግ በዓመት አንድ ቀን፥ በኅዳር ወር "የምስጋና ቀን" (Thanksgiving Day) በማለት አሜሪካውያን ሁሉ የሚያከብሩት የበዓል ቀን ሆነ።

በክርስትና ሕይወታችን ምን ያህል እንዳደግን የምንለካበት አንደኛው መንገድ በምንሰጠው ምስጋና ነው። ከውስጣችን በሚወጣው ማጉረምረም ወይም ምስጋና ማንነታችን ይለካል። ሁኔታዎች ልክ ሲመጡልን በምንሰጠው ምስጋና ሳይሆን፥ ያልጠበቅናቸው አንዳንድ ክፉ ነገር ሲደርሱብን በምናሰማው የምስጋና ወይም የምሬት ቃል ነው። በጎ ያልሆኑ ሁኔታዎች ሲገጥሙን ከውስጣችን ምን ዓይነት ነገር ይወጣል? መራራነት፥ ማጉረምረም ወይንስ መልካም መዓዛ ያለው የምስጋና ቃል ከውስጣችን ይወጣል? በመንፈሳዊ ሕይወታችን ማደጋችን በጤናማው ምላሳችን ይለካል። የልጆች ጸባይ ብዙ ጊዜ ማጉረምረም ነው። ህጻናትን ሁለት ሰዓት ታቅፈናቸው፥ ለአንድ ደቂቃ ስናስተኛቸው፥ ወይም ስናስቀምጣቸው "ዕሪ!"

ብለው ያለቅሳሉ። ያላደገም ክርስቲያን እንደዚሁ ነው። ጥቂት መልካም ያልሆነ ነገር በሕይወቱ ሲደርስበት፣ ከአፉ የሚወጣው ምሬትና ማጉረምረም ብቻ ነው።

እግዚአብሔርን ማመስገን ከመረጡት ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች መካከል አንደኛው ኢዮብ ነው። ኢዮብ በሕይወቱ ላይ በላዩ አደጋ ሲደርስበት በእግዚአብሔር ላይ ቦክስ ጨብጦ፣ "ለምን ይሄን ሁሉ መዓት አወረድክብኝ? ምን አደረግሁህ?" በማለት ክፉ ቃል ከአፉ አልወጣም። አደጋ ላይ በላይ ሲደራረብበት ሀዘን አልተሰማ ውም፣ ልቡ አልተሰበረም ማለት አይደለም። ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ መጎናጸፊያውን ቀድዶ፣ ራሱን ተላጭቶ በምድር ላይ ተደፍ ቷል። ነገር ግን በማማረር ፈንታ "...ራቁቴን ከእናቴ ማህጸን ወጥ ቻለሁ፣ ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ፣ እግዚአብሔር ሰጠ፣ እግዚ አብሔርም ነሣ፣ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን" አለ (ኢዮብ 1፥21)። የኢዮብ ሕይወት በመከራ ወፍጮ ሲታሽ ከውስጡ የወጣው የምሬት ቃል ሳይሆን፣ የምስጋና ቃል ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ጥሩ ግንኙነት የሌላቸው፣ ወይም ወደ ኋላ የተመለሱ ሰዎች የምስ ጋና ሰዎች አይደሉም። ጳውሎስ እንደነዚህ ዓይነቶቹ "...እነርሱ እግዚአብሔርን አውቀውት ሳለ ለእርሱ የሚገባውን ክብርና ምስጋና አልሰጡትም.." ይላቸዋል (ሮሜ 1፥21)። ብዙ ታላላቅ የእግዚአብ ሔር ሰዎች አፋቸው በምስጋና የተሞላ ነው። ከእነርሱ መካከል ሌላው ዳዊት ነው። መዝሙሮቹ አብዛኞዎቹ የምስጋና መዝሙሮች ናቸው። "...በሕዝብ ጉባኤ መካከል ሆኜ አመሰግንሃለሁ፣ ብዙ ሕዝ ብም በተሰበሰበበት ቦታ አከብርሃለሁ" (መዝ. 35፥18)። "...አምላክ ሆይ! በጽዮን ሆነን አንተን ማመስገን ...ይገባናል" ይላል (መዝ. 65፥1)። እንዲሁም "እግዚአብሔር ሆይ! አንተን ማመስገን፣ ልዑል አምላክ ሆይ! ስለ ክብርህ መዘመር እንዴት መልካም ነው" (መዝ. 92፥1) ይላል። ጳውሎስም መልዕክቶቹን ሁሉ ሲጽፍ የሚጀምረው እግዚአብሔርን በማመስገን ነው (ሮሜ 8፥1፤ 1 ቆሮ. 1፥4)።

ጤናማ ምላስ በምስጋና የተሞላ ምላስ ነው። አንዳንድ ሰዎች ዓይናቸው ሁልጊዜ እንከን ብቻ የሚያይ፣ ሁሉ ነገር ጨልሞ የሚ ታያቸው ናቸው። ብዙ ነገር ተቀብለው ጎልቶ የሚታያቸው ነቁጥ የሚያክለው መጥፎ ነገር ብቻ ነው። ሲታዘዛቸው ቆይቶ አንድ ቀን



"አልችልም" የሚላቸውን ሰው ጠላት የሚያደርጉ ናቸው። ነገርን ሁሉ በቀጥታ ማየት የማይችሉ፣ ሁሉን ነገር አጣመው የሚተረ ጉሙ፣ ሁሉ ነገር ተጣሞ የሚገባቸው ናቸው። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ማጉረምረምና መራራ ቃል እንጂ ከአፋቸው የምስጋና ቃል አይወ ጣም። የመርገም ቃል እንጂ የመባረክ ቃል የማይወጣቸው ናቸው። ከእግዚአብሔር ብዙ በጎ ነገር ተቀብለው፣ አንድ በጎ ያልሆነ ትንሽ ነገር ሲደርስባቸው፣ በእግዚአብሔር ላይ የሚያጉረመርሙ፣ የሚያ ማርሩ ናቸው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የምትሆነን የኢዮብ ሚስት ነች። "እስከ አሁን ፍጹምነትህን ይዘሃልን? እግዚአብሔርን ሰድበና ሙት አለችው" (ኢዮብ 1፥9)። ኢዮብ ግን "አንቺ ከሰነፎች ሴቶች እንደ አንዲቱ ተናገርሽ፣ ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀበልን፣ ክፉ ነገርንስ አንቀበልምን?" አላት፣ በዚህ ሁሉ ኢዮብ በከንፈሩ አልበደ ለም" ይላል (ኢዮብ 1፥10)። ጳውሎስ እንዲህ ዓይነቶቹን ሲመክር፣ "በመጥፎና በጠማማ ትውልድ መካከል ያለ ነቀፋ የዋሆችም ነውርም የሌለባችው የእግዚአብሔር ልጆች እንድትሆኑ ሳታንጎራጉሩ፣ ክፉም ሳታስቡ ሁሉን አድርጉ" ይላል (ፊል. 2፥14-15)።

በሕይወታችን በጣም ጎዱን የምንላቸው በጣም የቀረቡንና የቀ ረብናቸው ናቸው። አንዳንዶቹ ላደረግንላቸው በጎ ነገር፣ መልሰው በጎ ማድረግ ሲገባቸው፣ ክፉ ያደረጉብን ናቸው። በማመስገን ፈንታ የወቀሱን፣ በማድነቅ ፈንታ ስማችንን ያጠፉ ናቸው። በነዚህ ውለ ታቢሶች ሰዎች ልባችን ምን ያህል እንደተሰበረና እንዳዘነ የምናው ቀው በውስጡ ያለፍን ሰዎች ነን። ምስጋና በሌላቸው ሰዎች ይህን ያህል ልባችን የሚያዝን ከሆነ፣ እግዚአብሔርማ በእኛ ውለታቢስነት፣ በእኛ ምስጋናቢስነት ምን ያህል ልቡ ያዝን ይሆን? ምስጋና ቢስ መሆን እግዚአብሔርን ከሰው የበለጠ ያስቀይመዋል። በእግዚአብ ሔር ላይ ከምንፈጽመው ትልቅ በደል አንዱ፣ ምስጋና ቢስ ስንሆን ነው።

የምናመሰግነው እግዚአብሔርን ብቻ ሳይሆን፣ ምስጋና የሚገባ ቸውን ሰዎች ጭምር ነው። ቀኑን ሙሉ ስትለፋ የዋለች ሚስት፣ ምስጋና ስትጠብቅ ነቀፋና ትችት ሲደርስባት ምን ያህል ስብራት ይደርስባት ይሆን? ሚስት ብቻ ሳትሆን እንዲሁም ባል። ልጆች መልካም ነገር ሲያደርጉ ማመስገን፣ "ማጨማለቅ" የሚመስላቸው

ሰዎች አሉ። ጥሩ ሠርቼአለሁ ዛሬ እመሰገናለሁ ብለው ሲጠብቁ፥ ምክንያት ፈልጎ ወቀሳ ማብዛት ቤተሰብን ያራርቃል እንጂ አያቀራርብም። ጥሩ የቤት እመቤት፥ መልካም ትግባሯ በልጆቿም ሆነ በባሏ ፊት ሞገስ አግኝታ ትመሰገናለች። *"ልጆችዋ አድናቆታቸውን ይገልጡላታል፥ ባልዋም ያመሰግናታል"* (ምሳሌ 31፥28) ይላል። ጤናማ ምላስ ሲኖረን፥ በመንቀፍ ፈንታ የምስጋና፥ የማበረታቻ ቃል፥ በማፍረስ ፈንታ የሚገነባ ቃል ከአፋችን ይወጣል።

እግዚአብሔር መልካም የሆነውን ነገር ስለሚወድ፥ ለሰው ልጅ ምላስን የሰጠው፥ መልካም ነገርን እንዲናገርበት ነው። ከመልካም ነገር አንደኛው እውነትን መናገር ነው። ዘማሪው *"እነሆ! እውነትን ወደድህ..." ይለዋል (መዝ. 51፥6)። እውነትን የማይናገረውን ምላስ እግዚአብሔር ይጠላል። "እግዚአብሔር ሐሰተኞችን ይጠላል፥ ቃላቸውን በሚጠብቁ ታማኝ ሰዎች ግን ይደሰታል"* ይላል (ምሳሌ 12፥22)። የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ ባርነት በሙሴ መሪነት ነጻ ወጡ። ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት አርባ ዓመት ወሰዶባቸዋል። የሚገርመው ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት የጓጉና የጠበቁ ሳይገቡ ባት በምድረበዳ እንዳለቁ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ወተትና ማር ወደምታፈሰው ወደ ተስፋይቱ ምድር ብዙዎቹ መግባት ያልቻሉበት ምክንያት ምን ይሆን? ጣዖት አምላኪዎች፥ ዘማዊ፥ ጠብ ጫሪ በመሆናቸው ሳይሆን፥ መልካም ነገር ከአፋቸው እንዲወጣ በመፍቀድ ፈንታ፥ በጎ ባደረገላቸው እግዚአብሔር ላይ ክፉ ቃል በመናገራቸው ነው።

እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን *"እነዚህ ክፉዎች የሆኑ ሕዝብ በእኔ ላይ የሚያጉረመርሙት እስከ መቼ ነው? ይህን አሰልቺ የሆነ ጉርምርምታቸውን ሰምቻለሁ"* አላቸው (ዘኁልቁ 14፥27)። በዚህ ክፉ ንግግራቸው ምክንያት ምን እንደሚደርስባቸው ሲናገር፥ *"ሁላችሁም ትምታላችሁ፥ ሬሳችሁም በዚህ ምድረ በዳ ተበትኖ ይቀራል፥ በእኔ ላይ በማጉረምረማችሁ ምክንያት ከእናንተ መካከል ከሃያ ዓመት በላይ ዕድሜ ያለው ሁሉ ከቶ ወደዚያች ምድር አይገባም፥ ወደዚያች ምድር ገብታችሁ እንደምትኖሩ ቃል ገብቼላችሁ ነበር፥ ነገር ግን ከካሌብና ከኢያሱ በቀር ከእናንተ አንዱ እንኳ ወደዚያች ምድር አይገባም"* አላቸው (ዘኁልቁ 14፥29-30)። እስራኤላውያን በማጉረምረማቸው ምክንያት በምድረበዳ ሁሉም ጠፉ። ከባርነት ነጻ አውጥቷቸው ነበር፥ በጉዟቸው ላይ አንዳንድ ዕንቅፋት ባጋጠማቸው ቁጥር ግን በእግዚአብሔር ላይ አጉረመረሙ። ምስጋና ቢስ ሆነው፥ እያማረሩና እያጉረመረሙ በምድረ በዳ አለቁ። የማጉረምረም ዋጋው ሞት እንደሆነ እናያለን። በፍርድ ቀንም ዋጋቸውን እንደሚያገኙ እናውቃለን። ይሁዳም *"እነዚህ ሰዎች ሁልጊዜ የሚያጉረመርሙና በምንም ነገር የማይደሰቱ ናቸው፥ የራሳቸውን ክፉ ምኞት የሚከተሉ ናቸው፥ አፋቸው በትዕቢት ቃል የተሞላ ነው፥ የራሳቸውን ጥቅም በመፈለግ ሰውን ይለማመጣሉ"* ይላል (የይሁዳ መልዕክት 16)። ከተናገርን በኋላ የማይጸጸተንን፥ ሌሎችን የሚያንጽና የሚገነባ፥ ተገቢ የሆነውን ቃል ብቻ ለመናገር ራሳችንን እና ለማምድ።